GEBECON PLC

# ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ

# GEMSHU BEYENE CONSTRUCTION PLC

*Paving the Way for Development!*









ዓመታዊ መጽሔት፤ ነሐሴ 2012
Annual Publication, August 2020

ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ
**Gemshu Beyene Construction PLC**

Tel:. +251-11-618 9550
Fax:. +251-11-663 0462
P.O. Box: 29228
Addis Ababa, Ethiopia
Email: info@gebeconstruction.com
www. gebeconstruction.com

*Paving the Road for Developmen!!!*

ማውጫ
# Content


| | | |
|---|---|---|
| i | የካምፓኒው ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች<br>Vision, Mission and Values of the Company | 01 |
| 1 | የዋና ሥራ አስኪያጁ መልዕክት<br>Message of General Manager | 03 |
| 2 | የምክትል ዋና ሥራ አስከያጅ መልዕክት<br>Message of Deputy General Manager | 05 |
| 3 | የ2012 የደርጅታችን ልዩ የድርጅታችን ገጠመኝ ቅኝት<br>Special Experience of the Year | 08 |
| 4 | ዓመታዊ የግንባታ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም<br>Annual Performance of Construction Projects | 15 |
| 5 | ውጤታማ የሥራ ቦታ ቡድን ግንባታ መንገዶች<br>The Way for Effective Team Building in the Workplace | 30 |
| 6 | በገበኮን የሰው ኃይል ውጤታማነትን ለማጠናከር የሚያስችል ስልጠና ተሰጠ<br>GEBECON Has Conducted Human Resource Capacity Building Training | 42 |
| 7 | የገበኮን የ2011 የሥራ ዘመን አመታዊ የሠራተኞች ጉባኤ ተካሄደ<br>2012 EFY GEBECON Annual Staff Assembly Has Held | 45 |
| 8 | ገበኮን የኮቪድ 19 ወረርሽን የመከላከል ዘመቻን ስኬታማ ለማድረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጀመረ<br>GEBECON Launches COVID-19 Mitigation Campaign | 50 |
| 9 | የሥራ ቦታ COVID-19 መከላከያ እና ቁጥጥር ምክሮች<br>Tips on Workplace COVID-19 Prevention and Controls | 52 |
| 10 | የመዝናኛ ገጾች<br>Entertainment Pages | 59 |

# የካምፓኒው ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች

## ራዕይ

የገበኮን ራዕይ በኮንስትራክሽን ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለውና ግንባር ቀደም ኩባንያ ሆኖ መገኘት ነው።

## ተልዕኮ

ተልዕኮአችን በተመጣጣኝ ወጪና በኮንትራት ውል መሠረት በወቅቱ አጠናቅቆ በማስረከብ ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያላቸው የግንባታ ሥራዎችን በተመጣጣኝ ወጪና በኮንትራት ውል መሠረት በወቅቱ አጠናቅቆ በማስረከብ ደንበኞቻችንና ባለድርሻ አካላትን ማርካት ነው፡፡ ይህንን ተልዕኮአችንን ለማሳካት፡-

የምንከተላቸው ስልቶች፤

- ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና ጠንካራ የማኔጅመንት ሥርዓት በመዘርጋት የኩባንያው የፋይናንስ አቅም አስተማማኝ ማድረግ፤
- አዳዲስ ለውጦችን ከተወዳዳሪዎቹ ቀድሞ በጥራትና ቅልጥፍና ተግባራዊ በማድረግ በአገሪቷ የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ጥራት ማሳደግ፤
- የኩባንያውን የውስጥ አቅም ለመገንባትና የተሻሻሉ የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ዘዴዎችን ለመጠቀም በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ከሆኑ የውጭ አገር የኢንጂነሪንግ ዲዛይንና ኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ጋር ተባብሮ መሥራት፤
- የግንባታ ሥራዎችን በተፈለገው ጥራትና ጊዜ እንዲጠናቀቁ አስተማማኝ አቅርቦት መኖሩን ለማረጋገጥ በግንባታ ማቴሪያሎች አቅርቦት ሥራ ውስጥ መግባት፡፡

## እሴቶች

- የተሻለ የሠራተኛ ተነሳሽነትና ቆይታን ማበረታታት፤
- የቡድን ስሜትና ምን ጊዜም የመማር ዝንባሌን ማሳደግ፤
- መልካም ባህሪያትን (ሐቀኝነት፤ታማኝነትና የዳበሩ እውቀቶችን) ማበረታታትና በሞዴልነት መጠቀም፤
- ለሠራተኞቻችን ትኩረት ሰተን የእነሱን ሙሉ ድጋፍና ቁርጠኛ ተሳትፎ ማሳደግ፤
- ከባለድርሻ አካላት ጋር ቀጣይነት ያለው ግንኙነት ማዳበር፤
- ለውጦችን በመልካም አጋጣሚነት መውሰድ፤
- ግልጸኝነት፤ተጠያቂነትና የሙያ ሥነ-ምግባር በኮንስትራክሽን ዘርፍ ማስፋፋት፡፡

# Vision, Mission and Values of the Company

## Vision

GEBECON PLC envisions becoming an internationally reputable and leading company in the construction sector.

## Mission

Our mission is to meet the expectations of our clients and stakeholders by undertaking high quality construction works at reasonable cost and within the contract period. To achieve our mission, we:

- Put in place strong and modern construction management systems and technologies to grow into a financially sound construction company;
- Take a long term perspective by implementing important changes, more effectively and efficiently than our competitors, to improve the quality of construction management in the country;
- Partner with renowned companies engaged in the area of engineering design and construction, local and overseas, as a strategy to build in-house capacity and facilitate the adoption of best construction management practices; and
- Engage in the business of construction related supplies to ensure the reliability and delivery of construction works on time and within stated quality standards

## Values

- Foster improved staff motivation & retention.
- Cultivate life-long learning and employee team spirit.
- Model and reward good behavior (honesty, loyalty, resourcefulness.)
- Treasure staff to gain their full support and commitment.
- Build & maintain synergy with stakeholders.
- Embrace challenge as an opportunity, and
- Promote transparency, responsibility and professionalism in the construction sector.

# የዋና ሥራ አስኪያጁ መልዕክት
# Message of General Manager



**Ato Gemshu Beyene**
General Manager
**አቶ ገምሹ በየነ**
ዋና ሥራ አስኪያጅ

በ2012 የሥራ ዘመን ኩባንያችን እንደወትሮው የሥራውን አፈጻጸም ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገርና የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ በዕቅድ የተደገፈ ዝግጅት በማድረግ ወደ ተግባር የገባበት ዓመት ነበር፡፡ በተግባር ሂደት ውስጥ ያልተጠበቀ ተግዳሮት ያስተናገደበት ዓመት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከልማት ዕቅዱ በጊዜያዊነት ቢደናቀፍም፣ በመላው የኩባንያው ማህበረሰብ፣ በመንግሥት አካላት እና በህዝቡ ያልተቆጠበ ድጋፍና ርብርብ ከሞላ ጎደል ውጤታማ ተግባር ለመፈጸም ችሏል፡፡

በዚህ ዓመት በካምፓኒያችን በግንባታ ላይ የነበሩት ስምንት ፕሮጀክቶች ሲሆኑ፣ እነዚህም አምስት የመንገድ ሥራዎች፣ ሁለት የህንጻ ግንባታና አንድ የመስኖ ውሃ ግድብ ሥራ ናቸው፤ ከእነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል ሁለቱን የህንጻ ግንባታዎች ማለትም የአርሲ ዩንቨርስቲ እና የኢሊሊ ሆቴል ማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን ሙሉ በሙሉ በማጠናቀቅ ለማስረከብ ተችሏል፡፡ ከአምስቱ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች መካከል ሶስት ፕሮጀክቶች እና አንድ የመስኖ ውሃ ግድብ ፕሮጀክት አፈጻጸማቸው ጥሩ ሊባል በሚችል ደረጃ ላይ ናቸው፡፡ ከኮክንስትራክሽን ዘርፍ በተጓዳኝ የቢዝነስ ሥራችንን ለማስፋፋት በማኑፋክቸሪንግና በሌሎች ዘርፎች መሰማራት እንዲቻል አዲስ እህት ካምፓኒ-አሜን ማኑፋክቸሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር-በማደራጀት የታሸገ ውሃ በማምረት ወደ ገበያው ለመቀላቀል እና የእምፖርት እክስፖርት ዘርፍ ላይም ለመሰማራት የሚያስችሉ  ተግባራትን መፈጸማችንም መጠቀስ ያለበት ተግባር ነው፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ መሀል ሜዳ-ዓለም ከተማ እና ዓለም ከተማ-ደጎሎ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች ላይ ጥቅምት 16 ቀን 2012 ዓ.ም. በአከባቢው ተፈጥሮ የነበረውን የጸጥታ ችግር ተከትሎ በተቃጣው ጥቃት ሳቢያ ከፍተኛ ቁሳዊና ሰብአዊ ጉዳት በመድረሱ የፕሮጀክቶቹ ሥራ ሙሉ በሙሉ እንዲቋረጥ ከማስገደድም አልፎ በሌሎች ፕሮጀክቶችም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማስከተሉ በዓመቱ ያጋጠመን ያልተጠበቀ ከፍተኛ ተግዳሮት ነበር፤ ይህም ሆኖ የዓለም ከተማ-ደጎሎ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ለወራት ግንባታው ከተቋረጠ በኋላ በሙሉ አቅምም ባይሆን መልሶ ግንባታውን ማስቀጠል ተችሏል። በዕቅዳችን መሰረት እስከ ዓመቱ አጋማሽ ድረስ አምስት ከመቶ

As always 2012 E.C. was the year when the company went into action in accordance with proper planning to deliver better results. During the year, although the company encountered unprecedented challenge that temporarily impeded it from its development plan it has more or less managed to become effective with a concerted effort of the entire company community, government bodies and the wider public.

The year saw the company's operation of eight projects namely; five road projects, two building and one water irrigation dam work. Of these projects the two building projects i.e. Arsi University and Elilly Hotel Expansion projects have been completed and transferred to the client. Three of the five road projects and the irrigation dam project are also making good progress. In a bid to expand our businesses to manufacturing and other sectors beside to the construction sector we have launched a new sister company called Amen Manufacturing PLC that has already completed its preparation activities to begin with entering into bottled water production and import-export businesses.

In the meantime, the attack on October 27, 2019 at Mehalmeda-Alemketema and Alemketema-Degolo road projects due to the security problem happened in the areas has brought significant material and human damages and ultimately terminated these projects. This unprecedented incident has also negatively affected other projects. However, after months of termination we managed to partially

የማይበልጠውን ቀሪ ሥራ ሙሉ በሙሉ አጠናቅቆ ለማስረከብ ታቅዶ የነበረው የመሀል ሜዳ-ዓለም ከተማ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ግን በዚሁ በአካባቢው ተፈጥሮ በነበረው ችግር ምክንያት ውሉ ተቋርጧል፤ የዚህ ፕሮጀክት ሥፍራ አስቸጋሪ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ከዲዛይን መለዋወጥ ጋር ተዳምሮ ካምፓኒያችን ብዙ ዋጋ የከፈለበት እንደመሆኑ መጠን ይህንን ፕሮጀክት አጠናቀን ለምርቃት በቅቶ የልፋታችንን ውጤት ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር የደስታው ተካፋይ ለመሆን ያለመታደላችን በእጅጉ የሚያስቆጨን ክስተት ሆኖ አልፏል፡፡

ለዓለም አገራት በሙሉ ስጋትና ፈተና የሆነው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝም በበጀት ዓመቱ በካምፓኒያችን የሥራ አፈጻጸም ላይ የራሱን አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳረፉም ሌላኛው የሚጠቀስ እንቅፋት እንደነበር ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደልም፡፡ በዚህ ረገድ በሽታው በድርጅቱ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመግታት የመከላከል እርምጃዎችን ከመውሰድ ጎን ለጎን በዚህ ዓመትም ድርጅታችን ማኅበራዊ ኃላፊነቱን በትጋት የመወጣት ልማዱን በማስቀጠል ከቫይረሱ ወረርሽኝ ህብረተሰቡን መከላከል ይቻል ዘንድ የንጽህና መስጫ ቁሳቁሶችን ለግሷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች አገራዊ እገዛ ሲያደርግ የቆየ ሲሆን፣ ባጠቃላይ ሃያ አምስት ሚሊዮን ብር የሚገመት ገንዘብ ለዚሁ አገልግሎት እንዲውል አድርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ ያጋጠመን ያልተጠበቀ አደጋ ያደረሰብንን ጉዳት በመቋቋም የጀመርናቸውን ፕሮጀክቶች ለማስቀጠል ስናደርግ የነበረውን ጥረት ለውጤት እንዲበቃ ሳትታክቱ ከጎናችን ሆናችሁ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ስትደግፉንና ስታበረቱን ለነበራችሁት መንግሥታዊ አካላት፣ የሥራ አጋሮቻችን፣ መላው የድርጅቱ ሠራተኞችና አመራሮች በሙሉ ያለኝን ታላቅ ምስጋናና አክብሮት በዚህ አጋጣሚ ከልቤ ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም በያዝነው በጀት ዓመትም እራሳችንና ህብረተሰባችንን ከኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ እየጠበቅን ለተሻለ ውጤትና ስኬት በጋራ ጠንክረን በትጋት እንደንሰራ ጥሪ እያቀረብኩኝ፣

ዓመቱ የሰላም፣ የስኬትና የብልጽግና እንዲሆንልን በመመኘት መልዕክቴን አስተላልፋለሁ፡፡

አመሰግናለሁ!

resume the construction of Alemketema-Degolo road project. Regardless of our plan to accomplish the remaining five percent of the work of Mehalmeda-Alemketema road project until the first half of the year had not been met due to the aforementioned incident and the contract come to termination. Given the topographic nature of this project the company incurred considerable cost that was attributed to design changes, and we regret to have missed the opportunity of seeing the completion of this project and cherish the fruit of our hard work with the local community.

The challenge paused by coronavirus global pandemic also affected negatively on the company's operation during the year. In this regard, besides undertaking various mitigation measures that helps prevent the spread of the virus into the company, we continued to discharge our social responsibility by donating sanitary materials to the public. In addition to this the company has been contributing to the national social services amounting to twenty-five million Birr.

I would like to pay my sincere gratitude to governmental bodies, partners, the entire employees and management of the company for supporting and encouraging us in our effort to overcome the unprecedented incident and bring the projects' work into a right track.

Finally, I call up on everyone to protect ourselves and the public from the coronavirus pandemic and work towards better results and accomplishment at this fiscal year.

I wish you all a year of peace, success and prosperity.

**Thank you!**

# የምክትል ዋና ሥራ አስክያጅ መልዕክት
## Message of Deputy General Manager



**Eng. Girma Guluma**
Deputy General Manager
**ኢንጂነር ግርማ ጉሉማ**
ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ

በሥራ ዓለም ውስጥ የሚፈለገውን ውጤት በማስመዝገብ ወደሚፈለገው ስኬት ለመድረስ የሚደረግን ጉዞ ለማሳካት ይቻል ዘንድ ጊዜን በአንጻ በመከፋፈል ተግባራትን በቅደም ተከተላቸው ሰድሮ በማቀድ መምራት የግድ ነው፤ በ2012 የሥራ ዘመንም ድርጅታችን ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ያለፈውን ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም በመገምገም ጥንካሬውንና ድክመቱን በመለየት በተሻለ አፈጻጸም የበለጠ ውጤትን አልሞ ወደ ተግባር የገባበት ዓመት ነበር፡፡ በበጀት ዓመቱ ስንፈጽም የነበረው በዕቅዳችን ያስቀመጥናቸውን ተግባራትን ለማሳካት ብቻም ሳይሆን ያልተጠበቀ አደጋ ያስተናገድንበት ዓመትም ስለነበረ የአደጋውን ተጽዕኖ ለመቋቋምና ጉዳቱንም ለመቀነስ ብዙ ተግባራትን የፈጸምንበት ዓመት ነበር፡፡ ለሆነው ነገር ሁሉ በቅድሚያ ለፈጣሪያችን ምስጋና የተገባ ይሁን፡፡

በዓመቱ በካምፓኒያችን ግንባታ ላይ የነበሩት ፕሮጀክቶች በአጠቃላይ ስምንት ሲሆኑ፣ እነሱም አምስት የመንገድ፣ አንድ የመስኖ ውሃ ግድብ እና ሁለት የህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶች ናቸው፤ ባለፈው ዓመት ግንባታቸው የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ደርሰው የነበሩት የአርሲ ዩኒቨርስቲ ህንጻ ግንባታ እና የኢሊሊ እንተርናሽናል ሆቴል ማስፋፊያ ሁለገብ ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶችን በዚህ ዓመት ሙሉ በሙሉ በማጠናቀቅ ለርክክብ ማብቃታችን በቅድሚያ የሚጠቀስ የተሳካ ተግባር ነው፡፡

ባለፈው በጀት ውል የተገባበትና ድርጅታችን የግንባታ ሥራ ዘርፉን ለማስፋት በያዘው የአምስት ዓመት የቢዝነስ መሪ ዕቅድ መሰረት አዲስ የጀመረው የሞጆ መስኖ ውሃ ግድብ ፕሮጀክት ሲሆን፣ ፕሮጀክቱም ከአዲስ አበባ ከ600 ኪሜ ርቀት ላይ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ ምስራቅ ሐራርጌ ዞን፣ መዩ ሙሉቄ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ በዚህ ዓመት አስፈላጊውን የሰው ኃይልና የግንባታ ግብአት አቅርቦት ተግባራትን በማከናወን በተሟላ ደረጃ ወደ ሥራ ተገብቷል፤ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ሲገመገም የፕሮጀክቱ ሥፍራ ከዋና መሥሪያ ቤት ካለው ርቀትና ካጋጠመው የዲዛይን ጉድለት ጋር ተያይዞ አደናቃፊ ሁኔታዎች ከማጋጠማቸው አንጻር ሲመዘን ጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

In order to attain the desired outcome in the world of work it requires budgeting time in accordance to activities. The EFY 2012 was the year when Gemshu Beyene Construction PLC has evaluated the previous year plan accomplishment to identify its strength and weakness at the course of planning and went into operations with ways to execute better performance.

During the budget year we have not only been implementing the plans we set but we had to undertake various activities to reduce the impacts of the unprecedented incident we sustained. We thank our Lord for everything that has happened. The year saw the company's operation of eight projects namely; five road projects, two building and one water irrigation dam work. The full completion of these two building projects namely Arsi University and Elilly Hotel Expansion building projects which were at their last phase in the preceding year was one of the major successes of the year.

The Modjo Medium Scale Irrigation Dam project was entered into contract last year as part of the company's five-year strategic plan to expand the construction sector. The project is located at 600 KM away from Addis Ababa in Meyu Muluke Wereda, East Harerge Zone of State of Oromia. Once provided with the relevant human and material resources the project has entered into full construction phase this year. Compared to its remote location from the Head Office and issues related to the design, the project is in good progress.

የተቀሩት አምስቱ የአስፓልት መንገድ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ በዚህ ዓመት ድርጅታችንን በቀን 16 ጥቅምት 2012 ዓ.ም በመሀል ሜዳ-አለም ከተማ እና በአለም ከተማ-ደጎሎ ፕሮጀክቶች ላይ በተፈጸመው ያልታሰበ ሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያት የደረሰው ከፍተኛ ጉዳት በመንገድ ፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አሉታዊ ተጽዕኖ ማስከተሉ አልቀረም፤ አደጋው በቀጥታ የደረሰባቸው ሁለቱም ፕሮጀክቶች በዚሁ ምክንያት ሙሉ በሙሉ ተቋርጠው እንዲቆዩም አስገድዶ ነበር፤ አደጋው በተፈጠረበት ወቅት የመሀል ሜዳ-አለም ከተማ ፕሮጀክት ከ95 ከመቶ በላይ ደርሶ የነበረና ቀሪውን ሥራ እስከ ዓመቱ አጋማሽ ለማጠናቀቅ፣ እንዲሁም የአለም ከተማ-ደጎሎ ፕሮጀክት አብዛኛው የመሬት ቆረጣ ተግባራት የተጠናቀቀ ስለነበር የድርጅቱን የማሽነሪና የሰው አቅም ወደ ሌሎች ፕሮጀክቶች ለማዛወር ታቅዶ እየተሰራ ሳለ የተፈጸመ በመሆኑ የጉዳቱ እንድምታ ተሻጋሪ አድርጎታል፡፡

ይህም ሆኖ የመሀል ሜዳ-አለም ከተማ ፕሮጀክት በመጠናቀቅ ላይ የነበረ በመሆኑ የመንገዱ ባለቤት በራሱ ለማከናወን ውሉ ሙሉ በሙሉ እንዲቋረጥ ቢደረግም፣ የአለም ከተማ-ደጎሎን ፕሮጀክት ለወራት ከተቋረጠ በኋላ ድርጅታችን በሰው ኃይልና በግንባታ መሳሪያዎች መልሶ በማደራጀት በሙሉ አቅም ባይሆንም ሥራውን ለማስቀጠል ችሏል፡፡ የጊንጪ-ሽኩቴ እና የአምቦ ከተማ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች ነባር ፕሮጀክቶች ሲሆኑ፣ በ2010 ዓ.ም በድርጅቱ ላይ ተፈጽሞ በነበረው ኃላፊነት በጎደለው መልኩ ከስድስት ወራት በላይ በዘለቀው የባንክ ሂሳብ እገዳ ምክንያት ግንባታቸው በመደናቀፉ የተንከባለሉ ውዝፍ ሥራዎች መኖራቸውን ታሳቢ በማድረግ እና በመሀል ሜዳ-ዓለም ከተማ እና በዓለም ከተማ-ደጎሎ ፕሮጀክቶች ሥራ ላይ ተሰማርተው የነበሩትን የግንባታ መሳሪያዎችን በማዛወር ግንባታቸውን ለማፋጠን ታቅዶ የነበረ ሲሆን፣ በተከሰተው አደጋ ምክንያት እንቅፋት ቢፈጠርም የተለያዩ ስልቶችን በመቀየስ ግንባታቸውን ወደ ፊት ለማስኬድ ተችሏል፡፡

የሽኩቴ-ጩሉጤ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ባለፈው ዓመት ውል የተገባበት አዲስ ፕሮጀክት መሆኑ ይታወቃል፤ በድርጅቱ ላይ የተቃጣው ጥቃት በዚህም ፕሮጀክት ላይ በተመሳሳይ አሉታዊ እንድምታው ያረፈ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ ለግንባታው የሚያስፈልጉ የሰው ኃይል አደረጃጀት፣ የካምፕ ግንባታን እና ሌሎች የግንባታ ቅድመ ዝግጅት ተግባራትን ከማከናወን አልፎ በአጭር ጊዜ ውስጥ የአፈር ቆረጣና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት ተከናውኗል፡፡

ድርጅታችን ያጋጠመው ያልታሰበ አደጋ የሚያስከትለውን ጉዳት በመቀነስ ተግዳሮቶቹን ተቋቁሞ የድርጅቱን ህልውና ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ አያሌ ተግባራት ተፈፅመዋል፤ ዋንኞቹን ለመጥቀስ ያክል፡-

- በአደጋው ምክንያት ከሥራቸው የሚፈናቀሉትን ሰራተኞች ቁጥር ለመቀነስ እንደየችሎታቸውና ሙያቸው ባሉት ፕሮጀክቶች ላይ ለይቶ የመመደብ ተግባር መፈጸሙ፣
- ከጉዳቱ የተረፉትን የግንባታ መሳሪያዎች ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ጥበቃውን የማጠናከር እና በመጨረሻም ከአካባቢው መውጣት ያለበትን ከሚመለከተው የክልልና የፌዴራል መንግሥት አካላት ጋር በመነጋገር ማስወጣት፣

The performance of the remaining five asphalt road projects have been directly and indirectly affected by the manmade incident occurred on October 27, 2019 at Mehalmeda-Alemketema and Alemketema-Degolo road projects. The incident had forced the construction work of these two projects to fully stop. When the incident had occurred the 95 percent of Mehalmeda-Alemketema project had been completed and the remaining work was set to complete before the first half of the year, while much of the Earthwork of Alemketema-Degolo project was completed the company was preparing to move its machineries and the workforce to other projects. This situation made the scale of the damage significant.

Since the Mehalmeda-Alemketema project was on the verge of completion it comes to terminate the contract so that the client would undertake the remaining work, however after months of ceasing the work the company has managed to continue the work at Alemketema-Degolo project after deploying limited workforce and machineries to the site. Due to the irresponsible freezing of the company's bank for more than six months in EFY 2010 the Ginchi-Shikute and Ambo Town Internal road projects were faced unexpected obstacle eventually leads works to delay; on the other hand the plan was to facilitate these projects after relocating machineries from Mehalmeda-Alemketema and Alemketema-Degolo road projects due to the incident however the company managed to implement various strategies to move forward these projects.

It is to be recalled that the contract of Shikute-Chulute road project was entered last year; similar to the other projects the attack triggered against the company has also negatively affected this project however, during the budget year the necessary inputs for the project such as organization of the workforce, construction of camp and other preparation works were completed along with quick Earthwork and related activities.

In order to ensure the resilience of the company by reducing the impact of the incident numerous tasks have been carried out. Some of these are;

- Reassignment of employees who have lost their jobs due to the incident as per their skills and profession to other projects;
- Enhancing the security to protect the remaining

- በአደጋው ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን የግንባታ መሳሪያዎችንና ተሽከርካሪዎች ጥገና ተደርጎላቸው ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ከማድረግ በተጓዳኝ በሌሎች ፕሮጀክቶች ላይ ተሰማርተው በተለያየ እክል ከሥራ ውጪ የሆኑትንም በልዩ ትኩረት ጥገና ተደርጎ ለአገልግሎት ማብቃት፣
- በአደጋው ምክንያት ተቋርጦ የነበረውን የአለም ከተማ-ደጎሎ ፕሮጀክትን ምንም እንኳን ድርጅቱ ከአደጋው በፊት ወደነበረው አቋሙ ያልተመለሰ ቢሆንም ከእንደገና መልሶ በሰው ኃይልና መሳሪያ በማደራጀት የግንባታው ሥራ እንዲቀጥል ማስቻል እና
- የግብኣት አቅርቦት እና የክትትልና ድጋፍ ተግባራትን በማጠናከር ሲፈጸሙ የነበሩትን ክንውኖች ማንሳት ይቻላል፡፡

በዚህ አጋጣሚ ለጥረቶቻችን ውጤታማነት መላው የድርጅታችን ሠራተኞችና አመራሮች፣ የሥራ አጋሮቻችን እና መንግሥታዊ አካላት ላደረጉት ያልተቆጠበ የድጋፍ አበርክቶት ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፤ በተለየ ሁኔታ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅና ባለቤት በአደጋው ተቋርጦ የነበረውን ፕሮጀክት ሥራ ለማስጀመር እና የጊንጪ-ሽኩቴ ፕሮጀክት ሥራ እንዲፋጠን ልዩ ትኩረት በመስጠት ተንቀሳቅሰው ለፈጸሙት ተግባር በድርጅቱ ማኔጅመንት፣ በሠራተኞች እና በራሴ ስም ከልቤ ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡

እነዚህ ጥረቶች መደረጋቸው እንደተጠበቀ ሆኖ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ በበጀት ዓመቱ ያጋጠመን ያልተጠበቀ ተግዳሮት በዕቅዳችን አፈጻጸም ላይ ያሳረፈው ተጽዕኖ የፕሮጀክቶቹ ግንባታ ተግባራት ወደ ቀጣይ ዓመት ከመንከባለል ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ያለመቻሉ ነው፡፡ በመሆኑም በቀጣይ በጀት ዓመት የሚናቅዳቸው ተግባራትም ይህንኑ እውነታ ከግምት ያስገቡ እንዲሆኑ የሚያስገድድ እንደመሆኑ መጠን ከምን ጊዜውም በላይ የሁሉንም የድርጅቱ ማህበረሰብ የተለየ ርብርብ እና ትጋት የሚያስፈልግበት ዓመት ነው፤ መላው የድርጅታችን ሠራተኞች እና አመራሮች ከወዲሁ ይህንኑ ተገንዝበው በቀጣይ እራሳችን እና ህብረተሰባችንን ከኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በንቃት እየጠበቅን፣ በትጋትና በቁርጠኝነት በተባበረ መንፈስ ለተሻለ ውጤት እንድንተጋ ጥሪ እያቀረብኩ፣

መጪው ዓመት የጤና፣ የሰላም፣ የስኬትና የብልጽግና እንዲሆንልን እመኛለሁ፡፡

አመሰግናለሁ!

machineries and vehicles as well as removing those which need to be in consultation with Federal and Regional authorities;

- Maintaining the damaged machineries and vehicles both due to the incident as well as those from other projects to redeploy them into the work;
- Although the company is unable to regain its position after the incident it managed to continue the Alemketema-Degolo road project, and;
- The strengthened input supply and follow-up are some of the activities among others.

At this juncture I would like to extend my heartfelt gratitude to employees and management of the company, partners and government bodies for their unreserved support and contribution for the success of our efforts. Especially, in the name of the management and the entire staff and myself I want to thank the Owner and General Manager of the Company for attentively working towards continuing the interrupted project as well as for quick implementation of the Ginchi-Shikute road project.

Given these efforts it should be noted that it is impossible to stop the negative impact imposed by the unprecedented incident during the budget year to continue in the following year against our plan of the project performance. Therefore, our planned activities for the next budget year will require taking this situation into consideration and special effort and diligence of the entire company community is expected more than ever. By taking note of these I call upon the entire members of the company and the management to actively protect our self and the public from coronavirus pandemic as well as to work in diligence in spirit of cooperation to deliver better results.

I wish us a year of health, peace, success and prosperity.

**Thank you!**

# የ2012 በጀት ዓመት ልዩ የድርጅታችን ገጠመኝ ቅኝት
# Special Experience of the Year



**Eng. Asfaw Diribsa**
D/General Manager Engineering Dep't

**ኢንጂነር አስፋው ድርብሳ**
የምህንድስና ዘርፍ ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ

*"ስኬታማ ለመሆን በጉዞ ሂደት የሚያጋጥሙትን ሁሉንም ፈታኝ ሁኔታዎች መቀበል እንጂ፣ የሚወዱትን ብቻ መርጦ መቀበል አይቻልም፡፡ " - ማይክ ካፍካ*

***"To be successful you must accept all challenges that come your way. You can't just accept the ones you like." – Mike Kafka***

## 1. መግቢያ

ድርጅታችን ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በግንባታ ሥራዎች ላይ መሳተፍ ከጀመረ ከአንድ ዓስርተ ዓመታት በላይ አስቆጠሯል:: በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ሸዋ ዞን በመርሃቤቴ ወረዳ እና በሚዳ ወረሞ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ የመሀል ሜዳ-አለም ከተማ እና አለም ከተማ-ደጎሎ የአስፓልት መንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ጋር በገባው የግንባታ ውል መሰረት በግንባታ ላይ እያለ በአለም ከተማና በአካባቢው ከተፈጠረ የጸጥታ ችግር ጋር ተያይዞ ያጋጠመው ክስተት ግን አዲስና ያልተለመደ ነበር፡፡ በዚህ ክስተት ሳቢያም የሁለቱም ፕሮጀክቶች ግንባታ ለጊዜው እንዲቆም አስገድዷል፡፡

ድርጅቱ በግንባታ ሥራ ላይ በቆየባቸው ዓመታት ሁሉ አጋጥሞት የማያውቅው እና በኮነስትራክሽን ሴክትሩም ያልተለመደ አዲስ ገጠመኝ እንደመሆኑ መጠን በድርጅቱ ታሪክ ውስጥ አሳዛኝም ቢሆን የራሱ የሆነ ሥፍራ እንዲኖረው የግድ ይላል፡፡

በዚህ መነሻነትም የክስተቱን ሁኔታ፣ አደጋውን ለመቆጣጠር የተደረጉትን ጥረቶችና የተለያዩ አካላት በሂደቱ የተጫወቱትን ገንቢ ሚና፣ የአደጋው እንደምታ እና ከክስተቱ የተቀሰሙትን ትምህርቶች በዚህ ጽሁፍ ባጭሩ ለማስቃኘት ተሞክሯል፡፡

## 1. Introduction

It has been more than a decade since Gemshu Beyene Construction PLC has engaged in the construction sector. The company has entered into contractual agreement with the Ethiopian Roads Authority to construct the Mehalmeda-Alemketema and Alemketema-Degolo road projects located in Merha Bete and Mida Weremo Woredas of North Shewa Zone in Amhara Regional State. However the security related incident that has occurred in Alemketema Town and its surrounding was unique and unusual for the company, forcing the temporarily suspension of the two projects. This unforeseen incident shall have its own place both for the company and for the construction sector in general.

Accordingly, this piece tries to present the situation, efforts made to control the incident and positive role played by various actors as well as its impact and lessons learned from the incident.

## 2. The Incident

The company, since taking over the construction of Mehalmeda-Alemketema asphalt road project, has been active in the area for the past four years. During this period the company has been working in collaboration with the local administration and community while getting the necessary support and cooperation from them. As the saying goes "not every day is lucky day" the incident occurred on 27 October 2019 Sunday morning around 9:45AM when the company's Isuzu car carrying

## 2. የአደጋው ክስተት

ድርጅታችን የመሀል ሜዳ-አለም ከተማ አስፓልት መንገድ ግንባት ፕሮጀክትን ከተረከበበት ጊዜ አንስቶ ላለፉት አራት ዓመታት በአከባቢው ሲንቀሳቅ ነበር፤ በእነዚህ ጊዜያት ሁሉ ከአከባቢው አስዳደርና ህብረተሰብ ጋር መልካም ግንኙነትን በመመስረት አስፈላጊው የሥራ ትብብርና ድጋፍም ከእነዚሁ አካላት እየተደረግለትና እያገኘ ውጤታማ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ ሆኖም "ሁሌ ፋሲካ አይደልም" እንደሚባለው የነበረውን መልካም ነገር በአንዲት ቀን ያልተጠበቀ መጥፎ ክስተት ሁሉም ነገር ወደአልተፈለገ ሌላ ገጽታ ሊቀየር ችሏል፡፡

ክስተቱም በእለተ እሁድ፣ ጥቅምት 16 ቀን 2012 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 3፡45 አካባቢ በአለም ከተማ ለሠራተኞች ምሳ ጭኖ ወደ ግንባታ ስፍራ ሲጓዝ በነበረ የድርጅቱ ንብረት በሆነው አይሱዙ መኪና ላይ ተልዕኳቸው በግልጽ ባልታወቀ ግለሶቦች ጥቃት በማድረስ ተጀመረ፡፡ በመቀጠል ይኸው ኃይል በመሰባሰብ በሠራተኞች መኖሪያ ካምፕ ላይ ጥቃት ለመሰንዘር ሙከራ አድርገው ሳይሳካላቸው ሲቀር በቀጥታ የመንገድ ግንባታ ወደሚካሄድባቸው ሥፍራዎች አመሩ፡፡ በእነዚህ ሥፍራዎች በሥራ ላይ ተሰማርተው በነበሩት የድርጅቱ የግንባታ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ላይ የቃጠሎና የመሰባበር ጉዳት ማድረሱን ተያያዙት፡፡ የጥፋት ኃይሉ ጥቃቱን በማፋፋም ወደ ካምፑም ዳግም በመመለስ እና ሁለቱም ፕሮጀክቶች ወደ ሚገኙባቸው አካባቢዎች በመንቀሳቀስ የአገር መከላከያ ሰራዊት በሥፍራው ደርሶ አካባቢውን እስከ ተቆጣጠረበት ከምሽቱ አራት ሰዓት ድረስ የዘለቀ ውድመት ማድረሱን ቀጥሎበት ነበር፡፡

ጥቃቱን ተከትሎ በመንገድ ግንባታ ሥራ ላይ እና በካምፕ ውስጥ በቢሮ ሥራ ላይ የነበሩት ሠራተኞች በሁለት አቅጣጫ አጎራባች ወረዳዎች ወደ ሆኑት ሚዳ ወረሞ እና በመንዝ ቀያ ገብርኤል ወረዳ እራሳቸውን ከጥቃቱ ለማዳን በእጃቸው የነበሩትን ተሽከርካሪዎች በመጠቀም ከአደጋው ለማምለጥ ችለዋል፡፡

employee's lunch was attacked by a group of individuals whose intentions were not clear. Following this the group attempted to attack the project camp and wasn't succeeded. Then they moved to the project sites and continued to burn and broke the construction machineries and vehicles. The violent group went back to the camp and expanded its attacks to the two project sites. The damaging attack had continued through 10PM in the evening until the National Defense Force took control of the area. At this moment employees who was on duty both at camp offices and project sites managed to escape the attackers to the neighboring Woredas of Mida Weremo and Menz Keya Gabriel using the company's vehicles they could find.







Partial Picture of Totally Destroyed Property at Project Site

## 3. አደጋውን ለመቆጣጠርና ጉዳቱን ለመቀነስ የተወሰዱ እርምጃዎች እና የባለድርሻ አካላት ሚና

በፕሮጀክቶቹ ላይ የተቃጣውን ጥቃት ገና ከጅምሩ ለመከላከልና ለመግታት በክስተቱ ወቅትም የአደጋውን ጉዳት መጠንና ጥልቀት ለመቀነስ የተለያዩ አካላት የየበኩላቸውን ጥረቶችና ተሳትፎ አድርገዋል፡፡ የመሀል ሜዳ-አለም ከተማ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ለዋና መሥሪያ ቤት ወዲያው ችግሩን በማሳወቅ እርዳታ መጠየቃቸው፤ ቀጥሎም የነበረውን የጥቃት አዝማሚያ ገምግሞ የአካባቢው የጸጥታ ኃይል አደጋውን መቆጣጠር እንደማይችል ግንዛቤ በመውሰድ የአጎራባች ወረዳዎች አስተዳደርን ድጋፍ በመጠየቅና ፈቃደኝነታቸውን በማግኘት ሠራተኞቹን ከአደጋው ለማስጠለል የተወሰደው እርምጃ እና ሠራተኞቹም ይህንን ዕድል በመጠቀም በእጃቸው የነበሩትን የድርጅቱን ተሽከርካሪዎች በመጠቀም እራሳቸውን ከተቃጣባቸው ጥቃት መታደግ መቻላቸው በአደጋው ይደርስ የነበረውን ሰብአዊ ጉዳት በመቀነስ ረገድ ውጤታማ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡

የአጎራባች ወረዳዎች አስተዳደር አካላት የጸጥታ ኃይሉን ጨምሮ በዚህ ክስተት በድርጅቱ ሠራተኞችና ንብረት ላይ ከተደቀነባቸው አደጋ ለመታደግ በወረዳው እንዲጠለሉ በማድረግ ያሳዩት ቅንነት የተሞላበት ወገናዊ አለኝታነት፤ እንዲሁም የአካባቢው ህብረተሰብ ሠራተኞቹን ከማስጠለልም አልፎ ከአካባቢው እስኪወጡ ድረስ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ በተፈጠረው ችግር ምክንያት ሊከሰት የነበረውን ሰብአዊ ጉዳትን በማስቀረት ያደረጉት አበርክቶት የሚደነቅ አኩሪ ተግባር ተደርጎ መወሰድ ያለበት ነው፤ ለዚህ ተምሳሌታዊነት ላለው ተግባራቸው ምስጋና ሊቸራቸው ይገባል፡፡

የድርጅቱ ባለቤትና ዋና ሥራ አስኪያጅም የፕሮጀክቶቹ ባለቤት ለሆነው የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፣ ለክልል፣ ለዞኑና ለወረዳ አስተዳደር አካላት፣ ለፌዴራል የጸጥታ አካላትና ሌሎች ባለድረሻ አካላትን በማሳወቅ አደጋውን ለመቆጣጠር እንዲቻል የድጋፍና ትብብር ጥያቄ በወቅቱ በማቅረብ በትኩረት ክትትል በማድረግ አደጋውን ለመቆጣጠር የሚያስችል እርምጃ እንዲወሰድ ወሳኝ ድርሻ አበርክተዋል፡፡

የኢትዮጵያ የአገር መከላከያ አባላት ወደ ቦታው በመንቀሳቀስ የተፈጠረውን ችግር በመቆጣጠር ከአደጋው የተረፈውን ንብረት ከጥፋት በማስጣል ከጉዳት ለመታደግ ችለዋል፤ በችግሩ ምክንያት ወደ ተለያዩ ሥፍራዎች ሸሽተው ተጠልለው የነበሩትን የድርጅቱ ሠራተኞች ከአካባቢው በሰላም እንዲወጡ አድርገዋል፤ በዚህም ህዝባዊ አለኝታነታቸውን አስመስክረዋል።

ከችግሩ ክስተት በኋላ የፌዴራል መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ባለድርሻ አካላትን ለይቶ በማሳተፍ የጋራ ምክክር በማድረግ ለችግሩ መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉትን በቅደም ተከተል በማስቀመጥ እና ፈጻሚ አካላትን መድቦ ተልዕኮ በመስጠት የሰጠው አመራር ሊወሳ የሚገባ ነው፡፡ በዚህ ሂደት በተለይ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት፣ የትራንስፖርት ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላትን በማስተባበርና ከድርጅቱ ጋር በቅርበት በመፍትሄዎቹ ዙሪያ በመስራት በተግባር ያሳዩት ቁርጠኝነት በአደጋው ተከስተው የነበረው ውስብስብ ተያያዥ ችግሮች ፈር እንዲይዙ አስችሏል፡፡

## 3. Measures Taken to Control the Incident & Stakeholders Role

Different actors have exerted their efforts in order to prevent the attack from the start and reduce the severity of the damage. Project Manager of Mehalmeda-Alemketema had urgently informed the Head Office about the incident and after assessing the tendency of the attack he came to a conclusion that the security force in the area would not control the situation and eventually seek help from the neighboring Woredas administrations to shelter employees who immediately managed to save themselves using the available vehicles. The steps were very significant in preventing the level of severity of the attack on human life.

The administrators and security forces of the neighboring Woredas were praiseworthy in sheltering the employees and properties, while the local community was admirable in providing the necessary support to the sheltered employees that prevented the severity of the attacks. This exemplary deed saved lives and has to be commended.

Owner and General Manager of the Company, has made utmost effort in making urgent follow ups with the client – Ethiopian Roads Authority- and concerned actors such as Regional, Zonal and Woreda administrations, Federal Security forces and others. He was instrumental by submitting timely request to these actors and thus seeking support to control the incident.

Members of the National Defense Force have moved to the area to control the incident and protected the remaining properties. They also provided peaceful evacuation of employees who had been sheltered at different places. With this the Defense Force of Ethiopia proved to be a national pride.

After the incident the leadership demonstrated by the Federal government through special attention paid into matter came with a consultation involving stakeholders to identify possible remedy and assignment of executive bodies for action is mentionable. In this process the concerted effort made by the FDRE Office of the Prime Minister, Ministry of Transport and the Ethiopian Roads Authority along with other concerned bodies was instrumental which has been demonstrated in action in addressing complex issues relating to the incident.

## 4. ክስተቱ ውጤትና እንድምታ

በፕሮጀክቶቹ ላይ ተፈጽሞ ነበረው ጥቃት ሊያስከትል የሚችለው ዙሪያ መለስ አሉታዊ ውጤትና እንድምታ ስፋትና ጥልቀት ያለው መሆኑ ቢታመንም በቀጥታ በተስተዋሉት ላይ ብቻ በመገደብ እንደሚከተለው በአጭሩ ተደሷል፡፡

በንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳት ስንመለከት የተለያየ መጠንና ዓይነት ያላቸው የግንባታ መሳሪያዎች አጠቃላይ አኃዛቸው 87 የሆኑት እክስካቫተሮች፣ የጠጠር መፈጫ (ክሬሸር)፣ ግሬደሮች፣ ዶዘሮች፣ ሮለሮች፣ ሎደሮች፣ ወዘተ እና የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ሙሉ በሙሉ ወድመዋል፤ የተቀሩት ሌሎች ከዚህ አኃዝ ያላነሰ ተመሳሳይ ንብረቶች ላይ ደግሞ የተለያዩ ጉዳቶች ደርሶባቸዋል፤ ግምታቸው ቀላል የማይባል የቅየሳ መሳሪያዎች፣ የቤተ ሙከራ ቁሳቁሶች፣ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች፣ የድርጅቱ ሰነዶች፣ የተሽከርካሪና የግንባታ ማሽነሪ መለዋወጫዎች እና ሌሎች ንብረቶች ተዘርፈዋል፤ የተቀሩትም ከካምፑ ጋር አብረው ጋይተዋል፡፡ ከድርጅቱ ንብረት በተጨማሪም የሠራተኞች የግል መገልገያ ቁሳቁሶችና አልባሳት ጭምርም የዚህ አደጋ ሰለባ ሆነዋል፡፡ ከውድመት የተረፉት የግንባታ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ከአካባቢው ሳይወጡ ከአምስት ወራት ላላነሰ ጊዜ ከአገልግሎት ውጪ ሆነው በአካባቢው አመቺ የጸጥታ ሁኔታ እስኪፈጠር ድረስ እንዲቆዩ አስገድዷል፡፡

ከዚሁ ችግር ጋር ተያይዞ የድርጅቱ ሠራተኞችም ለአካላዊ (ለአብነት አንድ መሃንዲስ ላይ የደረሰ ድብደባ) እና ስነልቦናዊ ጥቃት ተዳርገዋል፤ የሁለቱም የመንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች ሙሉ በሙሉ በመቋረጣቸው የድርጅቱ ሠራተኞች ከሥራ ውጪ በመሆናቸው ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳትም እንዲዳረጉ አስገድዷቸዋል፡፡

የአካባቢውም ህብረተሰብ የፕሮጀክቶቹ ግንባታ በመቋረጡ መንገዶቹ ተጠናቀው የመሰረተ ልማት ችግሮቻቸው የሚፈቱበትን ቀን በጉጉት የሚጠብቁትን ሁሉ ተስፋቸው ላይ የስጋት ደመና በማጥላት ጊዜያዊ የስነልቦና መረበሽን ማስከተሉ አለ የሚባል አይደለም፡፡ ከመንገድ መሰረተ ልማት ጋር ተያይዞ የነበረባቸው ችግርም ዕድሜውን የማርዘም ውጤት ከማስከተሉም በተጨማሪ በፕሮጀክቱ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸው የነበሩት የአካባቢው ዜጎችም ከሥራ ውጪ እንዲሆኑ አስገድዷቸዋል፤ የድርጅቱ ሠራተኞች በአካባቢው በመኖራቸው ለነዋሪው በተዘዋዋሪ ተፈጥሮ የነበረው የሥራ እድልም ስለተቋረጠ በዚህ ረገድም አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳርፍ አያጠራጥርም፡፡

በንብረቶቹ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር ተያይዞ የሚመጡት ሌሎች አሉታዊ ውጤቶች እንዳሉም መዘንጋት የለበትም፤ ለአብነትም የወደሙትን ንብረቶች ለመተካትና የተጎዱትን ለመጠገን የሚያስከትለው ወጪ፣ እንዲሁም አብዛኞቹ የሚተኩት ንብረቶችና ለጥገና መለዋወጫነት የሚያገለግሉት ዕቃዎች ከውጪ በውጭ ምንዛሪ የሚገዙ በመሆናቸው በአገር ደረጃ በዚህ ረገድ ለሌላ የልማት ፕሮጀክት ይውል የነበረን ሀብትና የውጪ ምንዛሪን ጭምር በመሻማት ረገድ የሚያሳድረውን ጫና ማንሳት ይቻላል፤ ከዚህ ሌላም አገልግሎት ሳይሰጡ የቆዩት ንብረቶችም ለቆሙበት ጊዜ በመንግስት ላይ የሚያስከትለው ተጨማሪ ወጪ በተመሳሳይ የሌሎችን የልማት ፕሮጀክቶችን ሀብት በማጓደል መሆኑ፣ በድርጅቱ ላይም ወቅታዊ የገንዘብ ፍሰትን በማዛባት እና በሌሎች በድርጅ ቱ እየተከናወኑ ባሉት ፕሮጀክቶች አፈጻጸምንም በማጓተት በዚህም ለከሳራ ከመዳረጉም በላይ ድርጅቱ ለዘመናት የገነባውን የመልካም የአፈጻጸም ሥም ላይም የስጋት ደመናን በማጥላት ጭምር አሉታዊ ተጽዕኖውን አሳርፏል፡፡

## 4. Impact of the Incident

Although it is understandable that the negative impact of the incident could be sever by far some of the direct impacts of the incident are highlighted as follows:

The damage caused on properties carries diverse type and size of construction machineries totaling 87 Excavators, Gravel Production Equipment, Graders, Dozers, Rollers etc. and other vehicles were also totally destroyed. Other remaining properties which are not less than this number were damaged. Significant number of survey equipment, laboratory materials, office supplies, documents, vehicle and machinery spare parts and other properties were vandalized while the remaining were set on fire with the camp. Other than the company, properties of the employees and clothes were also damaged. Until security is ensured and evacuation takes place equipment and vehicles which were saved from the attack stood idly in the area for about five months. In related to this, employees of the company sustained physical and psychological damages including an Engineer who was beaten up. Due to the incident employees were forced to stay out of work causing them social and economic damages.

It is undeniable that the local community has sustained temporary psychological distress due to that their expectations have been shaded on the project completion so as to solve the infrastructure problem. The incident, other than adding more time to the problem relating to lack of infrastructure it also denied the job opportunity created for the local community members. There is no doubt that the indirect employment opportunities for the residents due to the presence of the employees in the area will also be negatively affected in this regard.

The persisting impacts relating to properties damage should be recognized considering the replacement and maintenance costs. While most of the equipment to be replaced and spare parts required for maintenance of damaged properties should be imported will cost the country's hard currency ultimately affecting the resource that should be investment on other development projects. The machineries idle time will also bring additional cost on the government, while causing temporary interruption on the financial flow of the company by further delaying other ongoing projects. Despite this sustaining loss on the company

ከሁሉም ለየት ያለው የክስተቱ ውጤት የመሀል ሜዳ-አዲስ ከተማ የመንገድ ፕሮጀክት ውሉ ሙሉ በሙሉ ተቋርጦ የፕሮጀክቱ ባለቤት በሆነው የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በራሱ የውስጥ አቅም ለማጠናቀቅ እንዲወሰን ያስገደደበት ሁኔታ መፈጠሩ ነው፡፡ እዚህ ላይ ባለሥልጣኑ የፕሮጀክቱን ቀሪ ሥራ በራሱ በማጠናቀቅ ለታለመለት አገልግሎት እንዲበቃ በወሰደው እርምጃ ላይ ድርጅታችን ቅሬታ ኖሮት እንዳልሆነ በቅድሚያ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

ይህ ፕሮጀክት በተፈጠረው አደጋ ምክንያት ውሉ ሲቋረጥ የመንገድ ግንባታው ከ97 ከመቶ በላይ ተጠናቅቆ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ በደረሰበት ወቅት ነበር፤ እዚህ ደረጃ ለማድረስ በፕሮጀክቱ የግንባታ ሂደት ውስጥ የአካባቢው መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ አስቸጋሪነት፣ የሥነ ምድራዊ ባህሪይ ለግንባታ አመቺ ያለመሆን እና በመንገዱ ዲዛይን ላይ ባጋጠመው ክፍተት ሳቢያ ድርጅቱ ብዙ ውጣ ውረድንና ፈታኝ ሁኔታዎችን ለማለፍ የተገደደበት ነበር፡፡ ይህንን እንቅፋት ለማለፍ በራሱ ኪሳራ ከውጭ አገርና ከአገር ውስጥ በዘርፉ የተሻለ ልምድና ዕውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች በማሳተፍ የኮንስትራክሽን ሙያ የሚጠይቀውን ሥነምግባር መርህን በመከተል የመፍትሄ ምክረ ሀሳብ ለፕሮጀክቱ ባለቤት ያቀረበበትና በዚህም የህዝብን ሀብት ከብክነት በተጨባጭ ለማዳን የተቻለበትን ጥረት አድርጓል፡፡ ሌላኛው የፕሮጀክቱ ግንባታ አስቸጋሪነት ማሳያው አምስት ተቆጣጣሪ መኃንዲሶች የተቀያየሩበት ፕሮጀክት መሆኑ ልብ ይለዋል፡፡

ድርጅታችን ይህንን ፕሮጀክት እዚህ ደረጃ ለማድረስ ፈታኝ ሁኔታዎችን ለማለፍ አያሌ ዋጋ የከፈለበት ሆኖ ሳለ በተፈጠረው ችግር ምክንያት ፕሮጀክቱን ለምርቃት አብቅቶ የልፋቱን ውጤት ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር ለማየት ባለመታደሉ እስካሁን ገንብቶ ለአገልግሎት ካበቃቸው ፕሮጀክቶች አንጻር በደርጅቱ ታላቅ ሀዘንና ቁጭትን መፍጠሩ ሌላኛው የችግሩ ጠባሳ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

ለማጠቃለል ከላይ የተጠቀሱት የዚህን ክስተት ውጤትና እንድምታውን ለአብነት ለማመላከት እንጂ ሁሉንም ያካተተ እንዳልሆነ ግንዛቤ መያዝ ይኖርበታል፤ በፕሮጀክቶቹ ላይ የደረሰው አደጋ አሉታዊ ውጤትና እንድምታው ከድርጅቱ ንብረት ውድመት የድርጅቱ አመራር የአደጋውን ሁኔታ በተረጋጋና አስተዋይነት በተሞላበት አኳኋን የመራበት በሳል አካሄድ ነው፤ ያልተጠበቁ ችግሮች የመፈጠር ዕድል ያለ እንደመሆኑ መጠን በተፈጠረው ችግር ተደናግጦ በወቅቱ ተገቢውን የመፍትሄ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ስለተፈጠረው ችግር ብቻ በመጨነቅ ጊዜ ማባከን በብዙ የአደጋ ገጠመኞች ይስተዋላል፡፡ ከዚህ አንጻር የድርጅቱ አመራር ችግሩ እንደተከሰተ ተረጋግቶ ለሚመለከታቸው አካላት በማሳወቅ ድጋፍ ከመጠየቅ ጎን ለጎን በራሱ አመራርና ከውጪም ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጥን ኃይል በማሳተፍ በቀጣይ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች አንድ በአንድ በመለየት ወደ ተጨባጭ የመፍትሄ መስጠት መግባት መቻሉ በጥንካሬነት ሊወሰድ የሚገባ ነው፡፡

በሌላ በኩል ይህ ገጠመኝ ድርጅቱ ዘላቂ የሆነ የአደጋ ጊዜ የሥራ አመራር ሥርዓትን የበለጠ የማጠናከር አስፈላጊነትን ከምን ጊዜውም በመልካምነቱ ሊወሰድ የሚገባ ነው፡፡ ሆኖም ተመሳሳይ ትላልቅ የህዝብና የመንግሥት ሀብት በሚፈስባቸው ፕሮጀክቶች አካባቢ ያለውን የጸጥታ ስጋት በየወቅቱ በሚደረግ ዳሰሳ እየተለየ እንዳይከሰት ቀድሞ የመግታት፣ ከተፈጠረም ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችል አፋጣኝ እርምጃ የሚወሰድበትን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊም ብቻ ሳይሆን ተገቢ መሆኑን ከዚህ ልምድ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በመንግሥትም ይሁን በግል ባለሀብቶች የሚሰሩት የልማት ፕሮጀክቶች የህዝቡና የሀገር ሀብት መሆኑን

it has also negatively affected the company's project implementation reputation built for years. The exceptional outcome of this incident is the situation where the Ethiopian Roads Authority has been forced to complete the fully terminated Mehalmeda-Alemketema road project by its own force. At this point we would like to stress that our company has no complain on the Authority's move to complete the project.

When this project comes to termination due to the incident it was on its final phase completed more than 97 percent. In order to reach to this phase the company had to come through various challenges subjected to geographical and geological conditions of the area as well as the gap relating to design issues. To overcome these hurdles the company made its utmost efforts to avoid wastage on public resources by engaging skilled experts from local and abroad at its own cost to meet the ethics and principles required by the profession.

The reshuffling of five resident engineers also shows the difficult nature of the project. Given the immense challenges the company had pass through unlike any other projects it deeply regrets for not able to see its completion and inauguration along with the local community and this remains to be the other side of the impact left by the incident. In conclusion, the aforementioned negative effects of the incident were not the only ones but it is the highlights which do not include the entire impact. The damage sustained on the project is beyond the distraction of the company properties; it has left negative impact on the employees, local community and at national level development plans.

## 5. What are the Lessons Learned?

Every good and bad incident we encounter will always give us certain message and once we associate its message with the events of the incident they will be identified as either strength or weakness.

In this regard the flow of information that started from the moment the incident has occurred to the Head Office was swift and timely which helped to share with concerned government bodies for a quick action. Whether this had bear fruit or not however, it is vital to agree on the importance of sharing timely and correct information for every problem encountered. Basically one can assume that the ultimate purpose of the

በህብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ የመፍጠርና የባለቤትነት ስሜትን የማስረጽ ሥራም በበቂ ትኩረት መሰራት እንዳለበት ክስተቱ ለሁሉም ትምህርት ሰጥቶ አልፏል፡፡ ባሻገር በሠራተኛው፣ በአካባቢው ህብረተሰብ ብሎም በአገር ደረጃ ባሉት የልማት እቅዶች ላይ ማካካሻ የሌለው ቀላል የማይባል አገራዊ ጉዳት እንዳደረሰ መገመት አይከብድም፡፡

## 5. ከክስተቱ ምን መማር ይቻላል?

በየወቅቱ ከሚከሰቱት በጎም ሆኑ መጥፎ አዳዲስ ክስተቶች ልብ ብለን መፈተሽ ከተቻለ ትተውልን የሚያልፉት ትምህርታዊ መልዕክት ይኖራል፤ መልዕክቶቹ ከክስተቶቹ ሂደት ጋር ተያይዘው የተስተዋሉ በጥንካሬ አሊያም በድክመት የሚፈረጁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በዚህ ረገድ ከአደጋው መከሰቻ ሰዓት አንስቶ ከክስተቱ ስፍራ እስከ ዋናው የድርጅቱ መሥሪያ ቤት የነበረው የመረጃ ፍሰት ፈጣንና ወቅታዊ በመሆኑ በፍጥነት ለመግታት እንዲቻል ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት ዘንድ በወቅቱ እንዲደርስ አግዟል፡፡ ይኸ መሆኑ ምን ውጤት አምጥቷል የሚል ጥያቄ መኖሩ ሌላ ጉዳይ ሆኖ ለማንኛውም ችግር መፍትሄ ለመሻት እንዲቻል ቅድሚያ ለወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ፍሰት ትኩረት መስጠት አስፈላጊነት ላይ መግባባት ያስፈልጋል፤ በመሰረታዊነት የአደጋው ጠንሳሾች ምናልባትም ግባቸው ንብረቱን ማውደም ብቻ ላይሆን እንደሚችል በማንም ውስጥ ሊፈጠር የሚችል ግምት ነው፤ የመረጃው ፍሰት ላይ ዝንፈት ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮ ለተዛቡ መረጃዎች መፈብረክና መስፋፋት ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥር ችግሩ ሌላ ያልተፈለገ ቅርጽ እንዲይዝ በማድረግ የጥፋት አድማሱን እንዲያሰፋ የማድረግ ዕድሉ ዜሮ ነው ማለት አይቻልም፤ ከዚህ አንጻር የመረጃ ቅብብሎሹና ፍሰቱ ውጤታማ ነበር ለማለት ያስደፍራል፡፡

ሌላው ቁልፍ ጉዳይ የድርጅቱ አመራር የአደጋውን ሁኔታ በተረጋጋና አስተዋይነት በተሞላበት አኳኋን የመራበት በሳል አካሄድ ነው፤ ያልተጠበቁ ችግሮች የመፈጠር ዕድል ያለ እንደመሆኑ መጠን በተፈጠረው ችግር ተደናግጦ በወቅቱ ተገቢውን የመፍትሄ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ስለተፈጠረው ችግር ብቻ በመጨነቅ ጊዜ ማባከን በብዙ የአደጋ ገጠመኞች ይስተዋላል፡፡ ከዚህ አንጻር የድርጅቱ አመራር ችግሩ እንደተከሰተ ተረጋግቶ ለሚመለከታቸው አካላት በማሳወቅ ድጋፍ ከመጠየቅ ጎን ለጎን በራሱ አመራርና ከውጪም ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጥን ኃይል በማሳተፍ በቀጣይ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች አንድ በአንድ በመለየት ወደ ተጨባጭ የመፍትሄ መስጠት መግባት መቻሉ በጥንካሬነት ሊወሰድ የሚገባ ነው፡፡

በሌላ በኩል ይህ ገጠመኝ ድርጅቱ ዘላቂ የሆነ የአደጋ ጊዜ የሥራ አመራር ሥርዓትን የበለጠ የማጠናከር አስፈላጊነትን ከምን ጊዜውም በላይ ጎልቶ እንዲወጣ ረድቶታል፡፡ በተለይ በአደጋው ምክንያት የተፈጠሩትን ተግባራት እና መደበኛውን ሥራ አቀናጅቶ ለመምራት የሚያስችል ጠንካራ አቅም መገንባትና ሥርዓት መፍጠር በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የአደጋውን ተፅዕኖ ለመቀነስ በድርጅቱ አመራር የተወሰዱት እርምጃዎችና የተፈጸሙት ተግባራት በጥንካሬነት መወሰዱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአደጋ ጊዜ ሥራ አመራር ሥርዓትን በተለየ ትኩረት ማጠናከርን ለቀጣይ የቤት ሥራው እንዲሆን ክስተቱ ለድርጅቱ ምቹ ተመክሮ ፈጥሮ አልፏል፡፡

## 6.ማጠቃለያ

መጥፎ ክስተትን ማንም የሚፈልገው ባይሆንም በተፈጥሮም ይሁን በሰው ሰራሽ ምክንያት መከሰቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሚያስከትለው

perpetrators might not only be destroying the flow it could have created conducive environment properties. If there was incorrect information for misinformation eventually leading to another level of distraction. For that reason there was an effective flow of information in this particular case. The other key commendable issue was the wise handling of the situation followed by management of the company. Even if there is an assumption that unprecedented incidents could happen at any time in this case had there not been careful mitigation measures were taken there could be more damages. In this regard, it should be emphasized that the management of the organization was able to calm down and inform the concerned parties about the problem and seek the support of its own leadership and external professional support.

On the other hand the incident indicated the need to strengthen sustainable disaster management of the company. Especially, it becomes very essential to build strong capacity to lead the regular company operation even at the time of disaster. Besides the measures taken by the management as a strong side in order to minimize the impact of the incident the company gained lesson to build strong disaster management system. After the incident had occurred the direction taken by the government to seek solutions in collaboration with concerned bodies has been instrumental to enhance joint efforts.

In order to craft preventive measures the security situations around other similar public projects should be reviewed ahead of time and if occurred, this experience shows that urgent mitigation system needs to be installed to reduce its severity. The incident was also an indication that there is a need to enhance public awareness toward projects undertaken by government and private investors as they are properties of the nation and the public.

## 6. Conclusion

Bad incidents are inevitable either natural or human-made. This incident shows that the negative impacts will not only be limited to an individual or an entity. Destruction of properties would affect the nation's resource. A resource reduced from a nation would one way or another affect other citizens. No one would benefit from destruction. In a nation's overall development endeavor it is very clear that private investors have indispensable role. Through the wealth generated

አሉታዊ ጉዳት ውጤት በአንድ አካል ወይም ግለሰብ ላይ ብቻ የሚገደብ እንዳልሆነ ከዚህ ክስተት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተፈጠረ ሀብት ሲወድም ከአገር ሀብት ላይ ይቀንሳል እንጂ አይጨምርም። ከአገር ላይ የተቀነሰው ሀብት በአንድም ሆነ በሌላ ዜጎችን መጉዳቱ እንደማይቀር መታሰብ ይኖርበታል፡፡ ካለው ነገር እንጂ ከሌለ ወይም ከወደመ ነገር ማንም ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

በአንድ አገር ሁለንተናዊ ልማትና ዕድገት ለማረጋገጥ በሚደረግ ጥረት ውስጥ የግል ባለሀብቶች የማይተካ ሚና እንዳላቸው የማይካድ ሀቅ ነው፡፡ ያፈሩትን ጥሪት፣ ያካበቱትን ልምድና እውቀት በማቀናጀት የልማት ፕሮጀክቶችን በራሳቸው አቅደው በመተግበርም ሆነ የመንግሥትን የልማት ዕቅድ ፕሮጀክቶችን በማሳካት ሂደት በቀጥታ በመሳተፍ የአገር ልማትን እውን በማድረግ እና በዚህ ሂደት ውስጥም ለዜጎች የሥራ ዕድልን በመፍጠር፣ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ማሳኪያ ለሚያስፈልግ ሀብት በታክስ መልክ ምንጭ በመሆን እና በሌሎች መስኮች በአንድ አገር ግንባታና ዕድገት ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ እጅጉን የጎላ ነው፡፡ በሥራ ላይ የሚገጥማቸው ሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሯዊ አደጋም የሚያስከተለው ጉዳትም በእነዚህ ሁሉ በሚኖራቸው አዎንታዊ አስተዋጽኦዎቻቸው ላይ የሚያርፍ እንደመሆኑ መጠን የሚያስከትለው ጉዳትም እንደዚያው የሰፋ ይሆናል፡፡

በዚህ ጽሁፍም ከላይ ለመዳሰስ እንደተሞከረው በመንገድ ፕሮጀክቶቹ ንብረቶች ላይ በተፈፀመው ጥቃት የወደመው ንብረት ባለቤትነቱ በአንድ ድርጅት ሥም የሚጠራ ይሁን እንጂ በተጨባጭ ግን የህዝቡ ንብረት እንደሆነ ጉዳቱ ከአካባቢው ህብረተሰብ ጀምሮ እስከ አገር አቀፍ ደረጃ ድረስ ካስከተለው አሉታዊ ውጤት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የአንድ ባለሀብት ንብረት ለባለቤትነት ስያሜ ሲባል በሥሙ የሚጠራ ቢሆንም፣ በተጨባጭ ግን የህዝቡ የጋራ ሀብት እንደሆነ ከአስተሳሰብ ጀምሮ ሁሉም ዜጋ እራስን በዚህ ቅኝት አንጾ በተግባርም መሰል ጥፋቶች ዳግም እንዳይደርሱ ይህንኑ መፈጸም የዜግነት ግዴታና ኃላፊነት እንደሆነ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል፡፡ ይህንን አስተሳሰብ በህብረተሰቡ ከማስረጽ ጎን ለጎን  በአገር ሀብትና ንብረት ላይ ጥቃት የሚፈጽም ማንኛውንም አካል የሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ከህዝቡ ጋር በመቀናጀት ተከታትሎ ለህግ በማቅረብ የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ ቀጣይ ተመሳሳይ ችግር ዳግም እንዳይፈጠር  አስተማሪ መልዕክት ማስተላለፍም ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ በመሆኑም ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍልም ሆነ እያንዳንዱ ዜጋ ይህንን እውነታ ተረድቶ የጥፋት አስተሳሰቦችንና ተግባራትን ተመሳሳይ አውዳሚ ችግር ዳግም እንዳይከሰት በማወገዝ እና በመከላከል የአከባቢውን ብሎም የአገርን ሰላም በጋራ የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለበት ሊገነዘብ ይገባል፡፡

ድርጅታችንን ያጋጠመው ያልተጠበቀ ጥቃት አሳዛኝ ቢሆንም፣ በዚህ መጥፎ ኩነት ተደናቅፎ ከጉዞው ለሴኮንድም ሳይዘናጋ እና ለችግሩ ምክንያት ከመፈለግ ይልቅ ፈተናውን ብልሀትና ብስለት በተሞላበት በመጋፈጥ ተቋቁሞ ለመሻገር የሚያስችል ቁመና መልሶ ለመገንባት ውጤታማ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል፤ በቀጣይም ይህንኑ አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ ለዚህም ሲባል ምን ጊዜም ከበጎ ገጠመኞቹ ብቻ ሳይሆን ከተግዳሮቶቹም ጭምር ትምህርት ቀስሞ ተጨማሪ አቅም ለመፍጠር በግብዓትነት የመጠቀም ሥልት እንደ አቅጣጫ መከተል ይጠበቅበታል፡፡ ለዚህም ድርጅቱ ከገጠመው ጉዳት አገግሞ ወደ ነበረበት የሥራ ሞራልና አቅም በመመለስ የተጀመሩትን ፕሮጀክቶች በተገባበት ውል መሠረት መፈፀም እንዲችል የድርጅቱ አመራርና ሠራተኞች ከዚህ ቀደም የነበራቸውን የሥራ ትጋትና ቁርጠኝነት ከማንኛውም ጊዜ በተለየ ሁኔታ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ድርጅቱ ሙሉ እምነት አለው፡፡

in tandem with the experience and skill whether they invest by themselves or directly engage incidents not to happen again. Besides promoting this mindset of ownership into the public the concerned government body in collaboration with the public has to take legal measures against those perpetrators and ensure rule of law which will be a lesson such crimes not to repeat for the future.

Therefore, every public sect as well as citizen should understand this fact and uphold its responsibility of creating awareness and taking preventive measures against distractions not to happen again. The company never bows for a second for this shockingly unprecedented incident from pursuing from its journey rather went on seeking wise way out and it has been building effective resilience and will continue to do so. For this reason, the company has to follow a direction by which it takes inputs from the good and bad incidents more than any time before. Accordingly, the company is fully confident that its management and employees will regain the past moral and capacity by far so as to properly accomplish the projects it has entered contact with.

with government's development projects and hence create employment opportunities, and they have immense contribution by paying tax commitment for social and economic development of the nation. Such natural or human made incidents the investors encounter could have wider impact on their positive contributions.

As highlighted above although the damaged properties at the two road projects are registered under one company they were actually properties of the public, and its negative impact was ultimately caused at local community and national level.

Although the property of an investor holds its name every citizen should be in a position where these investments are actually be perceived as the peoples' own resource and hence exercise their duties and responsibilities in preventing similar

*“መሪዎች በደንብ ያልዳበረ የፍርሃት ስሜት ያላቸው እና ከእነሱ በተቃራኒ የሚያጋጥሙአቸው ነገሮች የማያሳስባቸው ባለራዕይ ናቸው ፡፡” - አር. ጃርቪክ*

***“Leaders are visionaries with a poorly developed sense of fear and no concept of the odds against them.” - R. Jarvik***

# ዓመታዊ የግንባታ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም
# Annual Performance of Construction Projects



**Eng. Henok Mebrate**
Director of Road & Water Construction
**ኢንጂነር ሄኖክ መብራቴ**
የመንገድና ውሀ ግንባታ ዳይሬክተር

ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኃ. የተ. የግል ኩባንያ በኢትዮጵያ ካሉ ስመጥር የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች አንዱ ነው፡፡ ኩባንያው ከተመሰረተ አንስቶ ጥራታቸውን የጠበቁ የመንገድ ግንባታዎችን በኮንትራት ጊዜውና እሊፍ ስልም አስቀድሞም በተመጣጣኝ ወጪ ማስረከብ የኩባንያው መገለጫ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በዚህም የኮንስትራክሽኑን ዘርፍ ባለድርሻ አካላትን ፍላጎት በማሟላት መልካም ስም ገንብቷል፡፡

በአሁኑ ወቅት ኩባንያው በሶስት ዋና ዋና የግንባታ ዘርፎች የተሰማራ ሲሆን እነሱም፤ የመንገድ፣ የህንጻ እና የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ዘርፎች ናቸው፡፡ ከዚህ በታች በዝርዝር እንደተቀመጠው በ2012 ዓ.ም ኩባንያው አምስት የአስፋልት መንገድ፣ ሁለት የህንጻ ግንባታ እና አንድ የመስኖ ፕሮጀክቶችን ሲገነባ ቆይቷል፡፡ ከ2012 በጀት ዓመት እስከ አሁን ጠቅላላ ፕሮጀክቶች ለኩባንያው የሥራ አፈፃፀም ያላቸው አስተዋፅኦ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

Gemshu Beyene Construction PLC is one of the prominent construction company in Ethiopia. And it attains a remarkable reputation due its capability to fulfil expectations of road construction stakeholder's. Since its establishment, delivery of quality roads within or ahead of contract time at reasonable cost margin has been a custom of our company.

Currently the company is involved in three major Sectors of the Construction Industry; namely Road, Building and Water Works Construction sectors. In 2012 EFY (Ethiopian Fiscal Year), our company has been constructing five Asphalt road projects, two Building projects and one Irrigation project as described below.





2012 EFY Project Performance Evaluation Management

| ዘርፍ | የፕሮጀክት ስም | አይነት | የመጀመሪያ የኮንትራት መጠን (በብር) | ቦታ | አሁን የደረሰበት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| መንገድ | መሃልሜዳ-ዓለምከተማ አስፓልት | አስፋልት ኮንክሪት | 723,955,237.75 | ሰሜን ሸዋ (አማራ) | ለደንበኛው የተላለፈ |
| | አምቦ ከተማ የውስጥ ለውስጥ አስፋልት | አስፋልት ኮንክሪት | 403,620,756.00 | ምዕራብ ሸዋ (አሮሚያ) | ዋና ዋና የግንባታ ስራዎች የተከናወኑበት ነው |
| | ዓለምከተማ-ደጎሎ አስፓልት | አስፋልት ኮንክሪት | 1,012,857,976.40 | ሰሜን ሸዋ (አማራ) | ዋና ዋና ስራዎች የተጠናቀቁበት |
| | ጊንጪ-ሽኩጤ አስፓልት | አስፋልት ኮንክሪት | 710,338,282.50 | ምዕራብ ሸዋ (አሮሚያ) | ዋና ዋና የግንባታ ስራዎች የተከናወኑበት ነው |
| | ሽኩጤ-ጨሉጤ አስፓልት መንገድ | አስፋልት ኮንክሪት | 1,001,728,671.10 | ምዕራብ ሸዋ (አሮሚያ) | ዋና ዋና የግንባታ ስራዎች እየተከናወኑበት ነው |
| | ጠቅላላ | | 3,852,500,923.75 | | |
| ህንጻ ግንባታ | አርሲ ዩኒቨርሲቲ | | 334,915,246.69 | አርሲ (አሮሚያ) | በወሳኝ ደረጃ የተጠናቀቀ |
| | ኢሊሊ ሆቴል ባለዘርፈ ብዙ | | 28,362,900.35 | ፊንፊኔ | በወሳኙ የተጠናቀቀ |
| | ጠቅላላ | | 363,278,147.04 | | |
| የውሃ ስራዎች | ሞጆ መካከለኛ ደረጃ የመስኖ ውኃ ግድብ | | 342,589,694.90 | ምሥራቅ ሀረርጌ (አሮሚያ) | ዋና ዋና ስራዎች በመከናወን ላይ ነው |
| **ጠቅላላ ዋጋ (በብር)** | | | **4,558,368,765.69** | | |

| Sector | Project Name | Type | Original Contract) (Works)Amount(Birr) | Location | Current Status |
|---|---|---|---|---|---|
| Road | Mehalmeda~ Alemketema | double Surface Treatment | 723,955,237.75 | N.Showa (Amhara) | Transferred to client |
| | Ambo Town | Asphalt Concrete | 403,620,756.00 | W.Showa (Oromia) | Major works are Under construction |
| | Alemketema-Dogolo | Asphalt Concrete | 1,012,857,976.40 | | Major works are completed |
| | Ginchi-Shikute | Asphalt Concrete | 710,338,282.50 | W.Showa (Oromia) | Major works are completed |
| | Shikute-Chulute | Asphalt Concrete | 1,001,728,671.10 | W.Showa (Oromia) | Major works are Under construction |
| | Total | | 3,852,500,923.75 | | |
| Building | Arsi University | | 334,915,246.69 | Arsi(Oromia) | Substantially Completed |
| | Elilly Hotel | | 28,362,900.35 | Finfinne | Substantially Completed |
| | Total | | 363,278,147.04 | | |
| Water Works | Mojo Medium Scale Irrigation | | 342,589,694.90 | East Hararge (Oromia) | Major works are Under construction |
| **Grand Total Amount(Birr)** | | | **4,558,368,765.69** | | |

## ሀ. የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች

ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን በመንገድ ግንባታ ዘርፍ ሰፊ ልምድ እንደማዳበሩ በተጠናቀቀው በጀት ዓመትም የሚከተሉትን አምስት የመንገድ ፕሮጀክቶችን ሲገነባ ቆይቷል፡፡

### 1. መሃልሜዳ (ኪሜ-72) - ዓለምከተማ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክት

መሃልሜዳ (ኪሜ72)-ዓለምከተማ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በአማራ ብሔራዊ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ይገኛል፡፡ ፕሮጀክቱ በዋነኛነት በዲኤስ-4 ጂኦሜትሪክ ዲዛይን ደረጃ አዲስ መንገድ መገንባት ነው፡፡ ይህ Double Bituminous Surfaced Treatment (DBST) የአስፋልት መንገድ ፕሮጀክት 48 ኪሜ ርዝመት አለው:: ይህ መንገድ በተራራማ፣ ተንሸራታች እና ዳገታማ መልክአ ምድር ውስጥ የሚገነባ ሲሆን ከፍተኛ የቁፋሮዎች እንዲሁም በዛ ያሉ ትላልቅና አነስተኛ የግንብ ስራዎችን ያካተተ ነው፡፡

በመልክአ ምድሩና ስነ-ምድራዊ ባህሪያት አስቸጋሪነት የተነሳ በፕሮጀክቱ ግንባታ ሂደት ውስጥ ያልተጠበቁ የመሬት መንሸራተቶች በማጋጠማቸው ተደጋጋሚ የዲዛይን ማሻሻያ እንዲደረግ አስገድዷል፡፡ ይህ ሁኔታ ከ3, 693, 000 ሜ. ኪዩብ በላይ ሰፊ ቁፋሮ እና 189 ሺ ሜ. ኪዩብ የግንብ ግንባታ ተግባርን አስከትሏል:: እነዚህን ስራዎች ለማከናወን ከሚያስፈልጉ የጥሬ እቃዎች አቅርቦትና አስተዳደር አንጻር ሥራውን ለማከናወን ያጋጠሙትን ፈታኝ ሁኔታዎች መገመት ይቻላል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች የተለዩ የስራ ስልቶች እና እቅድ አዘገጃጀት በማስፈለጋቸው የግንባታ ሂደቱን ፈታኝ እንዲሆን አድርገውታል፡፡

የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ አስቀድሞ በመረዳት በዲዛይን ሥራ ወቅት ከግንዛቤ ማስገባት ያለመቻል በፕሮጀክቱ የግንባታ ሂደት ካጋጠሙት ሌሎች ተግዳሮቶች መካከል ዋነኛው ነበር፡፡ ይህን መሰል ሁኔታዎችን ለማስተካከል በፕሮጀክትና በዋና መስሪያ ቤት ደረጃ የደብዳቤዎች ልውውጥ እና የሶስትዮሽ ምክክሮችን በማካሔድ እርምጃ መውሰድ ተችሏል፡፡ የተሰጠውን የዲዛይን ማሻሻያ በሚገባ በመመርመር ኩባንያው የዲዛይን ችግሮችን በመለየት ተግባራዊ መፍትሔዎችን ጠቁሟል፡፡

ከዚህም የተነሳ በኩባንያውና በሌሎች ባለድርሻ አካላት የጋራ ጥረት ከዲዛይን ጋር የተገናኙ ችግሮች ሊቀረፉ ችለዋል፡፡ ዋና ዋና የፕሮጀክቱ ስራዎችም በ2011 በጀት ዓመት ተጠናቋል፡፡ የፍሳሽ ማስወገጃና የመሳሰሉትን ሌሎች ቀሪ ጥቃቅን ሥራዎች ከታህሳስ 2012 በጀት ዓመት በፊት አጠናቆ በፕሮጀክቱ ሥፍራ የነበሩትን ዋና ዋና መሳሪያዎችን በማንሳት ወደ ጊንጪ-ሽኩቴ እና ሽኩቴ-ጨሉጤ መንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች ለማዘዋወር ታቅዶ ሲሰራ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ ወሳኝ ተግባራትን ፈጽመን እነዚህን እቅዶች ለማሳካት በሙሉ አቅማችን እየተረባረብን ባለንበት ወቅት ላይ በአካባቢው ያልተጠበቀ የጸጥታ ችግር በመከሰቱ በቀን 16 ጥቅምት 2012 በፕሮጅክቱ ንብረቶች ላይ ቃጠሎ፣ ውድመትና ስርቆት በመፈጸሙ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል፡፡ ይህን ጉዳት ተከትሎ ከጥቃቱ የተረፉትን ንብረቶች በፍጥነት ወደ ሌላ ፕሮጀክት እንዲዛወሩ ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ሆኖም ግን በተለያዩ ምክንያቶች መሳሪያዎቹንና

## A. ROAD CONSTRUCTION PROJECTS

Gemshu Beyene Construction PLC has acquired ample experience in the road construction sector. And, during this fiscal year, the company has been constructing the following five road projects under design bid and build contract agreements.

### 1. Mehalmeda (Km72)–Alemketema Asphalt Road Project

Mehalmeda (Km72)-Alemketema Road Project is located in the North Showa Zone of Amhara Regional National state. The project main work is the construction of new road with DS-4 geometric design standard. And it is Double Bituminous Surfaced Treatment (DBST) Asphalt road that covers 48 km length. This road traverse mainly through mountainous sections, some rolling and very steep escarpment terrain where heavy excavation, major and minor structure work dominantly exists.

In due course of time, the topographic and geo-technique character of the project location resulted unforeseen catastrophic landslides and necessitates frequent design revisions. These situation resulted excessive excavation work volume that exceeds 3,693,000 m3, and masonry work volume that exceeds 189,000 m3. While executing these activities, it can be imagined how it had been difficult to supply and manage resources required for the work. And these situations imposes construction difficulties due the need of special work methodologies and proper planning.

Failure to comprehend actual site scenario with that of design aspects had been the major challenge among a number of challenges that had been managed throughout the project life time. To ease such scenarios, proactive measures at project as well as at head quarter level had been made frequently through formal correspondences, and tripartite meetings. Indeed, with due scrutiny of proposed designs, the company had played indispensable roll in identifying design shortcomings and proposing practical solutions.

With due efforts of our company and other stakeholders, design related issues had been resolved. And major works of the project had been substantially completed last year (in 2011 EFY). Whereas, minor remaining works like side drainage activities and ancillary works were scheduled to be

ሌሎች ንብረቶችን የማዘዋወሩ ተግባር ረጅም ጊዜ በመዘግየቱ ሌሎች ፕሮጀክቶች ላይ ከፍተኛ ጫና ተፈጥሯል፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታ ክስተቱ በኩባንያው ሃብትና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ በጠቅላላ የደርጅቱ ስራ አፈፃፀም ላይ ጫና አሳድሯል፡፡

*"ጥንካሬህንና ባህሪይህን ለሚገነባ እያንዳዱን*
*አዳዲስ ፈተና አመስጋኝ ሁን፡፡"*
*ምንጭ- ያልታወቀ*

***"Be thankful for each new challenge, because it will build your strength and character."***
***Anonymous***

accomplished in 2012 EFY before end of December 2019. Moreover, upon completion of this project, it was planned to demobilize resources from this project and deploy on Ginchi-Shikute and/or Shikute- Chulute road projects.

While we were working to attain this scheduled, and executed significant work, unexpected riot or violence had occurred and caused major damages (burning, breaking and looting) to equipment and properties of the project on October 27, 2019. Following this incidence, immediate transfer of equipment, which were not damaged, to other project had been practically impossible. Whereupon a considerable time had elapsed, our plan had been obliterated and other projects progress had been significantly affected until we transfer the resources to other projects. Unfortunately, this event has caused substantial damage on the company resources and affects its overall performance.



**Partial Picture of Mehal Meda AlemKetema Road**

## 2. ዓለምከተማ - ደጎሎ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክት

የዚህ ፕሮጀክት መነሻ ከአዲስ አበባ በ180 ኪሜ ርቀት በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ይገኛል፡፡ ይህ መንገድ ከአዲስ አበባ-ጎንደር ካለው አውራ መንገድ ከሙካ ጡሪ ላይ ታጥፎ በሙከ ጡሪ-ዓለምከተማ-ደሴ መንገድ መሃል የሚሠራ ሲሆን መነሻው ዓለም ሆኖ ማብቂያው ደጎሎ ከተማ ነው:: የፕሮጀክቱ ዋነኛ ስራ 85 ኪሜ የጠጠር መንገድ ወደ አስፋልት ኮንክሪት መንገድ በዲኤስ4 በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ዲኤስ4 ዲዛይን ደረጃ መሰረት ወደ ኮነክሪት አስፓልት መንገድ ደረጃ የማሳደግ ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት ከፍተኛ የተራራማ ስፍራዎች የቁፋሮ ሥራና ከፍተኛ የሙሌት ስራዎችን የሚያካትት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ዋና ዋና የግንባታ ሥራዎች የሆኑት የድጋፍ ግንቦች፣ በወንጪት ወንዝ ላይ የሚደረግ ከፍተኛ የድልድይ ግንባታ እና በርካታ የፍሳሽ ማቋረጫ ግንቦች ሥራን ያካተተ ነው፡፡

## 2. Alemketema-Dogolo Aspahlt Road Project

This project is located 180 km away from Addis Ababa in Amhara National Regional State in North-East part of Ethiopia. It starts at Almketema town on Muketuri-Alemketema-Dessie road, after turning to the right of Addis-Gondar Arterial road at muketuri town. The project major work is upgrading of existing 85km gravel road to Asphalt Concrete road in line with DS4 ERA road design standard. The Project work comprises heavy excavation along mountains and escarpments sections while high fill embankment works exist in flat sections. In addition retaining structures, large span Bridge on Wonchit River and a number of cross drainage structures are among the major works.

የዚህ ፕሮጀክት ኮንትራት ስምምነት ከተፈረመ በኋላ ሥራው በፍጥነት የተጀመረ ሲሆን ግብአቶችም በጊዜ ወደ ስፍራው ተንቀሳቅሷል፡፡ ይሁንና በ2010 እና በ2011 የሥራ ዘመን እንዳይንቀሳቀስ ታግዶ የነበረው የኩባንያው የባንክ ሂሳብ በፕሮጀክቱ አፈፃፀም ላይ ጉልህ ጫና ፈጥሯል፡፡ ሆኖም በተጠናከረ ጥረትና ገሚሱን ሥራ ለንዑስ ተቋራጭ በመስጠት ፈታኙን ሁኔታ ለማለፍ ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት በ2012 የሥራ ዘመን ኩባንያው ቀድሞ ወደ ነበረበት የሥራ አፈጻጸም ደረጃ ሊመለስ ችሏል:: የጠጠር መፍጫና የአስፋልት ማዋሀጃ መሳሪያዎችን በሰዓቱ በማንቀሳቀስም የፕሮጀክቱን የግንባታ ሂደት እንዲፋጠን ተደርጓል፡፡

በ2012 የሥራ ዘመንም አብዛኛውን የፕሮጀክቱን ሥራ ማለትም 55 በመቶ ያህል ለማጠናቀቅ ታቅዶ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት በዓለም ከተማ እና ኪሜ 48+000 መሃል ባለው የመንገድ ክፍል ላይ በስፋት ስምሪት የተደረገ ሲሆን፤ ኤስ ሃዊ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ የተባለው ንዑስ የሥራ ተቋራጩ በአንጻሩ በመራኛ (ኪሜ 48+000) እና ዶጎሎ (ኪሜ 85+000) መካከል ባለው ሥራ ላይ በትኩረት በመሰማራት ሲሰራ ነበር፡፡ ሆኖም በጥቅምት 16 ቀን 2012 በአካባቢው በተፈጠረው ረብሻ ምክንያት አብዛኛው የኩባንያው እና የንዑስ ሥራ ተቋራጩ የግንባታ መሳሪያዎች ሲቃጠሉና ሲወድሙ ሌሎች ግብአቶች ደግሞ ተዘርፈዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ፕሮጀክቱ እ.አ.አ. እስከ መጋቢት 2020 ድረስ ሥራው ተቋርጦ ቆይቷል፡፡ ይሁንና በኩባንያውና በሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት የተቀናጀ ጥረት መራኛ ወረዳ ላይ ከጥቃቱ በተረፉት መሳሪያዎችና ሌሎች ግብአቶችን በማደራጀት በሚያዝያ 2020 (እአአ) ፕሮጀክቱን ዳግም ለመቀጠል ተችሏል፡፡ ፕሮጀክቱ ከቁፋሮና የተፋሰስ ሥራዎች ጋር የተያያዙ ተግባራትን በስፋት ያጠናቀቀ ሲሆን የአስፋልት ልባስ ስራ በ2013 የስራ ዘመን የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

*"ተግዳሮት በሚያጋጥምህ ወቅት፣ መፍትሄውን እንጂ ማምለጫውን መንገድ አትፈልግ፡፡"*
*-ዴቪድ ዊዘርፎርድ*

***"When faced with a challenge, look for a way, not a way out." -David Weatherford***

This project was commenced immediately after signing of the contract. Resources were timely mobilized to commence the permanent works. Despite this, debarment of the company Bank account in 2010 EFY, had significantly hampered the progress of this project in 2010 and 2011 EFY. Through indispensable efforts and assigning part of the work to subcontractor, the company had successfully managed and overcome the unfortunate scenario. And, at the beginning of 2012 EFY, the company had regained its former status. Crusher and Asphalt Mix Plants were mobilized and established on time to expedite the progress of this project. Most of the project works (about 55%C) were planned to be executed in 2012 EFY.

Accordingly, we had been aggressively executing the work on the road section between Alem ketem and km 48+000, while the sub-contractor, S.Hawi General Contractor, had been intensively engaged on road section between Meragna (km 48+000) and Dogolo(km 85+000). But, due to the riot event of October 27, 2019, most of our company construction equipment's had been burnt, damage and other resources were looted. And the project was suspended henceforth up to March 2020. With due successive efforts of our company and concerned stakeholders, on April 2020, we have resumed the works of this project by using some remaining resources in Meragna Woreda and by mobilizing additional resources as much as possible. This project has substantially completed activities related with Earthwork and drainages works. And yet, Pavement layer construction will be its major target for 2013 EFY.








**Prtila Picture of Alemketma -Degolo Asphalt Road Project at Different Stage**

### 3. ጊንጪ-ሽኩቴ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክት

ይህ የመንገድ ፕሮጀክት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምዕራብ ሸዋ ዞን የሚገኝ ሲሆን ከጊንጪ ከተማ ወጣ ብሎ ወደ ቀኝ በመታጠፍ የአዲስ-አምቦን መንገድ ወደ ግራ በመተው ይጀምራል። ይህ ፕሮጀክት የ59ኪ.ሜ የጠጠር መንገድን በዲኤስ4 ደረጃ የመንገድ ዲዛይን ስታንዳርድ መሰረት ወደ አስፋልት የማሳደግ ሥራ ነው፡፡ የመንገድ ሥራው ስምምነት ከተፈረመ በኋላ ወዲያው የተጀመረ ሲሆን ለግንባታው አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች በጊዜ ወደ አካባቢው ተጓጉዘዋል፡፡ ይሁንና በ2010 እንዳይንቀሳቀስ በታገደው የኩባንያው የባንክ አካውንት ምክንያት በ2010 እና 2011 በጀት ዓመት መከናወን የነበረባቸው ስራዎች እንዲጓተቱ አድርጓል፡፡ ከላይ እንደተብራራው በኩባንያው የተቀናጀ ጥረት እነዚህ አደናቃፊ ሁኔታዎች ሊታለፉ ችለዋል፡፡

በ2012 የሥራ ዘመን የዚህን ፕሮጀክት አፈፃፀም ለማቀላጠፍ ኩባንያው ከታህሳስ 2019 (እአአ) አስቀድሞ መጠናቀቅ ካለባቸው ፕሮጀክቶች መሳሪያዎችን ወደ ሥፍራው አዘዋውሯል፡፡ ነገር ግን በመሃልሜዳ - ዓለምከተማ እና ዓለምከተማ - ዶጎሎ ፕሮጀክቶች ጥቅምት 16፣ 2012 በግንባታ መሳሪያዎችና ሌሎች ንብረቶች ላይ የደረሰው ውድመት የተያዘውን ዕቅድ አስተጓጉሏል፡፡ በተጨማሪም በከተሞች አካባቢ የነበረው 13 ኪ.ሜ የሚረዝም ወሰን የማስከበር ችግር በተለይም ጀልዱ (ጎጆ) እና ሽኩቴ ከተሞች ላይ በዓመቱ ካጋጠሙት መካከል ሌላኛው ችግር ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት በከተሞች አካባቢ በታቀደው መሰረት ለማከናወን ባለመቻሉ በመንገዱ ዳርቻ ያሉ ፍሳሽ ማስተላለፊያና የመንገድ አካፋይ ሥራዎች እንዲጓተቱ አድርጓል፡፡ ከወሰን ማስከበር ጋር ተያይዞ የነበሩ ችግሮች ስቀረፉ በሌሎች ቀጣይ ሥራዎች ላይ መጓተት እንዳይከሰት የተለየ ስልት በመንደፍ ተግባራዊ እንደሚደረግ ከወዲሁ ይታሰባል፡፡

የአካባቢው ዝናባማ የአየር ንብረት ሌላው በፕሮጀክቱ አፈፃፀም ላይ እንቅፋት የፈጠረ ተግዳሮት ነበር፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በዓመት ውስጥ ለፕሮጀክቱ የግንባታ ምቹ ጊዜ ከ7 ወራት እንደማይዘል ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህም የፕሮጀክቱን አፈፃፀም ለማሳደግ ተጓዳኝ ሥራዎች በትኩረት ማከናወን ነበረብን፡፡ በአሁኑ ወቅት ዋና ዋና የፕሮጀክቱ ተዛማጅ ሥራዎች የሆኑትን የአፈር ቆረጣ ሥራዎች፣ ፍሳሽ ማስተላለፊያ፣ ግንብና ድልዳሎን በወሰኝ ደረጃ ተከናውነዋል፡፡ በ2013 የሥራ ዘመን ያልተጠናቀቁ ሥራዎችን በማከናወን ፕሮጀክቱን በጊዜ ለማስረከብ ታቅዷል፡፡

### 3. Ginchi-Shikutie Aspahlt Road Project

The road project was located in Oromia National Regional State in Western part of Ethiopia (West Showa Zone). And it starts at the outskirt of Ginchi town, turning to the right while leaving Addis Ambo trunk road to the left. The project work consists of upgrading existing 59 km gravel road to Asphalt Concrete road in line with DS4 ERA road design standard requirements.

This road project was commenced immediately after signing of the contract. Resources were timely mobilized to commence the permanent works. Despite this, debarment of the company Bank account in 2010 EFY, had significantly affected the progress of this project in 2010 EFY and 2011 EFY. As explained earlier, through indispensable efforts the company had successfully managed and overcome this unfortunate scenario.

In 2012 EFY, the company had planned to expedite the progress of this project by deploying equipment from projects which were expected to complete their major work before end of December 2019. But the damage of equipment and properties of Mehalmeda-Alemketema and Alemketema-Dogolo projects on October 27, 2019 had obliterated this planning. In addition, pending ROW issues of town sections, Jeldu(Gojo), and Shikute with a total length of 13km, has been one of the major problems we faced in this fiscal year. And, it had been difficult to execute actives in town sections as we had planned. This situation pends critical activities related with town section side drain Gutter and Median works. Up on settlement of ROW issues, special work methodologies must be implemented to avoid delay of subsequent activities.

Rainy weather condition of the area, had been another scenario that hampers the progress of the project. With time, we have confirmed that the effective construction period of the project is not more than 7 months. Hence we must execute elusively all parallel activities of the project at a time to boost this project performance. Currently, Major activities related with Earth work, drainage, structures and pavement layer are substantially constructed in this project. In 2013 EFY, the project is expected to execute remaining works on sections which are not completed yet and deliver the project on time.



Partial Picture of Ginchi-Shikute Asphalt Road Project at Different Stage

## 4.ሽኩቴ - ጩሉጤ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በምዕራብ ሸዋ ዞን የሚገኝ ሲሆን ከሽኩቴ ከተማ ወጣ ብሎ ከአዲስ-አምቦ መንገድ 59 ኪ.ሜ ርቆ ከጊንጪ-ሽኩቴ መንገድ ጋር ተያይዞ በጩሉጤ ከተማ ላይ ያቆማል፡፡ ይህ የጊንጪ-ሽኩቴ-ጩሉጤ መንገድ ፕሮጀክት ሁለተኛ ክፍል አካል የሆነው 63.2 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድን በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ዲኤስ4 ዲዛይን ደረጃ መሰረት ወደ ኮንክሪት አስፋልት የማሳደግ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ነው፡፡

የፕሮጀክቱ ኮንትራት ስምምነት ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ጋር በግንቦት 1፣ 2011 ከተፈረመ በኋላ የመንገድ ሥራው ጷጉሜ 4፣ 2011 ላይ ወደ ሥራ የተገባበት ነበር፡፡ ይህ የመንገድ ፕሮጀክት የአካባቢውን ማህበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ ሁኔታ በማሻሻልና በደካማ የመንገድ መሰረተ ልማት ምክንያት በአካባቢው የሚስተዋለውን የህዝብ ትራንስፖርት ችግር ለመቅረፍ እንደሚያስችል ይጠበቃል፡፡ ልክ እንደ ጊንጪ-ሽኩቴ ፕሮጀክት ሁሉ በ2012 በጀት ዓመት ኩባንያው የዚህን መንገድ ፕሮጀክት ለማቀላጠፍ እንዲቻል ከመሃልሜዳ-ዓለምከተማ እና ዓለምከተማ-ደጎሎ ፕሮጀክቶች ዋና ዋና የግንባታ መሳሪያዎችን በማዘዋወር ዋና ዋና ስራዎችን እስከ ታህሳስ 2019 (እአአ) ለማጠናቀቅ አቅዶ ነበር፡፡ ሆኖም በመሃልሜዳ-ዓለምከተማ እና ዓለምከተማ-ዶጎሎ ፕሮጀክቶች ያጋጠሙት የንብረት ውድመቶች እቅዱን አደናቅፏል፡፡ በተጨማሪም ተቆጣጣሪ መሐንዲሱ የዲዛይን ክለሳውን የማፅደቅ ሂደቱን በማጓተቱ መደበኛ ስራው በጊዜ እንዳይጀመር አድርጓል፡፡ በተደረገው ጥረትም በዚህ ዓመት የፕሮጀክቱ የቁፋሮ ሥራን ለማስጀመር ተችሏል፡፡ ይሁንና በኮንትራት ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ እንዲቻል በሚቀጥለው በጀት ዓመት በርካታ ሥራዎች ማከናወን ይጠበቅብናል፡፡

## 4. Shikutie-Chulute Aspahlt Road Project

The road project is located in Oromia National Regional State in Western part of Ethiopia (West Showa Zone). And it starts at the outskirt of Shikute town at about 59km away from Addis Ambo trunk road along Ginchi-Shikute road and ends at Chulute town. It is part second part (Lot II) of Ginchi-Shikute-Chulute Road project. The project work consists of upgrading existing 63.2 km gravel road to Asphalt Concrete road in line with DS4 ERA road design standard requirements.

Up on signing a contract agreement with Ethiopian Roads Authority (ERA) on the 9th of May 2019 and the project work was commenced on the 9th of September 2019. And, after construction, this road project it is expected to improve the socio economic status of the community and resolve the current public transport problem arising from the current poor road condition.

Similar to Ginchi shukute project, In 2012 EFY, the company had planned to enhance the progress of this project by deploying equipment from Mehalmeda -Alemketema and Alemketema-Degolo projects, which were expected to complete their major work before end of December 2019. But the damage of equipment and properties of Mehalmeda-Alemketema and Alemketema-Dogolo projects on October 27, 2019 had obliterated this planning. Moreover late assignment of supervision consultant has also delayed design review and approval processes. Whereupon commencement of the permanent work were not on time as it had been planned. With due efforts, the project had executed significant earth work volume within a




Partial Shikute-Chullute Asphalt Road Project Pictures

## 5. አምቦ ከተማ የውስጥ ለውስጥ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክት

ይህ የመንገድ ፕሮጀክት ሙሉ በሙሉ በአምቦ ከተማ ውስጥ የሚገኙ የመንገድ ክፍሎችን ያካተተ ነው፡፡ ይህም 6 (ስድስት) ቀጠናዎች ያሉት እና በጠቅላላው 15ኪ.ሜ የሚረዝም ሲሆን የመንገዶቹ ስፋትም ከ18ሜ እስከ 30.50ሜ የሚደርስ ነው፡፡ የእነዚህ መንገዶች ግንባታ በጥቅሉ ሲታይ አማራጭ መስመሮችን በመፍጠር በአምቦ ከተማ ውስጥ ያለውን የመንገድ ትራፊክ ችግሮችን ያሻሽላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የፕሮጀክቱ ኮንትራት የካቲት 17፣ 2008 ተፈርሞ መጋቢት 15፣ 2008 ዓመተ ምህረት ግንባታው የተጀመረ ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት የአዳዲስ መንገዶች ግንባታን እና አሁን ያለውን የኮረኮንች መንገድና በከፊል አስፋልት የለበሰውን መንገድ ጭምር ወደ ተሟላ የአስፓልት መንገድ ማሻሻልን ያካተተ ነው፡፡

ይህ ፕሮጀክት ሙሉ በሙሉ በከተማ ውስጥ የሚከናወን በመሆኑ ከሌሎች የመንገድ ፕሮጀክቶች ይለያል፡፡ በከተማ ውስጥ የሚከናወን የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ዘርፈ ብዙ የወሰን ማስከበር ችግሮች አሉበት፡፡ በዋነኝነትም የተለያዩ በመሬት ውስጥና ከመሬት በላይ ያሉ ንብረቶች እና የመሰረተ ልማት አገልግሎት መስጫ መስመሮች ሳይነሱ ሥራውን ማከናወን አስቸጋሪ መሆኑ ከዚህ አንጻር የሚጠቀስ ነው፡፡

በ2012 በጀት ዓመትም የዚህን ፕሮጀክት የሁሉንም ቀጠናዎች ስራ ለማከናወን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የግንባታ ሥራዎቹ በቀጠና 2 እና ቀጠና 3 ብቻ ተከናውኗል፡፡ ይህም በዋነኝነት ለግንባታ ሂደቱ እንቅፋት የሆኑትን ንብረቶች በወቅቱ ማንሳት ባለመቻሉ ነው፡፡ ምንም እንኳን በቀጠና 1A የወሰን ማስከበር ሥራ በApril 2020 (እአአ) የተጠናቀቀ ቢሆንም በዲዛይን ክለሳ ምክንያት ተጨማሪ የወሰን ማስከበር ሥራ በማስፈለጉ ስራው ሙሉ በሙሉ ሊከናወን አልቻለም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በቀጠና 1B የነበረው የወሰን ማስከበር ሥራዎች በJune 2020 መጠናቀቅ ቢችሉም በዝናብ ምክንያት ሥራውን ለማከናወን አልተቻለም፡፡ በ2012 በጀት ዓመት ለመንገድ ሥራው ወሰን ማስከበር የተቻለው ከጠቅላላ የመንገዱ ርዝመት 50 ከመቶ ያነሰ በመሆኑ ምክንያት ዋናውን የፕሮጀክቱን ሥራ በተያዘው ፕሮግራም እና የውስጥ እቅድ መሰረት ለማከናወን አዳጋች አድርጎ ቆይቷል፡፡

short period. Yet, however, much has to be done in the forthcoming year's to complete the project works within the contract time.

## 5. Ambo Town Internal Asphalt Road Project

This road project is a package of road segments that are totally located within ambo town. The package has 6 (six) segments whose length adds up to 15km. And, the widths of the roads ranges from 18m-30.50m. Ultimately, the construction of these roads will improve the current traffic management difficulties by providing alternative access routes within the city.

After signing the contract, on the 25th of February 2016 the project was commenced on the 24th of March 2016.The project consists of construction of new roads, upgrading of the existing gravel and partially surfaced asphalt roads of the city.

The nature of works of this project is quite different from other undergoing road projects as it is located within a City. And road construction within a city has peculiar challenges related with ROW issues. Practically, it had been impossible to commence work in any of this project road sections without prior removal of surface, sub surface and areal properties.

During 2012 EFY it had been planned to execute work on all segments of this project. However, construction activities had been carried out only on two road segments, Segment 2 and segment 3. And this was due to late removal of obstructions by the roads authority. Segment 1A had been cleared of obstructions as of April 2020, but construction activities were not fully executed due late design

ይሁንና ወሰን በተከበረባቸው የፕሮጀክቱ ክፍሎች የቁፋሮ፣ የመንገድ ዳርቻ ፍሳሽ ማስወገጃ ስራዎች፣ የሁሉቃ ወንዝ ድልድይ አካቶ የንጣፍ ማልበስ ስራዎች በአብዛኛው የመንገድ ክፍል ተጠናቋል፡፡ በቀጠና 4፣ ቀጠና 6፣ ቀጠና 1A እና ቀጠና 1B የመንገድ ሥራ ወሰን ውስጥ ያሉ ንብረቶችን ማንሳት በ2013 በጀት ዓመት የሚጠበቅ ቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ ፕሮጀክቱን በታቀደለት ጊዜ ለማጠናቀቅ እንዲቻል ሁሉም ባለድርሻ አካላት ከላይ በተዘረዘሩት ቀጠናዎች ያሉት ንብረቶችን ለማንሳት በጋራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

revision and subsequent need for removal of additional obstructions. Similarly, Segment 1B was cleared of obstruction as of June 2020 and due rainy weather condition it became difficult to execute work except clearing activity. Indeed, in 2012 EFY only less than 50% of the contract length has been readily available for work. And it had been difficult to carry out the works in line with the approved master work program and internal work schedule of the project.

Despite this, however, the project had completed earth works, side drainage works, a box girder bridge ( at Huluka river ) and pavement layers up to sub base layer on substantial length of those section that were timely cleared of ROW obstructions. Certainly, removal of obstruction on segment 4, Segment 6, Segment 1A, and part of Segment 1B will be the outstanding issue of the project for execution of works in the upcoming, 2013 EFY. Hence, all stakeholders should work jointly to remove obstructions from the aforementioned road segments for on time completion of the project.



**Ambo Town Internal Asphalt Road Partial Pictures**

## ለ. የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክቶች

ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኃ. የተ. የግል ኩባንያ የራሱን ዋና መስሪያ ቤት እና እህት ኩባንያ የሆነውን የኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ህንጻ ግንባታን በተሳካ ሁኔታ በመፈጸም ወደ ህንፃ ግንባታ ኢንደስትሪ ዘርፍ በመቀላቀል የቢዝነስ አድማሱን አስፍቷል፡፡ የነዚህ ፕሮጀክቶች በስኬት መጠናቀቅ ኩባንያው በህንፃ ግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ እንዲሳተፍ አዲስ መንገድ እንዲቀይስ አስችሎታል። ከዚህ በታች የተመለከቱት የህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶች በዚህ የበጀት ዓመት በግንባታ ላይ የነበሩ ናቸው፡፡

## B. BULIDING CONSTRUCTION PROJECTS

While constructing its own head quarter building and its sister company international hotel building by its own force, the company expands its horizon in the construction industry. Indeed, the successful completion of these building projects have opened a new endeavor towards contracting construction projects in the Building sector. And, currently the following building projects were under construction in this fiscal year.

## 1. ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ማስፋፊያ እና ፓርኪንግ ፕሮጀክት

ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ኩባንያ በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን ባለ ዘርፈ-ብዙ ህንፃ ግንባታ ለመስራት ከእህት ኩባንያው ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ጋር ስምምነት ፈፅሟል፡፡ የዚህ ፕሮጀክት ግንባታ ሥራ ቁጥጥርና ክትትል በKOLLEG Consult ኃ.የተ. የግል ኩባንያ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

ይህ ፕሮጀክት ለኩባንያው በአይነቱ የመጀመሪያ በመሆኑ ኩባንያው ወደ ህንፃ ግንባታ ኢንደስትሪ ዘርፍና ተዛማጅ ፕሮጀክቶች ለመግባት ላስቀመጠው ግብ መንደርደሪያ ሆኖ አገልግሎታል፡፡ የዚህ ህንፃ ዲዛይን እጅግ ዘመናዊ እና ሁለት የምድር ውስጥ ወለልን ጨምሮ ባለ 24 ወለል ህንፃ ሲሆን ከኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል አጠገብ የሚገኝ ነው፡፡

ይህ ህንፃ ስምንት ወለሎቹን በአንድ ጊዜ ከ300 በላይ መኪናዎች ማቆሚያ እንዲሆን በማነፅ ረገድ ለከተማዋ በአይነቱ የመጀመሪያ ሲሆን ለኢሊሊ ሆቴል ተገልጋዮችን ጨምሮ ለሌሎች የመዲናይቱ ነዋሪዎች የፓርክንግ አገልግሎት እንዲሰጥ የታሰበ ነው፡፡ ህንፃው ሲጠናቀቅ ዘርፈ ብዙ ግልጋሎት ይኖረዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በ2013 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ውስጥ ከሚጠናቀቁ ቀሪ ጥቃቅን ሥራዎች በስተቀር ፕሮጀክቱ በአብዛኛው ተጠናቆ ለአሰሪው ለማስረከብ በሚያስችል ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

## 1. Ellilly International Hotel Expansion and Parking Project

GemshuBeyene Construction PLC signed the 1st ever high rise building contract agreement with Elilly International Hotel, a sister company, for the construction of Elilly Multi-purpose Building Complex and Parking. The construction supervision works is currently being undertaken by KOLLEG Consult PLC.

Since this ultra-modern high rise building project was the 1st in its type for GEBECON PLC, it opened further opportunities for the company to meet and realize the goals of building construction industry. The design scheme of this building is ultra-modern that comprises 2B+G+21 high stories. And it's is located adjacent to Elilly International Hotel.

It is the first building of its kind in the City with eight floors of car parking that can accommodate 300+vehicles at a time. And it has been intended to serve customers of Elilly International Hotel in particular and the public in general. The building is intended to provide multi-purpose functions up on its completion. Currently the project is almost completed except remaining minor finishing works which will be executed in the 1st quarter of 2013 EFY and the project is expected to be handed over to the client accordingly.



Completed Elilly Multipurpose 24 Stories Building

## 2. አርሲ ዩኒቨርሲቲ ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት

አርሲ ዩኒቨርሲቲ በአሰላ ከተማ የሚያስገነባቸው ህንፃዎች አካል የሆነውን የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት ለማስገንባት ከገበኮን ኃ. የተ. የግል ኩባንያ ጋር ውል ፈፅሟል፡፡ ይህ ፕሮጀክት አንድ ትልቅ የተማሪዎች መመገቢያ፣ ክሊኒክ እና 4.2 ኪሜ አጥር የዋና መግቢያ በር ግንባታን ያካተተ ነው፡፡ የፕሮጀክቱን ክትትል Aspire AECOM Architectural and Engineering ኃ. የተ. የግል ኩባንያ እያከናወነ ይገኛል፡፡

የግንባታው ዲዛይን የአርሲ ኦሮሞን ባህልና ታሪካዊ ማንነት እንዲያንፀባርቅ ተደርጎ የተዘጋጀ ሲሆን የተማሪዎቹ መመገቢያ ህንፃ፣ ዋናው በር እና አጥር ይህንኑ እንዲያሳኩ ተደርጎ ተነድፏል፡፡ የተማሪዎች መመግቢያ ህንፃን ጨምሮ የአጥርና የዋናውን በር ግንባታ በገበኮን ሲሰራ የነበረ ሲሆን የክሊኒኩ ህንፃ ግንባታ ደግሞ ሆማ ኮንስትራክሽን ኃ. የተ. የግል ኩባንያ በተባለ ንዑስ የሥራ ተቋራጭ እየተገነባ ነው፡፡ የመመገቢያ ህንፃው የዩኒቨርሲቲው ወሳኝ አካል እንደመሆኑ መጠን በርካታ ተማሪዎችን ማስተናገድ ከመቻሉ ባለፈ ትልቅ ታሪካዊ ቅርስም ጭምር ነው፡፡ ይህ ህንፃ ሲጠናቀቅ ትልቅ ዘመናዊ የማብሰያ፣ የመስተንግዶ፣ የመጋዘን እና ሰፊ የመመገቢያ አዳራሽ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ነው፡፡

የዚህ ፕሮጀክት ሥራ ከአጥር የብረት ሥራ፣ የመግቢያ በር ጮጮ ሥራ በስተቀር በገበኮን የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ከሞላ ጎደል ተጠናቀዋል፡፡ በሆማ ኮንስትራክሽን የሚገነባው የክሊኒክ ግንባታ በአብዛኛው ተጠናቋል፡፡ በዚሁ መሰረት ፕሮጀክቱ በጠቅላላው በመጠናቀቅ ላይ ያለ ሲሆን በዚህ የበጀት ዓመት ለአሰሪው ይተላለፋል፡፡

## ሐ. የውሀ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች

የውሀ ሥራዎችንና ተዛማጅ ፕሮጀክቶችን ለመስራት ገበኮን በ2017 (እአአ) የውሀ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ዘርፍ እንደ አዲስ የሥራ መስክ አስተዋውቋል፡፡ በ2012 የበጀት ዓመት ኩባንያው ከዚህ በታች በዝርዝር እንደቀረበው የሞጆ ውሃ መካከለኛ ደረጃ የመስኖ ፕሮጀክት ግንባታ ሥራን በመጀመር ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

## 2. Arsi University Building Project

Gemshu Beyene Construction PLC has entered in to a contract agreement with Arsi University for the construction of part of the University building in Asella town. The major works of the project comprises one large student canteen, Clinic and main-gate with 4.2km fence. The construction supervision of the project has been currently undertaken by Aspire AECOM Architectural and Engineering PLC.

The aspiration of design were historical symbolism and cultural reflection of Arsi- Oromo culture. Hence, the roof structure of student canteen, main gate and fence were architecturally designed to signify Arsi-Oromo heritages.

The construction of the student Canteen and the Fence with the main gate have been undertaken by GEBECON PLC while that of the Clinic was sub-contracted to Homa Construction PLC. And, the canteen building was one of the vital elements of a university as it accommodates a number of students besides its monumental symbolism. The building of canteen up on completion, comprises functions like large and modern kitchen, serving area, storage area, large hall for dinning with the provision of an open down lights spaces.
Major works which have been carried out by GEBECON PLC (Student Canteen, Fence and main gate) are more or less completed except the RHS Rubber Copping of the fence and the ‘Chocho’ construction at the main gate. The Clinic Work, undertaken by Homa construction PLC, has been also substantially completed. Indeed, the project is substantially completed and it will be handover to the client in this fiscal year.

## C. WATER WORKS CONSTRUCTION PROJECTS

GEBECON introduced Water Works Construction Department in 2017 as a new business line for the first time to undertake the construction of water works and related projects. In 2012 EFY our company has been engaged in the construction of Mojo Medium Scale Irrigation project whose detail is presented as follows.

## ሞጆ መካከለኛ ደረጃ የመስኖ ግድብ ሥራ ፕሮጀክት

የሞጆ መካከለኛ ደረጃ የመስኖ ግድብ ፕሮጀክት ከአሰግድ ኤፍሬም ውሀ ሥራዎች ተቋራጭ ጋር በጋራ ለመገንባት ገበኮን ከኦሮሚያ ግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮ ጋር በሚያዝያ 17፣ 2011 የሥራ ስምምነት ፈፅሟል፡፡ ይህ ፕሮጀክት በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሀረርጌ ዞን ማዩ ሙሉቄ እና ቁንቢ ወረዳዎች ይገኛል፡፡ ከአዲስ አበባ በሀረር አቅጣጫ በ511ኪ.ሜ ርቀት ጉዞ በኋላ ከአደሌ መንደር ወደ ቀኝ በመታጠፍ አደሌ፣ ግራዋ እና ኡሴ ከተሞችን በሚያገናኘው መንገድ ተጨማሪ 150 ኪ.ሜ ጉዞ በኋላ ይገኛል፡፡

ይህ ፕሮጀክት የዋና ግድብ ሥራና የውሀ መተላለፊያ ቦይ ሥራዎችን ጨምሮ የመስኖው መዳረሻ መንገዶች፣ እንዲሁም የካምፕ ግንባታ ሥራዎችን ያካተተ ነው፡፡ በ2012 በጀት ዓመት የካምፕና የመዳረሻ መንገድ ግንባታ የተጠናቀቀ ሲሆን የዋና ግድቡና የውሀ መተላለፊያ ቦይ ግንባታዎች በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚሁ መሰረት ዋናውና ሁለተኛው የውሃ መተላለፊያ ቦዮች፣ ተዛማች ግንባታዎችና ዋናው የግንብ ሥራ በ2013 በጀት ዓመት ለማጠናቀቅ በዕቅድ የተያዙ ናቸው፡፡

### የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ማጠቃለያ

ከ2012 በጀት ዓመት እስከ አሁን ጠቅላላ ፕሮጀክቶች ለኩባንያው የሥራ አፈፃፀም ያላቸው አስተዋፅኦ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## Mojo Medium Scale Irrigation Project:

GEBECON PLC in JV with Asegid Ephrem Water Works Contractor (WWC) entered in to a contract agreement on 25th April 2019 with Oromia Agricultural and Natural Resource Bureau for the construction of Mojo Medium scale Irrigation Project. This project is located in East Hararge Zone, Mayu Muluke and Qumbi Woredas of State of Oromia. And one can reach this project, after traveling 511 km on Addis-Harar main road and turning to the right at Adele village and travelling additional 150km on gravel road that connect Adele, Girawa and Usse towns,.

The works under this contract consists of the construction of Head Work, Canal works, Access Road and Camp construction. In 2012 EFY, camp and access roads construction were completely constructed while head work and main canal constructions are at promising stage. Therefore, main canals, secondary canals, drop structures and head work constructions should be completed in the upcoming 2013 EFY.

### SUMMARY OF TO DATE EXECUTIONS

Summary of the 2012 EFY year to date and total to date contribution of projects on the company performance is shown in Chart 1, Chart 2, for ease of reference.




**Chart1: 2012 EFY Total Executions by Project**




**Chart 1: 2012 EFY Total Executions by Project**




**Chart2: Total to date Executed Amount by project**




**Chart 2: Total to date Executed Amount by project**

*"እንቅፋቶች እንደሚያጋጥሙ አውቀህ አስቀድመህ ተጋፈጣቸው፡፡ መምጣታቸው ስለማይቀር ልዩነቱ የምትቆጣጠርበት መንገድ ነው፡፡"*
*- ላንስ ዴል*

***"Expect obstacles and face them head on. They are going to come up so the way you handle them is what makes all the difference." – Lance Dale***

## ማጠቃለያ

ምንም እንኳን በ2012 የበጀት ዓመት ድርጅቱን ያጋጠሙት ከላይ የተጠቀሙት ተግዳሮቶች እጅግ ከባድና ፈታኝ ቢሆኑም የኩባንያው ጠቅላላ የሥራ አፈፃፀም ሲገመገም አመርቂ ነበር፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ እነዚህ ድርጅቱን ያጋጠሙት ችግሮች ከፍተኛ የሥራ መጓተትን በማስከተላቸው የተወዘፉት ሥራዎች በ2013 በጀት ዓመት በከፍተኛ ርብርብ መፈጸም ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም ስኬት ሲባል የቀጣይ በጀት ዓመት የሥራ ዕቅድ በአግባቡ እነዚህን ሁኔታዎች ከግምት ያስገባ እና የሀብት አጠቃቀምን ውጤታማነት ማረጋገጥን የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

በ2012 በጀት ዓመት ሲሰሩ ከነበሩ ፕሮጀክቶች መካከል መሃልሜዳ-ዓለምከተማ መንገድ ፕሮጀክት ለአሰሪው ተላልፏል፡፡ ከጥቃቅን ቀሪ ስራዎች በስተቀር የአርሲ ዩኒቨርሲቲ እና የኢሊሊ ሆቴል ማስፋፊያ ፕሮጀክት በአብዛኛው ተጠናቋል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ፕሮጀክቶች በኩባንያው የ2013 በጀት ዓመት አፈፃፀም ላይ ጫና አይኖራቸውም፡፡

በሌላ በኩል የሸኩቴ-ጩሉጤ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክት እና ሞጆ መካከለኛ ደረጃ የመስኖ ፕሮጀክት አፈፃፀም በ2013 በጀት ዓመት መፋጠን አለባቸው፡፡ የዓለምከተማ-ደጎሎ እና የጊንጪ-ሽኩቴ ፕሮጀክቶች በ2013 በጀት ዓመት በአብዛኛው እንዲገባደዱ ልዩ ትኩረት መስጠትን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ዋጋ፣ ጥራት እና ጊዜ እንዲጠናቀቁ የኩባንያችን የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

## Conclusion:

Whereas the aforementioned problems that we had encountered in 2012 EFY had been very dreadful, the overall performance of our company is remarkable. But, these problems had leftover, a significant back logged work, which should be substantially completed in the 2013 EFY. And this necessities a well-planned action that can ascertain an efficient utilization of resources.

Among the projects that had been undertaken in the 2012 EFY, Mehalmeda-Alemketeam is transferred to the client. Arsi University and Elilly Hotel Expansion project are substantially completed except minor finishing work. Hence, these projects have no influence on the upcoming 2013 EFY Company performance.

Whereas Shikute Chulute Asphalt road project and Mojo medium scale Irrigation project progress should be expedited in the upcoming 2013 EFY. And special effort should be exerted on Alemketema~Dogolo and Ginchi Shikute projects which must be substantially completed in 2013 fiscal year. Therefore, our company management staff and employees should prepare and discharge their responsibility to complete these project within the anticipated cost, quality and contract time.

# ውጤታማ የሥራ ቦታ ቡድን ግንባታ መንገዶች
# The Way for Effective Team Building in the Workplace



**Ato Kassim Fite**
Company Adviser
አቶ ቃሲም ፊጤ
የካምፓኒ አማካሪ

*“ሁሉም ሰው  በጋራ መሥራት አለበት፤ እያንዳንዱ ሰው ወደጋራ ግቦች እንዲሠራ ማድረግ ካልቻልን ምንም ነገር ሊከወን አይችልም።” -ሃሮልድ ኬ. ስፔርሊች*

***“Everyone has to work together, if we can’t get everybody working toward common goals, nothing is going to happen.” –Harold K. Sp erlich***

## 1. መግቢያ

የቡድን ግንባታ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለማጎልበት እና በቡድኖች ውስጥ ሚናዎችን ለመለየት የሚያገለግሉ የተለያዩ አይነቶች እንቅስቃሴዎች የጋራ መጠሪያ ቃል ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የትብብር ተግባራትን ያጠቃልላል፡፡ ሥራ አስኪያጆች እና የድርጅት አባላት የንግድ ውጤቶችን እና ትርፋማነትን ለማሻሻል ዘዴዎችን በአጠቃላይ ይመረምራሉ፡፡ ብዙዎች የንግድ ሥራን በመፍጠር ረገድ ሁሉንም ሰራተኞች ለማሳተፍ በቡድን ላይ የተመሠረተ፣ አግድም መዋቅሮችን እንደ ምርጥ የድርጅት መዋቅር ይመለከታሉ፡፡ የቡድን ግንባታ ለድርጅቶች የቀረቡ እና የቡድን አፈፃፀም ለማሻሻል ያለሙ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያጠቃልላል፡፡ ሠራተኞችን እንደ ግለሰብ ሠራተኛ ሳይሆን እንደ ተሰናሰለ ቡድን አባላት የሚመለከት የሥራ ዲዛይን ፍልስፍና ነው ፡፡

የቡድን ሥራ ለስኬታማ ድርጅቶች እንደ ወሳኝ አቅም ተደርጎ ሲወሰድ ቆይቷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በተፈጠረው የአሰራር መሰረታዊ ለውጥና በዲጂታል አሰራር የታገዘ ለማድረግ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት መሻሻልን ለማሳየትና ኢኮኖሚውን ለማሳለጥ “ፈጣራ ወይም ሞት” በሚባልበት ምጣኔ ሀብት ዘመን የግዴታ አስፈላጊ መሆናቸውም ሰራተኞች ከዘመኑ ጋር አብረው በመጓዝና በተለያዩ ጂኦግራፊያዊ አካባቢዎች ሆነውና የተለየ የሥራ ተዋረድን ጠብቀው ሥራን በቡድን ማስኬድ እንዲችሉ ማድረግን ይሻል፡፡

## 1. Introduction

Team building is a collective term for various types of activities used to enhance social relations and define roles within teams, often involving collaborative tasks. Managers and organization members universally explore ways to improve business results and profitability. Many view team-based, horizontal, structures as the best design for involving all employees in creating business success. Team building involves a wide variety of activities, presented to organizations and aimed at improving team performance. It is a philosophy of job design that sees employees as members of interdependent teams rather than as individual workers.

Teamwork has always been an essential capability for successful enterprises, but with today’s organizations undergoing disruption and digitization in an ‘innovate or die’ economy, it is now more important than ever that employees can collaborate effectively across geographical sites, between business functions and within increasingly fluid job hierarchies.

በዚህ ረገድም ይህ ፅሁፍ የቡድን ሥራ የሚዳብርባቸውን መንገዶች ይፈትሻል፡፡ በጋራ መሥራት የሚቻልባቸውን ቁልፍ ጉዳዮችን በመለየት ይዳስሳል፡፡ በዘርፉም ያሉትን ተስፋዎችና ችግሮችን በማስቀመጥ በተግባር ምን ማከናወን እንደሚቻል ያሳያል፡፡

## 2. የቡድን ግንባታ ፅንሰ ሐሳብ

ቡድን ጥቂት በሆኑ ሰዎች የሚመሰረት፣ ግልጽ የጋራ ዓላማዎች ያለው፣ ራሳቸውን ሰጥተው ለጋራ ፍላጎት የሚሰለፉበት እና እራሳቸውን ለጋራ ተጠያቂነት የሚያስገዛ አደረጃጀት ነው፡፡ የቡድን ግንባታ የቡድኑን አባላት አቅም በማጎልበት የተቀመጡት ግቦች ላይ እንዲደርሱ የማስቻል ሂደት ነው፡፡ ሂደቱ የቡድኑን ግቦች ግልጽ ማድረግ፣ በግቦቹ ላይ ሊጋረጡ የሚችሉትን መሰናክሎችን መለየት፣ የተለዩትን ችግሮች መጋፈጥና ግቦቹ እንዲሳኩ ማስቻልን የሚያካትት ነው፡፡ በቡድን መሥራት ያሉትን ሃብቶችና ግብአቶችን ከድርጅቱ ግቦች ጋር በማጣጣም ለቡድኑ እያንዳንዱ አባል ተዘርዝረው የተሰጡት ሥራዎች የሚከወኑበት፣ ችግሮችን እኩል በመጋፈጥ መፍትሄ የሚሰጥበት እና በሂደቱም መሻሻሎች በቀጣይነት እንዲታይበት ይፈለጋል፡፡

የቡድን ግንባታ ሂደት ሁለት መሰረታዊ ክህሎቶችን ያካትታል። የመጀመሪያው ዋንኞቹን ጉዳዮች በትክክል ለይቶ የመገንዘብ ክህሎት ሲሆን፣ ሁለተኛው የተለዩትን ጉዳዮች በተገቢው መንገድና ቅደም ተከተል ለመፍታት የሚያስችል ተግባርን የመፈጸም ክህሎት ነው፡፡ የቡድን ግንባታ እንደ ቡድኑ አባላት ቁጥርና ባህሪይ ይለያያሉ፡፡ ለምሳሌ የቡድኑ አባላት በየጊዜው በሚቀያየርበት ሁኔታ ውስጥ እያንዳንዱ የቡድን አባል ባለበት ቦታ ላይ ብቁ የቡድኑ አባል እንዲሆን በግለሰቡ ክህሎት ግንባታ ላይ በማተኮር ግለሰቡ ባለበት ቡድን ውስጥ ወይም በብዙሃኑ ቡድኖች ውስጥ የላቀ ሚና እንዲጫወት ማብቃት ተገቢ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የቡድኑ አባልነት እንደ እንደ ማኔጅመንት ቡድን አባላት የቋሚነት ባህይሪይ የሚስተዋልበት ከሆነ በአባላቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ማሻሻልን ዒላማ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

ከፍተኛው የቡድን ግንባታ በድርጅት ደረጃ የሚደረገው ነው። ከከፍተኛ የሥራ አመራር ቡድን አባላት በስተቀር ግለሰቦች በድርጅታዊ ባህል ላይ ተጽዕኖ የማሳደር አቅማቸው በጣም ውስን ነው ፡፡ የቡድን ግንባታው ቁልፍ ዓላማዎች አንዱ በድርጅቱ ውስጥ የተንሰራፋውን ባህሪ እና አመለካከቶች መለወጥ ነው፡፡ ቡድን መገንባት ማለት ቡድኑን አንድ ላይ ማድረግ ማለት አይደለም፡፡ ቡድኑ ለሚፈልገው ወይም ለሚያስፈልገው ነገር ላይ በቂ ግንዛቤ ሳይኖር በቡድኖች ላይ ከሚጫኑት አጠቃላይ ተግባራትም በላይ ነው፡፡ የበለጠ የታሰበ አካሄድ እና ከሁሉም በላይ ዓላማዎች በግልጽ የተቀመጡበት እና የሚሟሉበት ነገር ያስፈልጋል፡፡ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ የተወሰኑ ጉዳዮችን እና በቡድኑ ውስጥ የተካተቱትን ሰዎች ዓይነት ወይም ስብዕናዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ የቡድን ሥራ የግለሰቦችን ሥራ የሚያካትት የጋራ ሥራ ዓይነት ነው፤ ግን ብዙውን ጊዜ እያንዳንዱ አባል የቡድኑን የጋራ ጥበብ የሚያንፀባርቅ አንድ የተፃፈ ሰነድ አካል የሚያበረክተውን አንድ ዓይነት የጋራ ሥራን ያጠቃልላል፡፡ የስብስቦች (grups) ሥራ በሀሳብ ልውውጥ ላይ የተመሠረተ ሲሆን የቡድን ሥራ ግን በውይይት ላይ የተመሠረተ ነው ፡፡

The paper examines the development of teams in organizations. It explores key issues associated with the implementation of teamwork and examines the prospects and challenges of team building to present a realistic idea of what can be achieved through teamwork.

## 2. The Team Building Concept

A team can be defined as a small number of people, with a set of performance goals, who have a commitment to a common purpose and an approach for which they hold themselves mutually accountable. Team Building involves the process of enabling the group of people to reach their goals. It consists of steps like clarification of team goals; identification of hindrances to goal achievements; facing the identified challenges and enabling the achievement of the goals. Teamwork is an integration of resources and inputs working in harmony to achieve organizational goals, where roles are prescribed for every organization member, challenges are equally faced and incremental improvements are sought continually.

There are two basic skills in the team building process. The first involves recognizing the right issues, and the second has to do with tackling them in an appropriate way and order. Team building has various forms depending on the size and nature of the team. For instance in situations where team composition is continually changing, the emphasis is on developing the skills in individuals to be effective team members and it endeavors to change the skills and abilities of the individual at operating within a team or within multiple teams. However, where team membership is relatively static like in management teams the emphasis is on efforts aimed at improving relationships between team members.

The largest scale is that of organizational team building. With the exception of the senior management team, the ability of individuals to make an impact on the corporate culture is very limited. One of the key aims of the team building is to change the behaviors and attitudes prevalent in the organization, which are almost independent of who actually works there. Team building doesn't just mean getting the team together. It is more than generic activities imposed upon teams without any real consideration for what the team wants or needs.

ሥራዎቹ ብዙውን ጊዜ የጋራ ስለሆኑ የቡድን ሥራ ውይይቶች ተፈጥሯዊ ውጤቶች ድርድር እና ስምምነት ናቸው ። ምንም እንኳን አባላት በሙሉ የራሳቸውን መንገድ ማግኘት ባይችሉም ውጤቱ ሁልጊዜ የእያንዳንዱን ቡድን አባል ጥሩ አስተሳሰብ እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ያንፀባርቃል። የቡድን ስራ የእሱ ወይም የእሷ አመለካከት በበቂ ሁኔታ እንደ ተወከለ እና ተጠያቂ እንደሚሆን እንዲሰማው ስለሚያደርግ በጣም ውጤታማ ይሆናል። ውይይቱ የእያንዳንዱን ሰው ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ለመለየት የሚያግዝ ሲሆን ድርድሩ እና ስምምነቱ እነዚህን ለማሳካት የቡድን አጠቃላይ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ወደ ሚያንፀባርቅ ውጤት ለመስገኘት ይረዳል።

## 3. የቡድን ግንባታ አስፈላጊነት መወሰን

በርካታ ምክንያቶች ለቡድን ግንባታ አስፈላጊነት አመላካች ሊሆኑ ይችላሉ። ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡ ፡ ለአስተዳዳሪው አሉታዊ ምላሾች መኖር፤ የምርታማነት መቀነስ፤ ግዴለሽነት እና የተሳትፎ መጓደል፤ ስለ አገልግሎት ጥራት ቅሬታዎች መበራከት፤ የተነሳሽነት፣ የፈጠራና ምናብዊነት እጥረት፤ ውስብስብ ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ መደበኛ እርምጃዎች፤ በሠራተኞች መካከል ግጭቶች ወይም ጠላትነት መስተዋል፤ ውጤታማ ያልሆኑ የሠራተኛ ስብሰባዎች፤ ዝቅተኛ ተሳትፎ፣ አነስተኛ ውጤታማ ውሳኔዎች፤ ውሳኔዎች በተሳሳተ መንገድ መረዳትና በውጤቱም በትክክል ያለመከወን፤ ስለ ሥራዎች ግራ መጋባት፣ ያልጠሩ ግንኙነቶች እንዲሁም የመድልዎ ወይም አድልዎ አቤቱታዎች ለጠቀሱ ይችላሉ።

## 4. የቡድን ግንባታ ዓላማዎች

የቡድን ግንባታ በርካታ ዋና ዋና ዓላማዎች ያሉት ሲሆን አንደኛው እንደ ቡድን አባላት እና ግለሰቦች ከተሳታፊዎች ጋር ጥሩ ግንኙነትን ማሳደግ ነው። በተጨማሪም ምርታማነት እና የፈጠራ ችሎታ ይጨምራል። የቡድን ግንባታ ሌላው ዓላማ የተሻሉ የአሠራር ፖሊሲዎችን እና አሠራሮችን ማሳካት ሲሆን በዚህም የቡድን አባላትን ግቦችን ለማሳካት የሚያነሳሳ ነው። እንዲሁም ግልጽ የሥራ ዓላማዎችን እና የትብብር አየርን እና የትብብር ችግር መፍቻ ሁኔታን ለማረጋገጥ ያለመ ነው። በተጨማሪም የቡድን ግንባታ በከፍተኛ ደረጃ መደጋገፍንና መተማመንን ብሎም በጋራ በመሥራት የሚመጣን ከፍተኛ የሆነ የቃልኪዳን አንድነትንና በሥራ መርካትን ያቋድሳል።

## 5. የቡድን ግንባታ ደረጃዎች

ቡድኖች ውጤታማ እንዲሆኑ ካስፈለገ፣ በውስጡ ያሉት ሰዎች የጋራ ውጤት ለማምጣት ሲባል በጥምረት አብረው መሥራት የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል። ነገር ግን ይሄ በቀላሉና ወዲያውኑም ይከሰታል ማለትም አይደለም። ለአንድ አላማ የተሰለፈ ቡድን በጋራ ሲሰራ ግን ይህንን በጥምረት የመሥራት ክህሎት ያዳብራል። በመሰረታዊ ደረጃ የቡድን ልማት ማቋቋም፣ ልዩነቶችን ማውጣትና መከራከር፣ ከልዩነት ወደ አንድነት መምጣትና ሥራን በአግባቡ ፈፅሞ ማስፈፀም እና ሥራን አጠናቆ ወደሌላ ፕሮጀክቶች ትኩረትን ማዞር የተባሉና የራሳቸው ሆነ ለየት ያለ ፈተና ያለባቸው አምስት ደረጃዎችን ይካተቱበታል።

There is need for a more considered approach and above all, something where the objectives are clearly stated and can be met. It is necessary to take into account specific issues that need to be addressed and the sorts or personalities involved in the team. As opposed to group work, which relies on exchange, teamwork relies on discussion. Since the tasks are usually collective, the natural outcomes of teamwork discussions are negotiation and compromise. While no members might get all their own way, the outcome always reflects the best thinking and priorities of each group member. Teamwork can be quite efficient since it results in everyone feeling that his or her point of view is adequately represented and accounted for. The discussion helps to identify each person's highest priorities and the negotiation and compromise helps to synthesize these into an outcome that reflects the group's collective priorities for success.

## 3. Determining the Need for Team Building

Several factors may be indicative of the need for team building. Some of these include; negative reactions to the manager; decreased productivity; apathy and lack of involvement; complaints about quality of service; lack of initiation, imagination, innovation; routine actions taken for solving complex problems; conflicts or hostility among staff members; ineffective staff meetings, low participation, minimally effective decisions; decisions misunderstood or not carried through properly; confusion about assignments, missed signals, and unclear relationships as well as complaints of discrimination or favoritism.

## 4. Objectives of Team Building

Team building has several major objectives one of which is enhancing good communications with participants as team members and individuals. There is also increased productivity and creativity. Another objective of team building is to achieve better operating policies and procedures thereby motivating team members to achieve goals. It is also aimed at ensuring clear work objectives and a climate of cooperation and collaborative problem-solving. Furthermore team building enhances higher levels of trust and support. With team building, diverse co-workers work well together and there are higher levels of job satisfaction and commitment.

የመጀመሪያውና ቡድንን ማቋቋም የሚባለው ደረጃ በርካታ ሰዎች የጋራ የሆነን አላማ ለማሳካት ሲባል ወደ አንድነት የሚመጡበት ነው፡፡ ሁለተኛው ሂደት ደግሞ ልዩነቶችን ማውጣትና መከራከር ሲሆን ይህም የቡድኑ አባላት በተልዕኮ፣ራዕይ እና በአካሄዶች ላይ ያለውን ልዩነት አውጥተው ይሚገቱበታል፤ እርስ በርስም ይግባቡበታል፡፡

ይህ የሁለተኛው ደረጃ ሂደት የቡድን አባላቱ ግንኙነት የሻከረና ግጭቶች ያሉበት ነው፡፡ ይህም ደረጃ በሶስተኛ ደረጃ ላይ ወደሚገኘው አባላቱ በጊዜ ሂደት አስበውበትም ሆነ ሳያስቡበት በፍጥነት የሥራ ግንኙነት የሚመሰረቱበት ሲሆን ይኼም ሂደት የቡድኑ አላማዎችን ለማሳካት የሚቻልበትን ሂደት ቀስ በቀስም አላማዎቹን የሚያሳኩበት ነው፡፡

አራተኛው ደረጃ የሰዎች መስተጋብሮች፣ ቡድኑ የሚሰራበት አካሄድና ውጤታማነትን ከሥራው አላማዎች ጋር በማዋሀድና በማስማማት ስኬታማ በሆነ ሁኔታ የሚሰራ ቡድንን መፍጠር ያስችላል፡፡

የመጨረሻው ደረጃ ቡድኑ በጥሩ ሁኔታ እያከናወነ ያለው የለውጥ ደረጃ ሲሆን አባላት ያጋጠሟቸው በጣም ስኬታማ ቡድን ነው ብለው ያምናሉ ፡፡ ወይም ቡድኑ ተልእኮውን ወይም ዓላማውን ያጠናቀቀበት የመጨረሻ ደረጃ እና የቡድን አባላት ሌሎች ግቦችን ወይም ፕሮጀክቶችን ለመቀላቀል የሚችሉበት ጊዜ ነው፡፡

በተጠቀሰው ቅደም ተከተል መሠረት እያንዳንዱ ቡድን በእነዚህ ደረጃዎች ውስጥ የሚያልፍ አለመሆኑን ልብ ማለት ይገባል፡፡ እንደገና፣ እንደ አዲስ የቡድን አባላት መካተትን የሚጋብዙ የተለያዩ ተግባራት ሲፈጠሩ ቡድንን ወደ ቀድሞ ደረጃዎች ሊመልስ ይችላል ፡፡ የአባላቱ ልምድ ፣ ቡድኑ የሚያገኘው ድጋፍ እና የቡድኑ አባላት ዕውቀት እና ክህሎቶች በእነዚህ ደረጃዎች ውስጥ ለማለፍ አስፈላጊ የሆነውን የጊዜ ርዝመት የሚወስኑ ምክንያቶች ናቸው ፡፡

## 6. ውጤታማ ቡድኖችን መገንባት

ውጤታማ ቡድኖችን ለመገንባት ዋና ዋናዎቹ መስፈርቶች፡- (1) የአባላቱ ቁጥር በቂ መሆን አለበት፤ (2) ተጋጋፊ የሆነ የተሟላ ችሎታ፤ (3) ተጨባጭና ትርጉም ያለው ዓላማ፤ (4) የተወሰነ ግብ ወይም ግቦች፤ (5) ግልፅ የሆነ የአሰራር ዘዴና አካሄድን በቡድን ውስጥ መመስረት፤ (6) የጋራ ተጠያቂነት ስሜት፤ እና (7) ግልጽና ተገቢ የአመራር መዋቅር ናቸው፡፡ ውጤታማ የቡድን ሥራ በተለይም በቡድኑ የመጀመሪያ ደረጃዎች ላይ አመቺ ጊዜን መፈለግ፣ የቡድን አባላትን መምረጥ፣ የቡድን አባላትን ማብቃት፣ ተፈላጊ በሆኑ ክህሎቶች እና ዕውቀት ላይ ሥልጠና መስጠት፣ የጋራ ግቦችን ማዘጋጀት እና የቡድን ሥራን ማመቻቸት ይጠይቃል፡፡

ውጤታማ ቡድኖች በጥንቃቄ የተቀየሱ ናቸው ፡፡ አንድ ቡድን ሲደራጅ የቡድኑን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ማጤን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ የዘርፉ ምሁር ለቡድን ስኬት መሰረታዊ የሆኑ አምስት ተለዋዋጭ ጉዳዮችን ለይቷል፡፡ የመጀመሪያው ተለዋዋጭ የቡድን አባልነት ነው፡፡ ስኬታማ ቡድኖች ልምድ ያካበቱ፣ ችግር የመፍታት ችሎታ ያላቸው፣ ችግሩን ለመቅረፍ ዝግጁ የሆኑ እና በድርጊት ላይ የተመሰረቱ ውጤታማ ግለሰቦች ስብስብ ናቸው፡፡ ሁለተኛው ጉዳይ የቡድን ግንኙነት ሆኖ የቡድኑ አባላት ግብረመልስ ለመስጠት እና

## 5. Stages of Team Building

For teams to be effective, the people in the team must be able to work together to contribute collectively to team outcomes. But this does not happen automatically: it develops as the team works together. Basically team development involves five stages each with its own special challenges. They called the stages: forming, storming, norming, performing, and adjourning.

The first stage of team building is the **forming** which is the stage at which a group of people come together to accomplish a shared purpose. Next is the **storming** stage which involves disagreements about mission, vision, and approaches and team members getting to know each other. This stage can be characterized by strained relationships and conflicts. This is followed by the **norming** stage where the team has consciously or unconsciously formed working relationships that are enabling progress on the team's objectives. The fourth is the **performing** stage in which relationships, team processes, and the team's effectiveness in working on its objectives are synching to bring about a successfully functioning team. The final stage is the **transforming** stage where the team is performing so well that members believe it is the most successful team they have experienced; or the ending stage where the team has completed its mission or purpose and it is time for team members to pursue other goals or projects.

It must be noted however that not every team moves through these stages in the stated order. Again, various activities such as addition of new team members can send a team back to earlier stages. The experience of the members, the support the team receives and the knowledge and skills of the team members are factors that determine the length of time necessary for progressing through these stages.

## 6. Building Effective Teams

The major requirements for building effective teams are: (I) It should be small enough in the number of members; (II) Adequate levels of complementary skills; (III) Truly meaningful purpose (IV) Specific goal or goals; (V) Established clear approach to the team's work; (VI) A sense of mutual accountability; and (VII) Defined appropriate leadership structure. Effective team functioning requires finding time,

ለመቀበል ያላቸው ችሎታ ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ሦስተኛው ተለዋዋጭ ጉዳይ የቡድን ችግር መፍታት ሲሆን ይህም የቡድን ውጤታማነት በቡድኑ ግቦች ትኩረት እና ግልጽነት ደረጃ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያሳያል፡፡ አራተኛው የቡድን አመራር ነው፤ ውጤታማ የቡድን አመራር በአመራር ብቃት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ብቃት ያለው መሪ በግቡ ላይ የሚያተኩር፣ የትብብር መንፈስን የሚፈጥር፣ የቡድን አባላትን በራስ መተማመንን የሚገነባ፣ ተግባራትን ቅደም ተከተል የሚያስይዝ፣ በቂ ዕውቀትን እንዳለው በተግባር የሚያረጋግጥ እና በሥራ አፈጻጸም ላይ ግብረመልስ እየሰጠ የሚመራ ነው፡፡ የድርጅቱ ካባባዊ ሁኔታ አምስተኛው የቡድን ስኬት ተለዋዋጭ ጉዳይ ሲሆን ከድርጅቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ባህል ጋር ለቡድን ባህሪይ ካለው አመቺነት ጋር የተቆራኘ ነው ፡፡

በርካታ የዘርፉ ተመራማሪዎች ውጤታማ ቡድኖችን በመገንባት ዙሪያ የተለያዩ ዘዴዎችን አበርክተዋል፡፡ ምንም እንኳን ምርጥና በከፍተኛ ደረጃ ውጤታማ የሆኑ ቡድኖችን ለመቅረፅና ለማዳበር የሚያስችል አይነተኛ ምርጥ ዘዴ ባይኖርም ዋና ዋና መንገዶችን ግን ከዚህ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

ከፍተኛ ውጤታማ ቡድኖችን ለመንደፍ፣ ለማዳበር እና ለመደገፍ የተሻለው መንገድ ባይኖርም ውጤታማ የቡድን ግንባታ ዋና ዋና አካላትን ለማጠቃለል ሙከራ ተደርጓል ፡፡

ሀ. **የተጠባቂ ውጤቶች እና ዓላማዎች ግልፅነት:-** ለቡድን ግንባታው ውጤታማ እንዲሆኑ ዓላማዎች የተለዩ ፣ የሚለኩ ፣ ሊደረስባቸው የሚችሉ እና ተዛማጅ መሆን አለባቸው፤ እንዲሁም በአጭር ጊዜ ውስጥ SMART መሆን አለባቸው፡፡ በተቻለ መጠን ከሁሉም አባላት የሚሰጠው ግብዓት በግቦቹ ዲዛይንና ቃላት ውስጥ መካተት አለበት፡፡ ሁሉም ከቡድኑ አባላት የሚጠበቁ ነገሮች በግልፅ መገለጽ አለባቸው፤ ቡድኑ የተፈጠረበትን ምክንያት መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከሁሉም የቡድን አባላት ጋር ለመግባባት እና ለመወያየት በመጨረሻ ሊፃፍ የሚገባውን የቡድን ቀጣይ ውጤታማነት ለመለካት ግልጽ መንገዶች መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ የቡድኑን ውጤታማነት የሚለካትበት መንገድም በግልፅ መፃፍና ለሁሉም የቡድኑ አባላት ለውይይት መቅረብ አለበት፡፡

ለ. **አመለካከት:-** አመለካከት የቡድኑ አባላት ከተሳትፏቸው ጀርባ ያሉትን ምክንያቶች በመለየት ቡድኑ ከተቋሙ ጋር ያለው ውህደት ምን እንደሚመስል ጠቋሚ ነው፡፡ የቡድኑ አባላት ማወቅ ያለባቸው ጉዳይ ቢኖር ከተቋሙ ግብ ጋር ራሳቸውን ማግባባታቸውን ነው፡፡ አባላቱና ቡድኑ በአጠቃላይ ከድርጅቱ ስትራቴጂ በተጨማሪም ከጠቅላላው እቅዶችና የስኬት ግቦች፣ ተልዕኮች፣ መርሆች፣ ራዕዮችና እሴቶች ጋር ግንዛቤያቸውን ማጣጣም አለባቸው፡፡

ሐ. **ቁርጠኝነት:-** በዚህ ሂደት የቡድኑ አባላት በቡድኑ ውስጥ በመሳተፍ ተልዕኮውን የማየትና ለመተግበር ፈቃደኛ መሆን አለባቸው፡፡ ራዕይ በሰራተኞች ውስጥ ሊሰርፅ፤ ሊጋሩትና ገቢራዊ ሊያደርጉት ግድ የሚላቸው ነው፡፡ የቡድኑ ህልምና የትኩረት አቅጣጫም ሌሎች ሰዎች እንዲጋሩት የሚያደርጋቸው ፍላጎታቸውን የሚያነሳሳና ሊከተሉት የሚሹት እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያትም የአመራሩ ራዕይ

selecting team members, empowering team members, providing training in relevant skills and knowledge, developing shared goals, and facilitating team functioning - particularly in the early stages of the team's work.

Effective teams are carefully designed. When assembling a team it is very important to consider the overall dynamics of the team. A scholar identifies five dynamics that are fundamental to team success. The first dynamic is team membership. Successful teams are made up of a collection of effective individuals who are experienced, have problem solving ability, are open to addressing the problem and are action oriented. Second is team relationship which has to do with the ability of team members to give and receive feedback. The third dynamic is team problem solving which implies that team effectiveness depends on the level of focus and clarity of the goals of the team. Fourth is team leadership. Effective team leadership depends on leadership competencies. A competent leader is focused on the goal, ensures a collaborative climate, builds confidence of team members, sets priorities, demonstrates sufficient "know-how" and manages performance through feedback. Organizational environment is the fifth dynamic of team success and it has to do with the climate and culture of the organization being conductive to team behavior.

Several authors have come up with ways of developing effective teams. While there is no best way to design, develop and support highly effective teams, it has been tried to summarize the major components of effective team building as:

**A. Clarity of Expectations and Objectives:** For team building to be effective the objectives must be specific, measurable, achievable, and relevant and have a time frame, in short must be SMART. As much as possible, input from all members must be included in the design and wording of the goals. All expectations must be clearly stated and this must be clearly understood by team members who must also understand the reason for the creation of the team. There must be clear means of measuring the ongoing effectiveness of the team which should be written down for eventual communication to and discussion with all team members.

**B. Perspective:** Perspective has to do with team members understanding the reasons behind

ከድርጅቱ ከተፃፉት መግለጫዎችና ራዕዮች በላይ የመሻገርና ከሥራ ቦታ ተግባራት፣ እምነቶች፣ እሴቶችና ግቦች በበለጠ የመስረፅ ብቃት ስላለው ነው። የሰራተኞችን ለማነቃቃትና ራዕዩን የራሳቸው እንዲያደርጉት የትኩረት አቅጣጫውና የራዕዩ ዓላማ በግልፅ ሊጠቀስ ይገባል። ጥንካሬው፣ ባህሉ፣ እሴቶችና የተቋሙ ቀጣይ እቅዶችም ይፋ መደረጋቸው አስፈላጊ ነው፡፡

የቡድኑ አባላት የቁርጠኝነት መጠን አብዛኛውን ጊዜ የቡድኑ ምርጫ ላይ፣ በአስፈላጊነቱ ላይ ባለው እምነት፣ ለአባላቱ በሚሰጣቸው ቦታ፣ ተግዳሮቶች፣ መጓጓት፣ ተስፋና እውቅና ላይ የተመረኮዘ ነው። ለቡድኑ አባላት አመቺ የሆነ ከባቢ መፍጠር የቡድኑን የሥራ አፈፃፀም ከማሻሻል  ባለፈም ብልሹ ፀባይን ይቀንሳል፡፡

መ. **ችሎታ፡-** ለውጤታማነት መሳለጥ ያመች ዘንድ፣ የቡድኑ አባላት ውስጥ ያሉት ተሳታፊዎች በጉዳዩ ላይ አግባብነት ያለው አስፈላጊውን እውቀት ስለመገብየታቸው፣ ክህሎትና ብቃት እንዳላቸውና ቡድኑ የተቋቋሙበትን ጉዳይ ብሎም እያንዳንዱ የቡድኑ አባላት በጋራ መሥራት የሚያስችላቸው ክህሎትና የተሳካ ተግባቦት፣ ግጭትና ችግር አፈታት ዘዴዎችን እንዲያውቁ ሥልጠና እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡ የሰው ሀብት ሥልጠናና ልማት ተግባራት ሰራተኞች አዳዲስ ኃላፊነቶችን እንዲወጡ ብቁ ያደርጋቸዋል፡፡ የቡድን አባላት በቂ የሥራ ችሎታ እና ዕውቀት ከሌላቸው ቡድኖች ውጤታማ የመሆን ዕድላቸው አነስተኛ ነው ፡፡

their participation on the team and how the team fits within the organization. Team members need to know not only where their team fits but how the team strategy fits in the total scheme of plans and success goals, mission, goals, principles, vision and values.

C. **Dedication:** This involves the willingness of team members to participate on the team and seeing their mission as important. Visions must be shared with employees in ways that compel them to act. The dream and direction of the team should be presented in such a way that other people want to share and follow. This is because the leadership vision goes beyond written organizational mission statements and vision statements to permeate the workplace and manifest in the actions, beliefs, values and goals of leaders. To excite and motivate employees to buy in the vision, the direction and purpose of the vision should be clearly set; the peculiar strengths, culture, values, beliefs and direction of the organization must be reflected.

The level of dedication of team members is usually dependent on factors like team choice; belief in the importance of the team; team members feeling valued; challenge, excitement and opportunity; as well as recognition. Appropriate environment for team success improves team performance, and reduces dysfunctional behavior.

D. **Capability:** For effectiveness to be achieved, there is need for the team to feel that participants are appropriate and that its members either possess requisite knowledge, skills and capabilities to address the issues for which such teams were formed or have access to needed help. The team members may need training to learn new skills which allow them to work together effectively, such as effective communication, conflict resolution and problem solving skills. Training and development allows them to take on new responsibilities. Where team members possess inadequate work skills and knowledge, teams are less likely to succeed.

ሠ. **የኮንትራት፡-** ውሉ ቡድኑ የተሰጠውን የኃላፊነት ቦታ ተቀብሎ ይህንኑ ለማሳካት የራሱን ተልእኮ፣ ራዕይን እና ስትራቴጂዎችን መንደፍ ያካትታል፡፡ ስለሆነም ቡድኑ ግቦቹን በግልጽ ማብራራት እና ማስተላለፍ አለበት፡፡ የሚጠበቁ ውጤቶች እና አበርክቶዎች፣ የጊዜ ሰሌደ፣ እና የሥራውን ውጤቶች እና ቡድኑ ኃላፊነቱን በሚወጣበት ወቅት ያለፋባቸው ሂደቶች የሚገመገምበትን ስልትም በግልጽ መስፈር ይኖርባቸዋል፡፡

ረ. **ሀብቶች፡-** የቡድን አባላት የተገለጸውን ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስፈልጉ ሀብቶች፣ ስትራቴጂዎች እና ድጋፎች እንዳሉ ሊሰማቸው ይገባል፡፡ ቡድኖች ውጤታማ እንዲሆኑ እንደ ገንዘብ፣ ጊዜ፣ መሣሪያ፣ ቴክኖሎጂ፣ ሰዎች እና መረጃዎች ያሉ ሀብቶችን ማግኘት ይፈልጋሉ፡፡ እነዚህን ሃብቶች ማቅረብም ከተቋሙ የሚጠበቅና ተዓማኒነቱን የሚያሳይበት ሲሆን የቡድኑ አባላት ደግሞ በኃላፊነት የመሥራትን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡

ሰ. **ሥልጣን፡-** ለቡድን ሥራ ውጤታማነት ቡድኖች ውሳኔዎችን የማድረግ ስልጣን ይፈልጋሉ፡፡ ስለሆነም ሥራቸውን በብቃት ለመፈፀም የተወሰነ የሥልጣን ደረጃ ለእነሱ አስፈላጊ ነው። የቡድን አባላቱ የኃላፊዎችን ቅቡልነት የማያገኙ ከሆነም፣ ሥራዎቻቸው በተግባር ሳይፈተሹም ሆነ ተፈትሸው ሃሳቦቻቸው ተቀባይነት ከማግኘት ውድቅ ሊደረጉባቸው ይችላል፡፡ ፈጠራ እንዲጎለብት ከተፈለገ የሥራ ቡድኖች በተግባር አንድን ነገር እንዲፈትሹ እንዲፈቅድላቸው ማድረግ ግዴታ ነው፡፡ ይሁንና በቡድኑ አባላት መካከል ግልፅ የሆነ እርስ በርስ የመናበብ መስመር ሊበጅለት ግድ ነው፡፡ ይህ ፍሬ እንዲያፈራም ማኔጅመንት ላይ ያሉት ኃላፊዎች አባላቱ ብቁ፣ ውጤታማ፣

E. **Contract:** Contract involves the team taking its assigned area of responsibility and designing its own mission, vision and strategies to accomplish the mission. Consequently the  team must

ጉልህ አበርክቶት የሚያሳርፉና ደስተኛ የሚሆኑበትን ምቹ የሥራ ከባቢ እንዲፈጠር መትጋት ግዴታቸው ነው፡፡

ሸ. **ትብብር፡-** ይህ ከቡድኑ አባላት ጋር የቡድን እንቅስቃሴን እና የቡድን ሂደቶችን ከመረዳት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የቡድን ግንባታ ደረጃዎችን፣ እንደቡድን አባላት ያላቸውን ሚና እና ሃላፊነቶች በመረዳት በግለሰቦች ደረጃ ውጤታማ በሆነ መልኩ አብሮ መሥራት መቻል አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ትብብሩ ቡድኑን ለችግር አፈታት፣ ለሂደት ማሻሻያ፣ ለግብ ማጣያ እና ልኬት በጋራ መሥራት መቻልን ያጠቃልላል፡፡ እንደ ግጭት አፈታት፣ የጋራ መግባባት ውሳኔ እና የስብሰባ አመራር ባሉ የቡድን ደንቦች ወይም የስነምግባር ህጎች የድርጊት መርሃ ግብሩን ለማሳካት ተገቢውን ስትራቴጂ በመጠቀም በቡድኑ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

ቀ. **ተግባቦት፡-** ውጤታማ የሆነ የቡድን ግንኙነት በአባላቱ መካከል በሚከናወኑት ክንውኖች ላይ ቅድሚያ ተሰጥቶ ግልፀኝነት የሚንፀባረቅበትና ለግብረ መልስም ስልት የሚበጅበት ነው፡፡ ለሥራ አፈጻጸም የሚሰጡት ግብረ መልሶችና አስተያየቶች ግን በቀናነት መንፈስና የሌሎችን ሰዎች ሃሳብ በማክበር መቀበል አስፈላጊ ነው፡፡ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የሌሎችን ስሜት ላለመጉዳት በሚል ትችትና ሃሳባቸውን ከማቅረብ ሲያቅማሙ ይታያሉ፤ ምክንያቱም በአፀፋው ከሰዎች በኩል ራስን የመከላከል ጥያቄ ያቀርብብናል ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ግብረ መልስ ለማግኘት ራስን ለአስተያየት ዝግጁ የማድረግ ባህል ሊዳብር ይገባል፡፡ እንደዚያም ሆኖ ግን ግብረ መልስ ሁልጊዜም ትክክል ላይሆንም ይችላል፡፡ የግብረ መልሱን አስተማማኝነት የሚወሰነውም ከሌሎች ሰዎች ጋር አብሮ ሲፈተሽ ነው፡፡ አስፈላጊ የሆኑ የቢዝነስ መረጃዎችም በየጊዜው ከቡድኑ አባላት ጋር በሚደረግ ውይይት በግልፅና በታማኝነት መነሳትና የተለያዩ አመለካከቶች በጠረጴዛ ዙሪያ ማንሸራሸርም ይገባል፡፡ አስፈላጊ የሆኑ አለመግባባቶችም ተነስተው መፍትሄ እንዲሰጣቸው ያስፈልጋል፡፡

በ. **ፈጠራ የታከለበት መሻሻል፡-** የቡድን ግንባታ አስኳሉ ጉዳይ ለውጥና የመለወጥ ፍላጎት ብቻና ያም ፍላጎት እውነተኛ የሆነ ብቻ መሆኑ ሳይሆን፣ እሴታዊ ፈጠራና አስተሳሰብ የታከለበት፣ በአይነታቸው ለየት ያሉ መፍትሄዎች የሚሰጡበት እንዲሁም አዳዲስ ሃሳቦች የሚመነጩበት ብሎም ካለው ነባራዊ የሥራ ከባቢ ጋር የተስማሙትን ሳይሆን ምክንያታዊ የሆነ አደጋን የሚያስከትሉ የቢዝነስ አሰራሮችን በድፍረት የወሰዱ ባልደረቦችን መሸለምን በማዕቀፉ ውስጥ ያካትታል፡፡

አዳዲስ እሳቤዎችን የሚያጭሩና የሚያነቃቁ በቂ የሆኑ ምቹ መደላድሎች በሰው ኃይል ልማት ሥራ ሂደት ውስጥ ህልውናቸው መረጋገጥ አለበት፡፡ የሰራተኞችን ሃሳቦች መዳሰስና ፈጠራ የሚንፀባረቅባቸውን አስተሳሰቦች ጎልተው እንዲወጡ ማበረታታት ለረጅም አመታት የተሰራባቸው ዘዴዎች ናቸው። አዳዲስ አስተሳሰቦችን በንባብ ለመቅሰምና ባልደረቦች ለሚያመጧቸው አስተሳሰቦች በይፋ እንዲወጡ አድናቆት እንዲቸራቸው ለማድረግ በቂ የሆነ ጊዜ ሊመደብላቸው ያስፈልጋል፡፡

define and communicate its goals; its anticipated outcomes and contributions; its timelines; and means of evaluating both the outcomes of its work and the process the team followed in accomplishing tasks.

**F. Resources:** Team members must feel that the resources, strategies and support needed to accomplish the stated mission are available. Teams need access to resources such as money, time, equipment, technology, people and information for them to operate effectively. Providing the resources depends on trust on the part of the organization and responsibility on the part of the team members.

**G. Power:** For effectiveness teams need authority to take decisions. Consequently a certain level of empowerment is necessary for them in order to carry out their work efficiently. Without this authority they would need to get approval for their ideas and these ideas may be rejected before they are either proven or not proven. For innovation to occur, teams must be allowed to experiment. However, there must also be a clear understanding of boundaries by team members. To achieve this management must create a work environment in which people are empowered, productive, contributing, and happy.

**H. Cooperation:** This has to do with the team members understanding team dynamics and group processes. They must understand the stages of group development, their roles and responsibilities as team members and be able to work together effectively at the interpersonal level. Cooperation also involves the team being able to approach problem solving, process improvement, goal setting and measurement jointly. Group norms or rules of conduct in areas such as conflict resolution, consensus decision making and meeting management must be established by the team using an appropriate strategy to accomplish its action plan.

**I. Communication:** Effective team building involves clarity about the priority of team member's tasks with an established method for the teams for feedback. Feedbacks must however be received with grace and dignity bearing in mind that people hesitate to give feedback to others out of fear of hurting them or having to deal with defensive or justifying behavior.

ተ. **ኃላፊነትና ተጠያቂነት:-** ለሰራተኞች እውቅና መስጠት ሁነኛ የሚባል ማነቃቂያ መንገድ ቢሆንም ቅሉ፤ በብዙ ድርጅቶች ግን ይህ እውነታ የታፈነና በብዙ ሰበቦች ገቢራዊ የማይደረግ ነው፡፡ ይህም ጊዜ እየገፋ በመጣ ቁጥር የሥራ ባልደረቦችን የሚያስከፋ፣ በሥራቸው ደስተኛ እንዳይሆኑ ከማድረግ አልፎም ተርፎ ተጠራጣሪዎችና ቅሬታን የሚያቀርቡ ወደመሆን ጠርዝ የሚገፉቸው ነው፡፡

የቡድን አባላቱ ኃላፊነትና ተጠያቂነት በሞላበት መልኩ ለስኬት እንዲሰሩ ከእነሱ ይጠበቃል፡፡ የተቋም ሰራተኞች ቅጣትን እንዲፈሩ ከማድረግ ይልቅ የቡድኑ አባላት ምክንያታዊ የሆነ አደጋን ተጋፍጠው ስኬታማ ሲሆኑ ሽልማቶችና ማበረታቻዎች መበርከት አለባቸው፡፡ አባላቱ ለችግሮች መላ በማፍለቅ እንጂ እርስ በርስ ጣት በመቀሳሰር ጊዜያቸውን በከንቱ ማባከን የለባቸውም፡፡ የሽልማት ስርዓቶችም የግለሰቦችንና የቡድኖችን የሥራ አፈፃፀም ባማከለ መልኩ እንዲሰጡ ተደርገው መቀረፅ አለባቸው፡፡ ለሽልማቱ አሰጣጥ የሚረዱ ግልፅ የሆኑ አሰራሮች ተዘርግተው እነዚህን መመዘኛዎች/መስፈርቶች ያሟላ ማንኛውም ሰው የእውቅናው ተጋሪ መሆን አለበት፡፡ ይህ ሲባል ግን የሰራተኛ እውቅና አሰጣጥ መንገዶችና በመዘርዝሩ ውስጥ መካተት ያለባቸው ጉዳዮችም የተለያዩ እንዲሆኑ ያስፈልጋል፡፡

የሰራተኛ እውቅና አሰጣጥ አስተማማኝ በሚባል ደረጃ ፍትሃዊ ሆኖ ነገር ግን የግድ እንደ መብትና ሹመት የሚጠበቅ መሆን የለበትም። ስለዚህም የሚሸለሙትና እውቅና የሚያገኙት አባላት በየወቅቱ የተለያዩ ቢሆኑ ይበረታታል፡፡ እውቅና መስጠት ጠንካራ ከሚሰኙት የግብረ መልስ አይነቶች ውስጥ ይጠቀሳል፡፡ በወቅቱ የሚደረግ እውቅና አዎንታዊ የሆኑ ስሜቶችን በማስፋፋት፤ በሥራ ገበታቸው ላይ ባላቸው ብቃት የራስ መተማመንን እንዲያዳብሩ በማድረግ በኩል በጎ አበርክቶ አለው፡፡

ቸ. **ማጣጣም:-** ማጣጣም ቡድኖቹ ከአንድ የአመራር ማዕከል ከሚሰጠው አመራር ጋር ተስማምተው እንዲሄዱና እግረ መንገዳቸውንም ለስኬት የሚያበቋቸውን ቁም ነገሮች የሚገበዩበት ነው፡፡ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በእቅድ ውስጥ ማካተትና የተለያዩ ሃብቶችን በየሥራ ክፍሎቹ መመደብ በዚሁ ሥር የሚካተት ነው፡፡ እርስ በርስ የሚጋሯቸው ኃላፊነቶች ያሏቸውና የባለብዙ የሥራ ክፍል ቡድኖች በጋራ ሆነውና ተቀናጅተው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ ማኔጀሮችና ተቆጣጣሪዎች የቡድን መሪዎች ሆነው መሥራት ሲጀምሩ፤ እንደአሰልጣኝና መንገድ ጠቋሚ አማካሪ ሆነው ከመሥራት ባለፈ በቀጥታ ማዘዝና መቆጣጠር ስለማይችሉ ከፍተኛ የሆነ የሚና ለውጥ በቡድኖቹ ውስጥ ለማየት ይቻላል፡፡ ውጤታማ የሆነ ግንኙነት፣ አመራርና ማማከር ክህሎቶች ስለሚያስፈልጉ በስልጠና ራስን በማሳደግና የአስተሳሰብ ሽግግር በማድረግ እነዚህን ክህሎቶች መገብየት ይገባል፡፡ የቡድን መሪዎች ሥልጣናቸውን (ኃላፊነታቸውን) ስለማጣት ቢሰጉም አዲሱ የሥራ መደባቸው ግን ከቡድኑ ስኬታቸው ጋር በቀጥታ የተሰናሰነ ስለሆነ እውቀታቸውን ከዚህ ቀደም ካለው በበለጠ መልኩ ተፈላጊ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ የሥልጣን መሸርሸርና ማነስ ሳይሆን፤ የሥልጣን ምንጩን ከህጋዊነት ይልቅ እውቀትን መሰረት ወደሚያደርግ ማሸጋገር ነው፡፡

To obtain feedback there should be openness to feedback. Nevertheless, it should be noted that feedback is not always right. The reliability of the feedback should be determined by checking with others. There should be important business information regularly with team members communicating clearly and honestly with each other and bringing diverse opinions to the table. Necessary conflicts must also be raised and addressed.

J. **Creative Improvement:** Teambuilding is about change and the interest in change must not only be real, it must value creative thinking, unique solutions, and new ideas while at the same time rewarding people who take reasonable risks to make improvements rather than those who fit in and maintain the status quo. There must also be adequate provision for necessary human resource development to stimulate new thinking. The process of reviewing employee ideas, and encouraging creative thinking from employees, has evolved over the years. Adequate time must be created to read about new ideas, revel in the creative thinking of staff and make changes.

K. **Responsibility and Accountability:** In spite of the obvious value of employee recognition, it is so closely guarded in many organizations and several reasons have been adduced for this including time and the fact that it often results in employee complaining, jealousy, and dissatisfaction. Team members need to feel responsible and accountable for team achievements. Rewards and recognition must be given when teams are successful with reasonable risk being respected and encouraged in the organization rather than team members fearing reprisal. Team members need to spend their time resolving problems not finger pointing and the reward systems must be designed to recognize both team and individual performances. Clear criteria for eligibility must be established and anyone who meets the criteria should be recognized. However, employee recognition approaches and content must also be inconsistent. Employee recognition should be consistently fair, but must not become expectations or entitlements. Inconsistency is therefore encouraged in the type of employee recognition given. Employee recognition is one of the most powerful forms of feedback.

ኘ. **የባህል ለውጥ፡-** ባህል ሁልጊዜም ቢሆን በሥራ ቦታ ላይ የሚኖር ሁኔታ ሲሆን በሥራ ደስተኛ መሆንንና የሥራ ግንኙነትንና ሂደቶችን የሚወስን ጠንካራ ግብዓትም ነው፡፡ ባህል እሴቶችን፣ እምነቶችን፣ አመለካከቶችና ባህሪያትንም አካቶ ይይዛል፡፡ ባህል አብሮ ለመሥራት የሚያስችልና ቅርፅ ይዞ፤ ባህሪና ልማድ ሆኖ መውጣት የሚጀምረውም ያልተፃፉና ያልተነገሩ በገቢር ግን በጣምራ ለመሥራት የሚያስችሉ ኹነቶች ሲከወኑበት ነው። የተቋም ባህል የሚዋቀረው እያንዳንዱ የተቋሙ ሰራተኞች ያላቸው የህይወት ልምድ ተቀምሮ ወደ ተቋሙ ሲዋሃድና መሥራት ሲጀምር ነው፡፡ በተለይም የተቋማት መሥራቾች፣ ሥራ አስፈፃሚዎችና ሌሎችም በአስተዳደር ደረጃ ላይ ያሉ ባልደረቦች በውሳኔ አሳጣጥና ስልታዊ አቅጣጫ በመንደፍ ያላቸው ኃላፊነት ሄዶ ሄዶ የተቋሙ ባህልም ላይ ረቂቅ አሻራውን ያሳርፍበታል፡፡

ባህል በቋንቋ፣ በውሳኔ አሰጣጥ፣ በምልክቶች፣ ታሪኮችና አፈ-ታሪኮች እንዲሁም በእለት ተዕለት የሥራ ልምምዶች ውስጥ ይንፀባረቃል፡፡ የተቋም ባህልም እያንዳንዱ የተቋሙ ሰራተኛ ባለው የህይወት ልምዶች የሚገነባ ነው፡፡ ቡድን ላይ የተመረኮዘ፣ ትብብር ያለበት፣ አቅምን የሚገነባና አስቻይ የሆነ ተቋማዊ የወደፊት ባህል፤ ከጥንቱና ተዋረዳዊ ከሆነው ተቋም ጋር በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ ስለዚህ በአሁኑ ዘመን ያሉ ተቋማት ለሰራተኞቻቸው የሚሰጡት የእውቅናና ሽልማት ሥርዓታቸውን፣ የግምገማና ምልመላ፣ መረጣ፣ ልማት፣ እቅድ፣ ማነቃቂያና አስተዳደራቸውን የማሻሻል ሂደት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡ ተቋሙ ለሰራተኞቹ እየተመቸና ድጋፍ እያደረገላቸው በመጣ ቁጥር፣ የተሻለና የተቀላጠፈ የሥራ ሁኔታን ከቡድኑ አባላት እያገኘ ይመጣል፡፡

## 7. በቡድን የመሥራት ጠቀሜታዎች

በኅብረት የመሥራት ጠቀሜታዎች በየተቋማቱ ባሉ እንደተቋም ባህልና የሥራው ሁኔታ፣ የአመራር ውጤታማነት ደረጃን በመሳሰሉ መለኪያዎች ምክንያት ከቦታ ቦታ የተለያዩ ባህሪያት አሏቸው። ታላቅ የሚባሉት ቡድኖች ከምንም ነገር በተሻለ መልኩ ትልቅ ስኬቶች በአንድ ድርጅት ውስጥ እንዲመዘገብ ያደርጋሉ፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ቡድኖች የሰው ኃይል አጠቃቀምን በማሻሻል ተቋማት የግለሰቦችን እውቀትና ክህሎት አሟጠው እንዲጠቀሙ ያደርጋሉ፡፡ ይህም የሥራ መሰባጠርን በማበራከት ማኔጀሮች (አስተዳዳሪዎች) ስለእያንዳንዱ የመስሪያ ቤቱ ክፍሎች እንዳያውቁና ከዚያ ይልቅ ባልተማከለ ሁኔታ የሰራተኞች እውቀትና ክህሎቶች በተቋማቱ እንቅስቃሴ ውስጥ በመግባት የተቋሙ አንቀሳቃሽ ሞተር እንዲሆኑ ያስችላሉ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ፣ ቡድኖች የተቋምን አዳዲስ ስትራቴጂዎችን በመቅረፅና በተግባር በመፈተሽ ምርጥ የተባለውን ለሥራቸው ስለሚያውሉ የተቋሙ የእውቀት መፍለቂያ ምንጮች ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ቡድኖች በመጣመር (መደመር) አሰራር ውስጥ ሆነውም የግለሰብ ምርታማነት ላይ በጎ አሻራቸውን ያሳርፋሉ፡፡ ከፍተኛ ደረጃ በሥራ ደስተኛ መሆን፣ ማነሳሳትና ግለሰቦች በበርካታ ሥራዎች እንደመጠመዳቸውም እነሱ በቁርጠኝነት መንፈስ እንዲሰሩ የማድረግ ተግባራትም የቡድኖች ትከሻ ላይ የተጣለ ተግባር ነው፡፡ እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው

Timely employee recognition enhances positive feelings and positively affects confidence in their ability to do well in the workplace. one of the most powerful forms of feedback. Timely employee recognition enhances positive feelings and positively affects confidence in their ability to do well in the workplace.

L. **Harmonization:** Harmonization involves the synchronization of teams by a central leadership team that assists the groups in obtaining what they need for success. It involves the planning of priorities and resources allocation across departments. Cross-functional and multi-department teams should be coordinated to work together effectively. Managers and supervisors who become team leaders experience a significant change of role because team leaders do not direct or control work, but instead work as coaches and mentors. Effective communication, leadership and consulting skills will be required which may necessitate training and development. A new mindset is also required. Team leaders concerned with a loss of power need to understand that their new role is pertinent to the success of the teams, and that their knowledge is required now more than ever. The issue is therefore not about the erosion of power, but a shift in the source of power from legitimate to knowledge based.

M. **Cultural Change:** Culture is the environment that surrounds a workplace at all times. It is a powerful element that shapes work enjoyment, work relationships, and work processes. Culture involves the values, beliefs, underlying assumptions, attitudes, and behaviors shared by a group of people. It is the behavior that results when a group arrives at a set of - generally unspoken and unwritten - rules for working together. An organization's culture is made up of all of the life experiences each employee brings to the organization. Culture is especially influenced by the organization's founder, executives, and other managerial staff because of their roles in decision making and strategic direction. Culture is reflected in language, decision making, symbols, stories and legends, and daily work practices. An organization's culture is made up of all of the life experiences each employee brings to the organization. The team-based, collaborative, empowering, enabling organizational culture of the future is different from the traditional,

ጠቀሜታዎችም በውጤታቸው ዝቅተኛ የሚባሉ የሰራተኞች ከሥራ መልቀቅንና መቅረትን ከመቀነስ ሌላም ሥራዎች እንዲቀላጠፉ ለማድረግና ተቋማት ለሥራዎች ማስፈፀሚያ የሚያወጡትን ወጪ በመቀነስ ስለመሥሪያ ቤቱ ቀና አስተሳሰብን በማዳበር በእውቀት መመራትን ያስገኛሉ፡፡

## 8. በቡድን የመሥራት ጋሬጣዎች

በቡድን መሥራትን መሬት ላይ በማውረድ መተግበር መሰረታዊ በሚሰኝ ደረጃ የተቋማት ለውጥና ልማት ሂደት ዋና ክፍል ነው፡፡ ስለዚህም ቡድኖች በዚህ የለውጥ ሃዲድ ውስጥ ሲጓዙ ለችግሮችም የተጋለጡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ከማይግባባውና ከዚህ ቀደም ከማያውቀው ሰው ጋር በጣምራ እንዲሰራ ሲደረግ ይህንን ለውጥ ስለሚቃወመው ይኼም በራሱ ችግር ሆኖ ብቅ ይላል፡፡

ግልፅ የሆኑና ገደባቸው የሚታወቅ ግቦችን መጋራት ጠቃሚ ቢሆንም፤ ቡድኑ ጥርት ያሉና የሚገቡ ግቦችና ተነሳሽነቶችን የማይጋራበት እድልም ይኖራል፡፡ ይህም በውሳኔ አሰጣጥ ላይ እግር ጉተታን በማስከተል ጊዜን ያባክናል፡፡ "በቡድን ከማሰብ" የሚነሱ ችግሮች የሚከሰቱበትና ምናልባትም በውሳኔ አሰጣጥ ላይ አስጊ የሆነና የተካረረ ግጭትም ሊከሰት የሚችልበት እድል ዝግ አይደለም፡፡ በዚህ ወቅት በቂ የሆነ የቡድን ሥልጠና ካልተሰጠና ዝግጅትም ካልተደረገ በስተቀር ቡድኖች በጋራ የተሰነቀውን ራዕይ እውን ለማድረግ የሚተጉበትና ውጤታማ የሚሆኑበት እድል የመነመነ ነው፡፡

ከተግባቦት እጥረት፣ ከግለሰብ ግጭት፣ ሰጥቶ በመቀበል ላይ በጣሙን ጥገኛ የሆነ ግንኙነትም ከችግሮቹ ውስጥ የሚመዘዙ ናቸው፡፡

ቡድን በመገንባት ሂደት ውስጥ ዋናው ስጋት አንድ የቡድን አባል ስለተቋሙ ተጠራጣሪና ጨለምተኛ አስተሳሰብ ሊኖረው መቻሉ ነው፡፡

ቡድንን የመገንባት ኹነቶች ተግባራዊ በሆነና ትርጉም በሚሰጥ የሥራ ላይ ልምምድ እንዲደገፉ ያስፈልጋል፡፡ የቡድን አባላት ከቡድን አወቃቀር ጋር ተያይዞ በተቋሙ ውስጥ ምንም መሻሻል ማየት ካልቻሉና ለውጥ ከሌለ ይህንን እንደጊዜ ማባከን ስለሚቆጥሩት፣በተቋሙ ላይ ያላቸውን እምነት ከመሸረርሸር ባለፈ ለሥራ የመነሳሳት መንፈሳቸውን የሚጎዳና ሞራልና የሥራ ውጤትንም የሚቀንስ ይሆናል፡፡

ሌላው በቡድን ውስጥ የሚፈጠር ችግር ቢኖር ቡድኖች ውሳኔዎችን ለመስጠት እምነት በማጣታቸው ምክንያት ተቋማቸው ሙሉ አቅማቸውን መጠቀም ሳይችል ሲቀር ነው። ውሳኔ ከመሥጠት በፊት አባላቱ ፈቃድ የሚጠይቁ ከሆነ የጊዜ መጓተትን ከማስከተሉ ሌላም የባለቤትነት ስሜትን ያጠፋል፡፡

ቡድኖች የማያምኑባቸውን መፍትሄዎችን እንዲሰጡ ሲገደዱም የፈጠራ አቅማቸው ይሸመደመዳል፡፡ ጥቂቶች ምክረ ሃሳብ ሲያቀርቡ እንደሚሉትም በጥምረት የሚሰራ ሥራ የጋራ አመራር ይፈልጋል፡፡ የቡድን ሥራ አፈፃፀም ደግሞ የሥራ ነፃነትንና ሥልጣንና ኃላፊነትን በማከፋፈል መካከል ሚዛናዊ መሆንን እንዲሁም ለሥራ

hierarchical organization. Therefore contemporary organizations must either be in the process of or have plans of changing systems of rewards, recognition, appraisals, recruitment, selection, development, planning, motivation and management of the people it employs. The more an organization can change its climate to support teams, the more it will receive in pay back from the work of the teams.

## 7. The Prospects of Teamwork

The prospects of teamwork may vary for across organizations because they are dependent on several factors, like the culture and climate, effectiveness of team leadership, and the organization. Great teams make things happen more than anything else in organizations. First, teams optimize the use of human resources by allowing organizations to gain access to individual knowledge and skills. An implication of increased complexity is that managers can no longer know everything about all aspects of organization operations and it is essential that the knowledge and skills of the workforce be utilized. Second, teams enhance organizational learning because employees are able to experiment and create strategies that are best suited to their work. Teams can create a synergy by bring about gains in individual productivity and efficiency. They also brings about increased levels of job satisfaction, motivation and employee commitment since they are associated with a greater variety of tasks and added responsibility for team members. The resultant effects of this include reduced staff turnover and absenteeism and consequently reduction in organizational costs and improved organization memory or knowledge base.

## 8. Impediments and Challenges to Teamwork

The implementation of teams is, fundamentally, an organizational change and development process. Teams are, therefore, susceptible to all the challenges that can occur during any organizational change process. In particular, employee resistance may result where employees are required to work with other employees with whom they are unfamiliar. The team may not share clear goals or purposes, and therefore as earlier discussed defining specific goals is very important. The time trade-offs in decision making. There may be problems of "groupthink" and pressure to conform as well as the potential for increased conflict over

በሁኔታዎች ውስጥ በተለዋዋጭ አሰራር መመራትን ጨምሮ በአንድ ማዕከል ደረጃ ለመቆጣጠር እንዲቻል ማድረግንና ቅንጅትና ተገማችነትን ማስፈንንም አስተሳስሮ መሄድ እንዳለበት ልብ ይሏል።

በሥራና በቤት ህይወት መካከል ሚዛናዊ ሆኖ መገኘት፤ ተቋማት ባልተሰናከለና ጥቂት ችግሮች ባሉበት መንገድ እንዲመሩ ይደርጋል፤ በተለይም ከፍተኛ ቅሬታ በሚነሳበት ወቅት የማማከር ብሎም ጭንቀትንና ግጭቶችን ከመቀነስ ባለፈም የህግ ክስ ሂደትን ለመለየት ይረዳል፡፡ ከሥራ የሚወጡት መበራከታቸው ደግሞ በቀጣይነት ቋሚ የሆኑ እቅዶችን የማዘጋጀት፣ የድርጅቱን ክብርና በጎ ገፅታ የማስከበር ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚያደርጉ ይታመናል፡፡

በማኅበራዊ ደረጃ የተጠያቂነት መንፈስ የማይታይባቸውን ሰዎች በቡድን ማደራጀትም የቡድኑን መርሃ ግብሮች ከማፋለስ በተጨማሪም አፈፃፀማቸውን ደካማ ያደርጋል፤ የአስተዳደር ኹነት መዘባረቅን ያስከትላል፤ ከሥራ የሚለቁት ባልደረቦችን ቁጥር ያንራል፤ በፍርድ ቤት ክስ ሂደት የመጠየቅ ሂደትን ከማስከተል ባለፈም የድርጅቱን ገፅታ በሰዎች ዘንድ የጎደፈ ያደርገዋል፡፡

ማኅበራዊ ኃላፊነት የሚሰማው ሰራተኛ በጥንቃቄና በትጋት በመሥራት ከሥራ ጋር የተያያዙ ኹነቶች ውስጥ የሚከሰቱትን ከላይ የተጠቀሱትን አደጋዎች በመቀነስ መልካም የሆነ አሰራሩን/አሰራሯን ማሳየትና ማስመስከር ይገባዋል/ይገባታል፡፡ በመጨረሻም ሁልጊዜም ቢሆን በተለይም ተደላድለው የቆዩበት "የምቾት ቀጠናቸው" በ"ቡድን ግንባታ" ሂደት ከሚነካባቸውም ሆኑ ከሌሎች ሰራተኞች በኩል ለውጥ እንዲያመጣ የሚቋቋመው ቡድን ተቀናቃኝ እንደማያጣው ግልጽ መሆን አለበት፡፡ ይህም ከግንዛቤ ውስጥ ገብቶና እውቅና ተሰጥቶት እነዚህ ችግሮች የሚፈቱበት መርሃ ግብር ሊጤንበት ይገባል፡፡

## 9. ማጠቃለያ

ቡድኖች በተግባር እንዲሰሩ ማድረግና ድጋፍ መስጠት፣ መሰረታዊ የሆነ ተቋማዊ ለውጥንና የሚፈልግና በርካታ ጉዳዮችን ከግምት የሚያስገባ ነው፡፡ አንድ ድርጅት ከቡድኑ አባላት አንስቶ፣ ተቆጣጣሪዎች፣ አስተዳዳሪዎች፣ የተቋሙ አወቃቀር፣ ባህል፣ የሥራ ሂደቶች፣ የአሰራር ዘዴዎችና ማኅበራዊ ግንኙነቶቹ ለጉዳት የተጋለጡ ናቸው፡፡ የለውጦቹ ሥፋትና ጥልቀት በቡድን ውስጥ ያለው አተገባበርም ረጅም ሂደቶችን የሚያካትትና በብዙ ፈተናዎች የተሞላ ያደርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ ያለው ጥቅም ትልቅ የሚባል ስለሆነ በቡድን አሰራር ገቢራዊነት ላይ ያሉት ሰዎች ወደኋላ ተመልሰው የቀድሞውን አወቃቀር መቃኘት አይገባቸውም፡፡ ምንም እንኳን በርካታ ችግሮች ቢኖሩትም ውጤታማ የሆነ ቡድንን መገንባት ለተቋማት በርካታ ጠቀሜታዎችን ይሰጣል፡፡

decision making. Without adequate team training and preparation, it is unlikely that teams will work effectively to develop and realize a shared vision. There are also the challenges arising from lack of communication; personal conflict; overemphasis on give and take relationship.

A major risk of team building is that a team member may become cynical of the organization. Team building events must be complemented with meaningful workplace practice. Where team members do not see an improvement within an organization associated with team building events, they may view such events as a waste of time and this may consequently result in loss of trust in the organization, harm motivation, decrease employee morale and production.

Another problem is that which occurs when the teams are not trusted enough to make major decisions and consequently the teams and the organization to which they belong, are not reaching their full potentials. Seeking permission before implementing ideas reduces timeliness and ownership. Innovation is also reduced as teams are forced to suggest solutions that are likely to be accepted. Some suggest that coordination needs effective team leadership and team performance requires a balance between autonomy and decentralization of power on the one hand, for the sake of both motivation and flexibility, and centralized control on the other hand, for the sake of coordination and predictability. Fostering a healthy work and home life balance tends to make organizations run smoother and less problematically, especially in areas of grievance and counseling, stress and conflict, disputes and litigation, recruitment and staff retention, succession planning, company reputation and image. There are also the implications and risks of organizing socially irresponsible team events and activities which affect performance, management distraction, and staff retention; risks of litigation and bad publicity. A socially responsible employer should be able to demonstrate they have been duly careful and diligent in minimizing such risks when organizing any work events. Finally, there are always going to be those resistant to the very idea of "team building" or others whose comfort zone is very small. This must be acknowledged and program that takes it into account created.

## 9. Conclusion

Implementing and supporting teams in an organization, needs considerable organizational change and consideration of many issues. The entire organization ranging from the team members, supervisors, managers, the organizational structure, culture, work processes, methods, and social relationships are affected. The depth and scope of the changes implies that team building and implementation is a lengthy process presenting many challenges. However the benefits are enormous and those implementing teams have no plans to revert to their previous structures. Despite the challenges, effective teambuilding provides many benefits to organizations.

*"ወደ አንድ መምጣት ጅማሬ ነው፤ አብሮ መቆየት እድገት ነው፤ አብሮ መሥራት ስኬት ነው፡፡"*
*-ሔንሪ ፎርድ*

***"Coming together is a beginning;***
***Keeping together is progress;***
***Working together is success."***
***-Henry Ford***




## References


Argote, L. & McGrath, J.D. 1993, 'Group Processes in Organizations: Continuity and Change', International Review of Industrial and Organizational Psychology, vol. 8, C.L. Cooper & I.T. Robertson (eds), John Wiley &Sons, New York.

Brower, M.J. 1995, 'Empowering Teams: What, Why and How', Empowerment in Organizations, vol. 3, no. 1, pp. 13-25.

Fajana S. (2002) Human Resources Management: An Introductory, Lobefin and Company, Lagos. Field, S.W. & Swift, K.G. 1996, Effecting a Quality Change: An Engineering Approach, Arnold, London.

Heap, N. 1996, 'Building the Organizational Team', Industrial and Commercial Training, vol. 28, no. 3, pp.3-7.

Kirkman, B.L. & Shapiro, D.L. 1997, 'The Impact of Cultural Values on Employee Resistance to Teams: Toward a Model of Globalized Self-Managing Work Team Effectiveness', Academy of Management Review, vol. 22, no. 3, pp.730-757.

LaFasto, Frank M. J.; Larson, Carl (August 2001). When Teams Work Best. Thousand Oaks, CA: Sage.

Robbins, S.P. 1998, Organizational Behavior: Concepts, Controversies, Applications, Prentice Hall, New York. Roufaiel, N.S. &Meissner, M. 1995, 'Self-Managing Teams: A Pipeline to Quality and Technology Management, Benchmarking for Quality, vol. 2, no. 1, pp.21-37.

Thompson and Luthans (2006) Critical Issue: Building a Committed Team. NCREI Journal.
Retrieved February 10, 2012, from http:/www.ncrei.org/areas/issues/educatrs/leadership/lezoo.

Wilson, F. 1996, 'Great Teams Build Themselves', Team Performance Management: An International Journal, vol. 2, No. 2, pp. 27-31.

# በገበኮን የሰው ኃይል  ውጤታማነትን ለማጠናከር የሚያስችል ስልጠና ተሰጠ

# GEBECON Has Conducted Human Resource Capacity Building Training

የሰው ሀብት ልማት ለማንኛውም ድርጅት ውጤታማነት ወሳኝ መሆኑን ገበኮን በጽኑ ያምናል፤ ከዚሁ እምነት በመነሳት ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን የሰራተኞቹን ክህሎትና ዕውቀት ለማዳበር በየዓመቱ የተለያዩ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ለሰራተኞቹ እና ለሥራ ኃላፊዎች ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ በ2012 በጀት ዓመትም በተለያዩ ርዕሶች ላይ በየደረጃው ለሚገኙት የድርጅቱ የሥራ አመራሮች እና ሠራተኞች ሥልጠናዎችን በማዘጋጀት ሰጥቷል፡፡

በዚሁ መሰረት በፕሮጀክት ሥራ አመራር እና በኮንትራት አስተዳደር (Project Management and Contract Administration) ላይ 22 ለሚሆኑ የዋና መ/ቤት እና ለየፕሮጀክቶቹ የሥራ አመራሮች በዘርፉ የካበተ ልምድና ዕውቀት ባለው ባለሙያ ለሁለት ቀናት (ጳጉሜ 1 እና 2/2011 ዓ.ም) በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

GEBECON strongly believes that human resource development is critical to the success of any organization. Based on this belief, Gemshu Beyene Construction PLC has been providing various trainings to the workers and managers every year to develop the skills and knowledge of the workers. In the 2012 Ethiopian budget year, it provided trainings to various management and staff personnel of the organization on various topics.

Accordingly, 22 management staffs from Head Office and projects on Project Management and Contract Administration topics have been given for two days (on Sep 6 and 7, 2019) at Ellily International Hotel.



Training on Project Management & Contract Administration

በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ በሰው ሀብት አስተዳደርና አመራር ሥራ ላይ ለተሰማሩ 9 (ዘጠኝ) የዋና መስሪያ ቤትና ለፕሮጀክት  ሥራ አመራር ኃላፊዎችና ኦፊሰሮች በውስጥ አሰልጣኝ በሰው ሀብት ልማትና አመራር ላይ ባተኮሩ  አራት የሥልጠና ርዕሶች ላይ ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ በተጨማሪም ከዋናው መ/ቤት እና ከፕሮጀክቶች ለተውጣጡ 15(አስራ አምስት) ለሚሆኑ የቴክኒክ ባለሞያዎች በመሳሪያዎች ጥገና እና አያያዝ  ዙሪያ ትኩረት ያደረገ የሁለት ቀናት ስልጠና በውስጥ አሰልጣኝ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

At the same time and place, 9 (nine) Head Office and Project administration officers engaged in Human Resource Management activities were trained on four topics focusing on Human Resource Development and Management. Additionally training on construction machineries and equipment maintenance and handling for 15 (Fifteen) technicians from Head Office and Projects was provided for two days using in-house resource persons.



Training on Cons. Machinaries & Equipment Maintenance

ከላይ ከተጠቀሱት ስልጠናዎች በተጨማሪ ድርጅታችን የISO 9001፡2015 የሥራ አመራር ጥራት ሥርዓትን የሚከተል እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ በየጊዜው ለማጎልበት ይቻል ዘንድ የተሰጠ ሥልጠና ሲሆን፣ በዚህ ረገድ በ ISO 9001፡2015 የሥራ አመራር ጥራት ሥርዓት የውስጥ ኦዲት ላይ ያተኮረ ሥልጠና በዘርፉ በተሰማራ የግል ድርጅት አማካይነት ለሁለት ቀናት ከዋናው መስሪያ ቤትና ከፕሮጀክቶች የተውጣጡ 10 ሠራተኞች የተሳተፉበት የሥልጠና መርሃ ግብር ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

In addition to the above trainings, our company adheres to the ISO 9001-2015 Quality Management System, which is designed to enhance this on a regular basis. A training program was implemented with the participation of 10 staff from the Head Office and Project Offices.



Training on Human Resource Management

በአንድ ድርጅት ውስጥ በለውጥ የሚያምን አመራር እና ሠራተኛ መኖር የድርጅቱን ስትራቴጂካዊ ዕቅድ በተገቢው መንገድ በመምራትና በመፈጸም ወደ ግብ እንደሚያደርስ ሰልጣኞቹ የግንዛቤ ማዳበሪያ ዕውቀት እንዲጨብጡ የተደረገ ሲሆን፣ ለወደፊቱ ውጤታማ ለሚያደርጋቸው ተግባር መንገድ እንደሚጠርግላቸው ሠልጣኞቹ በአስተያየታቸው ገልፀዋል፡፡

At the end of the training the trainees indicated that having a change-oriented leadership and staff in an organization will lead to the realization of the strategic plan of the organization, which could be achieved through implementation of capacity building programs.



**Training on ISO 9001-2015 Quality Management System**

ዛሬ ዓለማችን በደረሰችበት ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመጓዝ በዕውቀትና በችሎታ የዳበረ ተወዳዳሪ የሰው ሀብት ሊኖር ይገባል፡ ፡ ይህንንም ወሳኝ ሀብት በየጊዜው ዕውቀቱንና ክህሎቱን እያጎለበቱ ይዞ ማቆየት እጅግ ተፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ለአንድ ድርጅት ዕድገት ወሳኝ የሆነው የሰው ሀብት በስልጠና ማጠናከር፣ የሠራተኞችን አያያዝና አስተዳደርን የበለጠ በማሻሻል ፍትሃዊ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን እና የሰው ሀብት አስተዳደር ሥርዓቱን በዘመናዊ ኢንፎሜሽን ቴክኖሎጂ በማገዝ የሰራተኛን ፍልሰት መቀነስ አስፈላጊ መሆኑ በስልጠናው ወቅት ተጠቅሷል፡፡

In order to be competitive in today's world, there must be a competent human resource that is developed in knowledge and skills. It is imperative that a company keep up with this vital resource by constantly developing its staff knowledge and skills. Therefore, it is important to strengthen the human resources capacity through training, further improve staff management system and employee handling, ensure fairness, transparency and accountability, and reduce labor turnover with the help of modern information technology.

*“ወደ ፊት ለመራመድ ራስህን አሻሽል.” -ቢ.ሲ. ፎርብስ*

***“To make headway, improve your head.” - B. C. Forbes***

# የገበኮን የ2011 የሥራ ዘመን አመታዊ የሠራተኞች ጉባኤ ተካሄደ
# 2012 EFY GEBECON Annual Staff Assembly Hel



**Ato Gemshu Beyene**
General Manager of the Company
Delivering Opening Speech
on Staff Assembly



ገበኮን ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ እንደልማድ ይዞት የቆየውና መላው የድርጅቱ ሠራተኞች በጉጉት የሚጠብቁት ኩነት ቢኖር፣ በየፕሮጀክቶቹ ተሰማርተው የሚሰሩትና በዋና መሥሪያ ቤት ያሉት ሠራተኞች በየዓመቱ የሚገናኙበት፣ ዓመታዊው የድርጅቱ ዓመታዊ የሠራተኞች ጉባኤ ነው፤ ይኸው የተለመደው መድረክም ጳጉሜ 03 ቀን 2011 ዓ.ም. በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል መላው የድርጅቱ አመራሮች፣ ሠራተኞች፣ ተጋባዥ እንግዶች እና የድርጅቱ አጋሮች በተገኙበት በደማቅ ሁኔታ ተካሄዷል። በመድረኩም የተለያዩ የድርጊት መርሃግብሮች የተስተናገዱበት ነበር።

በቅድሚያ የካምፓኒው ዋና ሥራ አስኪያጅና መስራች የሆኑት አቶ ገምሹ በየነ ለታዳሚዎቹ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት በማስተላለፍ መድረኩን በንግግር የከፈቱ ሲሆን፣ በንግግራቸውም ካምፓኒው ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ ብዙ ውጣውረዶችን በማለፍ ዛሬ ላይ መድረሱን አስታውሰው፣ በዓመቱ ውስጥ የተመዘገቡትን መልካም ውጤቶች እና ተግዳሮቶችን በመግለፅ ቀጣይ አቅጣጫንም አመላክተዋል።

Gemshu Beyene Construction (GEBECON) PLC, since its establishment has been colorfully marking its staff assembly every year. This is one of the annual events anticipated with excitement among all staff. The even brings together company staff from across projects and from head office. Accordingly, GEBECON has colorfully held its annual assembly of staff members on September 08, 2019 at Elilly International Hotel in the presence of invited guests and company business partners.

Founder and General Manager of the Company Mr. Gemshu Beyene has welcomed the guests in his opening speech of the event and recalled that the company has come long rough way to present. He also highlighted some of the successes and challenges faced during the year and indicated future directions.

ከስኬቶቹ መካከል በዋናነት ድርጅቱ ቀደም ሲል አጋጥሞት በነበረው ሰው ሰራሽ ችግር ምክንያት ደርሶበት ከነበረው ጉዳት በማገገም ህልውናውን ዳግም በማስጠበቅና በማፅናት ለሠራተኛውም የሥራ ዋስትና ማረጋገጥ መቻሉ እንደሆነ አንስተዋል፤ በማያያዝም የአዘዞ-ጎርጎራ መንገድ ፕሮጀክትን ሙሉ በሙሉ በማጠናቀቅ ማስረከብ መቻሉን፣ እንዲሁም የመሀል ሜዳ-ዓለም ከተማ የአስፓልት መንገድ እና የአርሲ ዩኒቨርስቲ ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶችን አጠናቅቆ ለርክክብ ማብቃት እንደተቻለ በመግለጽ ስኬቱ የሁሉም የካምፓኒው ማህበረሰብ ርብርብና የጥረት ውጤት መሆኑን በማብሰር ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በማያያዝም በተለይ የመሀል ሜዳ-ዓለም ከተማ የአስፓልት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ብዙ ውስብስብ የሆኑ ችግሮች የነበረበት መሆኑን ጠቅሰው ከሥፍራው መልከኣምድራዊ አቀማመጥ አስቸጋሪነት፣ ከመሬቱ የመንሸራተት ባህሪይ እና ከዲዛይን ግድፈት የሚመነጩትን ችግሮች ለመፍታት ድርጅቱ በራስ ተነሳሽነት ከውጪ ባለሙያ እስከመቅጠር ድረስ ጥረት እንደተደረገ ገልጸዋል፤ የዲዛይን ክለሳም ከግንባታ ዘርፍ ከሚጠበቅ ሙያዊ ሥነምግባር በመነጨ አኳኋን በቀጣሪው አካል እንዲደረግ ባቀረብነው ምክረሀሳብ መሠረት ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ የአሰሪውን ወጪ ማዳን የተቻለበት፣ ከአራት በላይ ሥራ አስኪያጆችና ከአምስት ያላነሱ ተጠሪ መሐንዲሶች የተፈራረቁበት እና ብዙ ዋጋ ተከፍሎበት ለዚህ ደረጃ ማድረስ በመቻሉ፣ በተለይ ደግሞ ይህ ፕሮጀክት ከሁሉም የመንገድ ፕሮጀክቶች ሁሉ በአትራፊነቱ ብቸኛ ሆኖ መገኘቱ ለተቀሩትም መልዕክት የሚያስተላልፍ በመሆኑ የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽ፣ የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ለአቶ ሄኖክ መብራቴ፣ ፕሮጀክቱን በቅርበት ሲከታተሉና ድጋፍ ሲያደርጉ ለነበሩት አቶ ጌታነህ በየነ እና ለፕሮጀክቱ ሠራተኞች በሙሉ ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

ሌላው ስኬት የካምፓኒውን ቀጣይ ህልውና እና የሠራተኛውን የሥራ ዋስትና ለማረጋገጥ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በማፈላለግ በኩል የተደረገው ጥረትና  የተገኘውን ውጤት በተመለከተ አንድ አዲስ የአስፓልት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት እና ወደ አዲስ የሥራ ዘረፍ ጭምር በመግባት አንድ መካከለኛ የመስኖ ውኃ ግድብ ፕሮጀክት መገኘቱን አንስተዋል፡፡ ለዚህም ለአዲሱ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ዕድል መገኘት ታላቅ ሚና ለተጫወቱት ለዶ/ር ዋቅጋሪ ፉሪ በተለይ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

በሥራ ዘመኑ ከሠራተኛው ጋር በተያያዘ ሲነሱ ለነበሩት ጥያቄዎች ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን፣ ከጥቅማ ጥቅም ጋር የተገናኙ ጉዳዮች ካለው የአገሪቷ ነባራዊ ሁኔታና የድርጅቱን አቅም ከግምት ያስገባ ማስተካከያዎች መደረጋቸውን አንስተዋል፡፡ በመጨረሻም አንድ ድርጅት በሥራው ላይ ያልተጠበቀ ችግር ሲያጋጥመው ከችግሩ በመውጣት ወደ ነበረበት ለመመለስ ጊዜ ከማስፈለጉም በተጨማሪ የሁላችንም ያልተቆጠበ ጥረት እንደሚጠይቅ፣ በቀጣይ ሊያሳስበን የሚገባው  አዳዲስ ሥራዎችን የማግኘት ችግር ሳይሆን ለውጫዊ ችግሮች የተለየ ስትራቴጂ የመቀየስ እና በውስጣችን ያለውን የሰው፣ የፋይናንስና የማቴሪያል ሀብቶችን ምርታማ በሆነ ሁኔታ በትጋትና በቁርጠኝነት በሥራ ላይ በማዋል እንዴት ውጤት ማስመዘገብ እንደምንችል በትኩረት ሊሰራበት እንደሚገባ በማስመር፣ ሁሉም ለዚሁ እንዲረባረብ ጥሪ በማድረግ ንግግራቸውን ቋጭተዋል፡፡

Among the successes, he said the company has managed to overcome from the damages caused by manmade problems to sustain itself and ensure job security for employees. He indicated the full completion and handover of Azezo-Gorgora Road Project, and thanked the entire company community for the substantial successful completion of Mehal Meda-Alem ketema Asphalt Road and Arsi University Building projects.

In line to this Mr. Gemshu has mentioned the complex nature of Mehal Meda-Alem ketema Asphalt Road project. He said, given the difficulties associated with the topographic and geological character of the project site, as well as design gap, and to address these problems, the company took its initiative in hiring a foreign expert.

Considering an ethical standard expected from construction sector design appraisal has been recommended and that saved the employer a cost of more than 100 million Birr. The project has come to this level paying immense price and passing through four managers and five site engineers, he said. He expressed his joy for this project has emerged a special from other road projects by its profit record, which he said has to send a message to other similar projects. He also thanked the project manager Eng. Henok Mebratu, and Mr. Getaneh Beyene, who has been closely monitoring and supporting the project as well as the entire project staff.

On other hand, he mentioned the successful work undertaken at company level to sustain the operation and ensure job security through contracts of one new road project and new construction sector of mid-range irrigation dam project. He thanked Dr. Wakgari Furi for his role in realizing the new construction sector.

Mr. Gemshu also explained demands that had been forwarded by employees, and taking the overall situation of the country and capacity of the company into consideration, he said issues related to employment benefits has been adjusted. At last he said a company needs time to get back on track beating the unprecedented challenges it faced and that requires concerted effort. He also noted that for the future the concern should not be how to get new projects but it should be designing special strategy for external challenges and how to diligently enhance the productivity level within



Eng. Girma Guluma Presenting Company Report



Eng. Asfaw Diribsa Presenting Engineering Dep't Report

በመቀጠልም የካምፓኒው ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ ግርማ ጉሉማ የድርጅቱን አጠቃላይ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት አቅርበዋል፡፡ አቶ ግርማ ንግግራቸውን ሲጀምሩ ለዓመቱ የሠራተኞች መድረክ ቀን በሰላም ላደረሰው ፈጣሪ ምስጋናቸውን በማስቀደም የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ለታዳሚዎቹ አቅርበዋል፤ በመቀጠልም አጠቃላይ የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴና የየፕሮጀክቶቹ የሥራ አፈጻጸም ያለበትን ደረጃ፣ የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው የመሀል ሜዳ-አለም ከተማ እና አርሲ ዩኒቨርስቲ ህንጻ ግንባታ ሲሆኑ የተቀሩት ፕሮጀክቶች በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ቢሆኑም፣ አጠቃላይ ሲመዘኑ አመርቂ እንዳልሆነ በዝርዝር አብራርተዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በከፊል S.Hawa ተብሎ ለሚጠራው ሰብ-ኮንትራክተር የተሰጠው የዓለም ከተማ -ደጎሎ ፕሮጀክት የአፈር ሥራው (Earth Work) የተሻለ አፈጻጸም የሚያሳይ መሆኑን ጠቁመው፣ ሰብ-ኮንትራክተሩን አመስግነዋል፡፡ ድርጅቱ ሁለት አዳዲስ ፕሮጀክቶችንም በሥራ ዘመኑ በማግኘት ውል መግባቱን ጠቁመው ቀጣይነት ያለውን ስኬት ማስመዘግብ እንዲቻል ግን ዋናው ጉዳይ በእጃችን ያሉትን ውል የገባንባቸውን ፕሮጀክቶች በተሳካ ሁኔታ ለማጠናቀቅ መረባረብ ወሳኝ ስለሆነ ለዚሁ ሁሉም የበኩሉን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በማስከተልም በዓመቱ የተስተዋሉትን ድክመቶችን የዋናው መሥሪያ ቤት እና የፕሮጀክቶች በማለት በሁለት በመክፈል ዘርዝረዋል፡፡ በዋናው መሥሪያ ቤት በኩል የተስተዋሉት ዋና ዋና ችግሮች ተብለው ከተጠቀሱት መካከል፡-

- በወቅቱ ተገቢውን ግብአት ለፕሮጀክቶች ያለማቅረብና ለዚህ የሚሆን በቂ በጀት መድቦ ያለመንቀሳቀስ፣
- በንብረት አስተዳደር ሥርዓት ላይ በተለይ በሥራ ክፍሉ የሚደረጉ የክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም በዋና መ/ቤትና በፕሮጀክቶች መካከል በነበረው የሥራ ግንኙነት ላይ ክፍተቶች መኖራቸው፣
- ፕሮጀክቶችን በተገቢው ደረጃ ክትትልና ድጋፍ ያለማድረግ እና ተያያዥ ድክመቶች ሲሆኑ፣

internal human, finance and material resources. He concluded his remark by calling up on every staff to make their concerted effort.

Deputy General Manager of the Company Mr. Girma Guluma has also presented the overall operation report of the company for the year. He started his remark by thanking God for gathering everyone at the annual staff assembly and welcomed the guests. He presented the general project execution of the company by taking note of the projects with superior performance particularly; Mehal Meda-Alemketema and Arsi University Building projects while explaining the remaining ongoing projects as not at an appreciable status. Meanwhile, he indicated that the Earth Work of Alemketema-Degolo project given to a sub-contractor called S. Hawa PLC is in a better performance and thanked the sub-contractor. Mentioning the two new projects which contracts have been signed he said in order to maintain long run success the company has to successfully complete the projects at hand, and he call up on every staff to make utmost effort towards this goal.

He highlighted the major weaknesses witnessed over the year in two separate ways namely at head office and at projects.

### At Head Office

- Failure to meet project inputs supply and budget shortage that meets the inputs;
- Issues relating to property administration that implies to follow up and monitoring as well as gaps between head office and projects;
- Failure to undertake proper follow up and support and related issues;

ለእነዚህ ለተፈጠሩት ላንዳንዶቹ ክፍተቶች ውጫዊ የሆኑ መንስኤዎችንና ችግሮችንም አያይዘው እንደሚከተለው ለይተው ገልጸዋል፡፡

- የውጪ ምንዛሪ እጥረት ማጋጠሙ፣
- የአቅርቦቶች በገበያ ላይ እጥረት መኖርና የዋጋ ንረት መከሰቱ፣
- የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ተደጋጋሚ ብልሽት
- ለሥራው ቁልፍ የሆኑ ባለሙያዎች ከገበያ ላይ ያለመገኘት፣
- የወሰን ማስከበር ችግሮች መኖራቸው፣
- በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ላይ የዲዛይን ችግር ማጋጠሙ፣
- የፀጥታ ችግር እና
- ቀደም ሲል በደርጅቱ ላይ ተፈጥሮ በነበረው ሰው ሰራሽ ችግር ምክንያት ወደ በጀት ዓመቱ ተንከባለው የመጡት ጉዳዮች ጫና መፍጠራቸው እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

**ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በየፕሮጀክቶቹ ላይ ሲስተዋሉ የነበሩት ድክመቶች ተብለው ከተለዩት መካከል ዋንኞቹ፡-**

- የቀረበውን ግብአት በአግባቡ ያለመጠቀም፣
- ከንብረት አስተዳደርና ሀብት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ለድርጅቱ ንብረት አያያዝ ተገቢውን ጥንቃቄ ያለማድረግ፣ ብክነቶች መኖራቸው፣ የተቆርቋሪነት ስሜት ያለመኖሩ ተጨባጭ ማሳያዎች መኖራቸው እና የችግሮቹን ምንጭ ከምንጩ ለይቶ መፍትሄ አለመስጠት በተደጋጋሚ መታየታቸው፣
- የአማካሪ መሐንዲስ ተሽከርካሪዎችን እንደ ድርጅቱ ንብረት ቆጥሮ ክትትልና ቁጥጥር ያለማድረግ፣
- የክፊያ ሴርተፊኬት በወቅቱ አዘጋጅቶ ያለማቅረብ እና
- እያንዳንዱን ተግባር አዋጭነት መዝኖ ሪፖርት አለማድረግ መሆናቸውን አንስተዋል፡፡

ሲያጠቃልሉም፣ በቀጣይ እነዚህን ክፍተቶች ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ ሁሉም በየደረጃው የሚጠበቅበትን ተረድቶ በባለቤትነት ስሜት በመንቀሳቀስ የተሻለ ስኬት ለማምጣት በጋራ መረባረብ እንደሚገባ በማሳሰብ ሪፖርታቸውን አጠናቀዋል፡፡

የድርጅቱ የኮንትራት አስተዳደር መመሪያ ኃላፊ የሆኑት አቶ አሰፋው ድሪብሳ እና የውኃ ሥራዎች መምሪያ ኃላፊ የሆኑት ዶ/ር ዋቅጋሪ ፉሪ የየመምሪያቸውን የሥራ እንቅስቃሴና ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎችን በመጠቆም ሪፖርት አቅርበዋል፡፡

በዚሁ መድረክ የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠና የዕለቱ የክብር እንግዳ በሆኑት በዶ/ር መሠለ ኃይሌ አማካይነት "Construction project Management, planning, Risk Analysis, Quality, Safety and Ethics" በሚል ርዕስ ላይ ለሠራተኞቹ ተሰጥቷል፡፡

The Deputy General Manager discussed some of the external causes of these failures.

- Hard currency shortage;
- Supply shortage and inflation;
- Recurrent failure of construction machineries;
- Lack of key personnel in the market;
- ROW obstruction;
- Design gaps with some projects;
- Security problems and;
- Manmade challenges that have turned to the year from the previous year.

## At Project Level

- Improper utilization of inputs;
- Failure to comply with proper property administration and resource management, wastage, lack of sense of ownership, and absence of taking swift corrective measures from the source;
- Failure to make follow up and monitoring to vehicles of the consulting engineer;
- Not meeting payment certificate deadline and;
- Failure to report the evaluation of every activity. Upon concluding his presentation Mr. Girma called upon everyone at their capacity to jointly execute what is expected of them in a sense of ownership to deliver better results.

Moreover, the Company's Contract Administration Division Head Mr. Asfaw Diribsa and Water Works Division Head Dr. Wakgari Furi have also presented activities undertaken by their respective divisions during the year and their future directions.



Dr. Mesele Haile, Presenting Water Works Dep’t Report



Dr. Wakgari Furi , Delivering Training for Company Staff

በመጨረሻም በዓመቱ ካሉት ፕሮጀክቶች መካከል የተሻለ የሥራ አፈጻጸም ላስመዘገበው የመህልሜዳ-ዓለምከተማ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት የዋንጫ ሽልማት የተበረከተለት ሲሆን፣ ሽልማቱንም ከካምፓኒው ዋና ሥራ አስኪያጅና ከዕለቱ የክብር እንግዳ እጅ የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ኢ/ር ሄኖክ መብራቴ ተቀብለዋል፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ለፕሮጀክቱ ሠራተኞችም የአንድ ወር ደመወዝ በቦነስ መልክ እንደተበረከተላቸው የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ለሠራተኞቹ አብስረው ሁሉም ፕሮጀክቶች ከዚህ ትምህርት ቀስመው ለተሻለ ውጤትና ስኬት ተግተው እንዲሰሩ ለሁሉም የድርጅቱ ሠራተኞች በማሳሰብ መድረኩ ፍጻሜ አግኝቷል፡፡

On the occasion a capacity building training by Dr. Mesele Haile under the theme “Construction project Management, planning, Risk Analysis, Quality, Safety and Ethics” was given to the employees.

The event was concluded by handing out a trophy award to Mehal Meda-Alemketema Road project for its superior performance during the year. The Project Manager Eng. Henok Mebratu has received the trophy from the Company General Manager and the guest of honor. In related to this the General Manager announced that employees of the project would get their monthly salary in the form of bonus, and he called up on other projects to take lesson from this and work relentlessly to deliver better results and success.



Eng. Henok Mebratu Has Recieved Trophy from Honorable Gust & Company’s General Manager

# ገበኮን የኮቪድ 19 ወረርሽን የመከላከል ዘመቻን ስኬታማ ለማድረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጀመረ

# GEBECON Launches COVID-19 Mitigation Campaign

መነሻውን በቻይና አገር ውሀን ከምትባል ከተማ ያደረገውና በዓለም አቀፍ ደረጃ ታላቅ አደጋ በመደቀን ላይ የሚገኘው በሳይንሳዊ መጠሪያው ኮቪድ-19 በሚል የሚታወቀው በሽታ አምጪ ተህዋሲ ወረርሽኝ ሚሊዮኖችን በመበከል የብዙዎችን ህይወት እየቀጠፈ ይገኛል፡፡ ከዚህም አልፎ በሽታው በዓለም አገራት፣ ባለፀጋዎችንም ጨምሮ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን እያስከተለ መሆኑ አሳሳቢነቱን አጉልቶታል፡፡

በአገራችንም በዓመቱ ሁለተኛው አጋማሽ መጀመሪያ ላይ መከሰት መጀመሩ የሚታወስ ሲሆን፣ የበሽታውን ወረርሽኝ ለመከላከልና ብሎም ለመግታት በአገር ደረጃ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከማወጅ አንስቶ ሁሉን አቀፍ እርምጃዎች በየደረጃው እየተወሰደ ይገኛል፡፡ ገበኮንም ሰራተኞቹን ከዚህ አስከፊ ወረርሽኝ ለመታደግ እንዲቻል በጤና ተቋማት የተላለፉትን የመከላከል እርምጃዎችን ተግባራዊ ከማድረግ ባለፈ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች የሚገኙባቸውን አካባቢዎችን ጨምሮ በሌሎች አካባቢዎች የሚገኙትን የህብረተሰብ ክፍሎችን የመደገፍ ተግባራትን ሲከውን ቆይቷል፡፡

በየፕሮጀክቶቹ ላሉት የድርጅቱ ሠራተኞች ከዋና መሥሪያ ቤት ሰው በመላክ በበሽታው ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን መግለጫ አድርጓል፤ በሁሉም ደረጃ ለሚገኙት ሠራተኞች የንጽህና መጠበቂያ ሳንታይዘር ተገዝቶ በየጊዜው እንዲቀርብ እየተደረገ ይገኛል፤ ለዋና መ/ቤት ሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲመቻች የተደረገ ከመሆኑ በተጨማሪ በሥራ ቦታም በሽታውን ለመከላከል የተቀመጡትን ህግጋት እንዲተገበሩ ማሳሰቢያዎችን በየቦታው በመለጠፍ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

Believed to be originated from the Chinese city of Wuhan, described by its scientific name as COVID-19, the virus has threatened the global population spreading among millions and killing many people. The disease has become a point of concern causing social and economic crisis across the globe including those developed economies.

It is to be recalled that the disease was identified in our country at the start of the second half of the year. Besides prevention and mitigation efforts through declaring State of Emergency concerted efforts have been excreted at all levels in the nation. In order to protect its employees from this pandemic GEBECON has implemented various safety precautionary measures per the direction given by health institutions. Other than this the company has also undertaken mitigation support activities at its road projects sites as well as for other communities.

The company deployed relevant personnel from the head office to every project sites so as to raise awareness of the employees about the disease. While sanitizers are being provided for all employees, transportation services are availed for employees at head office in line with practicing safety standards set to be adhered at working areas.




**Some Pictures of Supports Provided by the Company for Coronavirus Prevention**

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በአካባቢው ለሚኖሩ አቅም ለሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ለንጽህና መጠበቂያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን በማቅረብ እንዲደርሳቸው ከመደረጉም በተጨማሪ፣ የህክምና አገልግሎቱን በአከባቢው ለማጠናከር እንዲረዳ አንድ አምቡላንስ ድርጅቱ ከዋና መ/ቤት ለጊንጪ-ሺኪቴ እና ሺኪቴ-ጩሉጤ ፕሮጀክት አከባቢ አገልግሎት እንዲውል በመመደብ በሽታው ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ ድርጅቱ በዚህም ብቻ ሳይወሰን የተለያዩ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች የሆኑት ሳኒታይዘር፣ የውሀ ማከማቻ በርሜሎችና የመሳሰሉትን በምዕራብ ኦሮሚያ ከጊንጪ እስከ ሆሮ-ጉዱሩ ባሉ ከተሞች በሽታውን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ እንዲቻል ለማህበረሰቡ አስረክቧል፡፡

ድርጅቱ ይህንን የበሽታ ወረርሽኝን ለመከላከል የጀመራቸውን ተግባራት አጠናክሮ እንደሚቀጥል በዚሁ አጋጣሚ እያስታወሰ፣ የህክምና ባለሙያዎችና ተቋማት የሚያወጡት የመከላከያ ዘዴዎች እና መመሪያዎችን እያንዳንዳችን በአግባቡ ተከታትለን በሁሉም ሥፍራና ሁኔታ ውስጥ ተግባራዊ በማድረግ ከዚህ ክፉ በሽታ እራሳችንን፣ ብሎም ህብረተሰባችንን እንጠብቅ የሚለው የድርጅታችን መልዕክት ነው፡፡

In addition to these mitigation efforts the company provided sanitary materials for most vulnerable community groups living in the project areas. In order to enhance the medical service provision at Ginchi-Shikute and Shikute-Chulute project areas in particular the company has deployed an ambulance vehicle from the head office and is serving the community ever since the virus was reported. The company's dedication to help mitigate the spread of the virus was not limited to the aforementioned activities but also entails supply of various sanitary materials and water tanker installation among others in Oromia regional state from Ginchi to Horo Gudru towns.

The company would like to note at this juncture that it will further enhance its dedication to continue its mitigation efforts against the virus. The company also stresses the need to adhere to prevention procedures and advises given by health professionals everywhere at every circumstance to protect ourselves and the public from the pandemic.

# የሥራ ቦታ COVID-19 መከላከያ እና ቁጥጥር ምክሮች
# Tips on Workplace COVID-19 Prevention and Controls

## 1. የኮቪድ-19 ምልክቶች

ኮቪድ-19 SARS-CoV-2 በተባለ ቫይረስ የሚመጣ ኢንፌክሽን ሲሆን ከቀላል እስከ ከባድ ህመም ከማስከተል አልፎ በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ ገዳይ በሽታ ነው። ከዋነኛ የህመሙ ምልክቶች መካከል ትኩሳት፣ ሳል እና መተንፈስ ያለመቻል ይጠቀሳሉ። በቫይረሱ የተያዙ አንዳንድ ሰዎች ሌሎች የመተንፈሻ አካላት ያልሆኑ ምልክቶች እንዳጋጠሟቸው ሪፖርት አድርገዋል። እንደ የአሜሪካው በሽታ መቆጣጠሪያ ማዕከል (CDC) የኮቪድ-19 በሽታ ምልክቶች ሳይለዩ ተጋላጭ ከተሆነበት ከ2 እስከ 14 ቀናት በሰውነት ውስጥ ሊደበቁ ይችላሉ።



## 2. የኮቪድ-19 ስርጭት ባህሪ

ምንም እንኳን የመጀመሪያዎቹ የኮቪድ-19 ምርመራ ውጤቶች ከእንስሳት ወደ ሰው እንደተላለፉ ቢታመንም፣ በቫይረሱ የተጠቃ ሰው ግን ወደ ሌሎች ሰዎች ሊያስተላልፍ ይችላል።
ይህ በዋነኝነት ከሰው ወደ ሰው የሚሰራጭ ቫይረስ በሚከተሉት መንገዶች ሊተላለፍ ይችላል፤

- በሰዎች መካከል ከሁለት ሜትር ባነሰ ርቀት የሚኖር ጥግግት ወይም ንክኪ
- በቫይረሱ የተጠቃ ሰው በሚያስልበት ወይም በሚያስነጥስበት ወቅት ከትፋሽ ጋር የሚወጡ ፍንጣቂዎች በቅርበት ባሉ ሰዎች አፍ እና አፍንጫ ላይ በማረፍ ወደ መተንፈሻ አካል ሊገቡ ይችላሉ።
- አንድ ሰው "SARS-CoV-2"ን በላዩ ላይ ያለበት አካል ወይም ቁሳቁስ በመንካት ከዚያም የራሳቸውን አፍ፣ አፍንጫ ወይም ምናልባትም ዓይኖቻቸውን በመንካት በCOVID-19 ሊያስ ይችላል፣ ነገር ግን ይህ ቫይረሱ የሚተላለፍበት የመጀመሪያ መንገድ ነው ተብሎ አይታሰብም።

## 1) Symptoms of COVID-19

Infection with SARS-CoV-2, the virus that causes COVID-19, can cause illness ranging from mild to severe and, in some cases, can be fatal. Symptoms typically include fever, cough, and shortness of breath. Some people infected with the virus have reported experiencing other non-respiratory symptoms. Other people, referred to as asymptomatic cases, have experienced no symptoms at all.

According to the American Center for Disease Control (CDC), symptoms of COVID-19 may appear in as few as 2 days or as long as 14 days after exposure.

## 2) How COVID-19 Spreads

Although the first human cases of COVID-19 likely resulted from exposure to infected animals, infected people can spread SARS-CoV-2 to other people.

The virus is thought to spread mainly from person-to-person, including:

- Between people who are in close contact with one another (within about 6 feet).
- Through respiratory droplets produced when an infected person coughs or sneezes. These droplets can land in the mouths or noses of people who are nearby or possibly be inhaled into the lungs.
- It may be possible that a person can get COVID-19 by touching a surface or object that has SARS-CoV-2 on it and then touching their own mouth, nose, or possibly their eyes, but this is not thought to be the primary way the virus spreads.

### 3. መሠረታዊ የመከላከያ መንገዶች

- ወደ ሥራ ቦታው የሚመጡትን ሰዎች ወይም የጣቢያ ተደራሽነትን ይቀንሱ፤
- በሠራተኞች መካከል የሚኖረውን ግንኙነትን ለመቀነስ የሥራ ዕቅድን እና እንቅስቃሴዎችን ያመቻቹ፤
- የሥራ ቦታውን አጠቃላይ ንፅህና ደረጃን ይጨምሩ፤
- ለሠራተኞች እና ለአካባቢያቸው ማኅበረሰብ ጤና እና ደህንነት ቅድሚያ ይስጡ፤
- የሠራተኛውን ኃይል ግንዛቤ ያሳድጉ፡፡

### 4. ዝርዝር የመፍትሔ አቅጣጫዎች

#### ሀ. በግንባታ ሥራ ዕቅድ ደረጃ

- ✓ የግንባታ ስራዎችን አስቀድሞ በምዕራፍ በመከፋፈል የሰራተኞችን ጥግግት መቀነስና አላስፈላጊ መደራረቦች ማስወደግ፤ ይህ የአሰራር ስልት ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ አስቀድሞ የታቀደ ከሆነ አስፈላጊውን ማሻሻያ በማድረግ ተግባር ላይ ማዋል፤
- ✓ ከግንባታ ሥራ ጋር የተገናኙ እንደ ጓንትና የአደጋ መከላከያ መነፅሮች ያሉ መሰረታዊ የግል መከላከያ መሳሪያዎች (PPE) ሰራተኞች ለተመደቡበት ሥራ በሚሆን መልኩ ማቅረብ፤ ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ሁለትና ከዚያ በላይ ለዳግም ግልጋሎት መዋል የሚችሉ የአፍና አፍንጫ ጭንብሎችን ማቅረብ፤
- ✓ በግንባታ ስፍራዎች የእጅ መታጠቢያዎችን ከንፁህ ውሀ እና ሳሙና አቅርቦት ጋር ሌሎች የኬሚካል ንፅህና መጠበቂያ ምርቶችን በሥራ ቦታ ማዘጋጀት፤ ለአዲስ የግንባታ ስፍራዎች እነዚህን የበሽታ መከላከያ ቁሳቁሶች ዝግጁ ማድረግና በበጀት መደገፍ፤
- ✓ በተቻለ መጠን እያንዳዱ ሠራተኛ በተመደቡባቸው ሥራዎች የሚያስፈልጉ መሰረታዊ የስራ መሳሪያዎች ሊቀርብላቸው ይገባል፤ በርካታ ሠራተኞች አንድን እቃ በጋራ መገልገል የለባቸውም፤ በጋራ መገልገል የሚኖርባቸው አልያም ለሁለተኛ ግልጋሎት የሚውሉ ከሆነ ለአገልግሎት ከመጠቀም በፊት መፀዳት ይኖርባቸዋል፤
- ✓ ከአንድ አካባቢ አልያም በአቅራቢያ ካሉ የመኖሪያ አካባቢ ወይም ካምፕ የሚኖሩ ሠራተኞችን ብቻ አብረው የሚሰሩበትን መንገድ ማመቻቸትና ከተራራቀ መኖሪያ ካምፕ የሚመጡ ሰራተኞችን ተሳትፎ ማስወገድ፤
- ✓ በኮቪድ-19 መከላከያ መርሆች ላይ የሚደረገውን ክትትል ማጠናከርና በአዳዲስ መመሪያዎች ዙሪያ ተቆጣጣሪዎችን ማብቃት፤

### 3) The main underlying Prevention approaches are:

- Reduce access to site
- Adapt work plan and activities to reduce close contact
- Increase overall level of hygiene of the site
- Prioritize health and safety of staff, workers and their surrounding communities
- Increase awareness of the workforce

### 4) Proposed Measures

#### i. Planning Phase

- ✓ Plan construction phases avoiding large group of workers and unnecessary overlap of crews. If the work plan was developed prior to COVID-19 outbreak, consider reviewing and adapting when necessary;
- ✓ Basic Personal Protective Equipment (PPE) related to construction safety such as gloved and glasses should be provided to workers depending on the tasks they are assigned to. In addition, each worker should be provided with two or more reusable masks (not surgical/medical graded masks);
- ✓ Establish hand washing stations including provision of clean water and soap, together with cleaning and disinfection products for construction sites. For new construction site, plan and budget provision of these items;
- ✓ Preferably, every worker should be provided with a basic set of tools needed for the tasks they are assigned to. Using of the same tool by multiple workers should be avoided. If tools are shared or stored for later use by another person, they need to be disinfected/cleaned;
- ✓ Plan to engage workers coming from the close proximity of the facility been built (possibly from the same block) and avoid involving labor from farther away camps or villages;

- ✓ ከተቻለ የግንባታ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የጤና አጋሮችን በማስተባበር አስፈላጊው ቅድመ ጥንቃቄ መደረጉን ማረጋገጥ፤

### ለ. ሠራተኞችን ማዘጋጀት

- ✓ ስለ ኮቪድ-19 ባህሪይ፣ ምልክቶች፣ መተላለፊያ መንገዶች፣ አደገኝነት እና የዓለም ጤና ድርጅት ያስቀመጣቸው በሥራ ቦታና በህዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎች እንዲሁም በቤት ውስጥ ሊደረጉ ስለሚገቡ የመከላከያ መንገዶች የተመለከተ መግለጫ ለሁሉም ሠራተኞች መሰጠት አለበት፤
- ✓ የበሽታው መከላከያ መልዕክቶች በግልፅ በሚታይ ስፍራ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህን ቁልፍ የመከላከያ መልዕክቶችን በማባዛት መላ ሠራተኞች ለቤተሰቦቻቸውና ላሉበት ማህበረሰብ እንዲያሰራጩ ማድረግ፤
- ✓ የቤተሰቦቻቸው አባላት ድንገት የሚታመሙ ከሆነ ሠራተኞች ምን ማድረግ እንዳለባቸው በሚገባ ማስረዳት፤
- ✓ ሠራተኞች በመካከላቸው የ2 ሜትር አካላዊ ርቀት እንዲጠብቁ ማሳወቅና ለሌሎች ለሚመከሩ የበሽታው መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ተግባራት ተገዢ እንዲሆኑ ከማድረግ አልፎ፡-
- ✓ እጅን በንፁ ውሀና ሳሙና ቢያንስ ለ20 ሰኮንድ በመደበኛነት መታጠብ አልያም በፀረ ተህዋሲ ማፅዳት፤
- ✓ እጅን ሳይታጠቡ አይንን፣ አፍንጫና አፍን አለመንካት፤
- ✓ በማሳል ወይም በማስነጠስ ወቅት አፍን በመፀዳጃ ቤት ወረቀት/ሶፍት በመሸፈንና በተከደነ ቆሻሻ ማስወገጃ ውስጥ ወዲያውኑ መጣል፤ ሶፍት የማይገኝ ከሆነ አፍን በክንድ በመሸፈን ማሳል ወይም ማስነጠስ፤
- ✓ ምራቅን በየቦታው አለመትፋት፡፡
- ✓ የሥራ ጓንቶች ራስን ከአደጋ ለመከላከል የሚጠለቁ እንደመሆናቸው የኮቪድ-19ን መተላለፍ ሊከላከሉ ስለማይችሉ ልክ እንዳልታጠቡ እጆች መታየት ስላለባቸው ፊትን መንካት የለበትም፤
- ✓ ሰራተኞች በየትኛውም የስራ ወቅት መጨባበጥ ወይም መተቃቀፍ የለባቸውም፤
- ✓ በህመም ወይም በበሽታ መያዛቸው የተጠረጠሩ ሰዎች ያሉበት አልያም ባለፉት ሶስት ቀናት ውስጥ የተዘዋወሩበት አካባቢ የሚሰሩ ሰራተኞች የፊት ጭምብል እና ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚያገለግሉ ጓንቶች አዘውትሮ መጠቀም አለባቸው፤
- ✓ ሰራተኞች ጭምብል የማያገኙ ከሆነ ከቤት ውስጥ ቅሳቁስ ወይም ጨርቅ በራሳቸው እንዲያዘጋጁ ማበረታታት፤
- ✓ ሰራተኞች አዘውትረው (ቢቻል በየቀኑ) ልብሶቻቸውን እንዲያጥቡ መምከር፡፡

- ✓ Supervision should be strengthened including COVID-19 prevention principles, and supervisors oriented on their new responsibilities;
- ✓ If possible, prior to start construction work coordinate with Health partners to check the site and ensure appropriate measures are adopted;

### ii. Prepare Your Workforce

- ✓ An orientation on COVID-19 should be provided to all workers, including description of the disease, symptoms, transmissibility, severity and WHO's key prevention messages to be followed on site, public spaces as well as in their homes;
- ✓ Prevention messages should be printed and clearly displayed on site. Consider providing an additional printed copy of the key prevention messages for all workers to disseminate in their families (and communities);
- ✓ Workers should be clearly informed on protocols to follow in case they or their family members get sick;
- ✓ Workers should be requested to maintain physical distance of 2 meters (6 feet) from others as much as possible and to adhere to the other suggested practices for infection prevention and control, in particular:
- ✓ Wash your hands regularly with clean water and soap for at least 20 seconds, or clean them with a hand sanitizer;
- ✓ Avoid touching your eyes, nose and mouth with unwashed hands;
- ✓ When coughing or sneezing, cover your mouth with tissue and throw it into closed bin immediately. If you do not have a tissue, cough or sneeze into your flexed elbow;
- ✓ Do not spit.
- ✓ Working gloves are sometimes worn to protect against injuries during some activities, but they do not offer any protection against transmission of COVID-19 and should be considered as unwashed hands in terms of minimizing touching one's face;

### ሐ. በመስክ መገኘት ስላለባቸው ነገሮች

- ✓ መስክ ላይ መገኘት የሚገባቸው ሰራተኞች፣ ተቆጣጣሪዎች እና ስራ አስኪያጆች እጅግ አስፈላጊ ግለሰቦች ብቻ መሆን አለባቸው፤
- ✓ የቁጥጥርና ክትትል ጉብኝቶችን መቀነስና ሰራተኞች በመስክ በማይኖሩበት በምሳ ወይም በፀሎት ሰዓታት ወቅት ማካሔድ፤
- ✓ የግንባታ ስፍራ ከተፈቀደላቸው ሰዎች ውጪ ወደ ሰራተኞቹ ማንም እንዳይደርስ መከላከል፤
- ✓ ወደ መስክ መግቢያና መውጪያ በሮችን በግልፅ መለየትና መቆጣጠር፤
- ✓ ወደ መስክ የሚገቡትን የሰውነት ሙቀት መጠን መለካት፤
- ✓ በመስክ ላይ ሰዎች እጆቻቸውን ሲታጠቡ ወይም ሙቀት በሚለኩበት ወቅት ጥንቃቄ ባለው መልኩ በቂ ርቀት እንዲጠብቁ ማድረግ፤
- ✓ የሰራተኞችን እና ጎብኚዎችን ሙቀት የሚለኩ እንዲሁም ጠቅላላ የጤና ሁኔታና ተጋላጭነት ለመቆጣጠር ስልጠና የወሰዱ ባለሙያዎችን መመደብ፤
- ✓ በመግቢያዎች ላይ በቂ የእጅ መታጠቢያ ስፍራዎች ከውሀና ሳሙና ጋር በግልፅ ከሚታይ ምልክት ጋር መኖሩን ማረጋገጥ፤
- ✓ በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ የሚካተት ማናቸውም ሰው ወደ ስራ ቦታ መግባት የለባቸውም፤
    - በኮቪድ-19 ህመም ከሚጠረጠር የቤተሰብ አባል ጋር አብረው የሚኖሩ ከሆነ ወይም ራሳቸውን አግልለው አልያም የኮቪድ-19 ህመምተኛ ከሆነ ሰው ጋር ባለፈው ሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ንክኪ ካለው/ካላት በስራ ቦታ አለመገኘት ወይም ራሳቸውን ለሁለት ሳምንታት ራሳቸውን በማግለል ማቆየት፤
    - ከአንድ በላይ ከኮቪድ-19 ጋር የተገናኙ ምልክቶች ማለትም ከፍተኛ የሰውነት ሙቀት መጠን፣ አዲስና ተከታታይ ሳል፣ ለመተንፈስ መቸገር ካለ ወደ ስራ ቦታ አለመቅረብ፤ በቤት በመቆየት ራስን ማግለል፣ ከፍተኛ የህመም ምልክቶች የሚታዩ ከሆነ ወደ ህክምና መሔድ፤
    - በዕድሜ፣ በሌሎች የጤና ምክንያት ወይም በእርግዝና ተጋላጭ ሲኮን፡፡
- ✓ ማንኛውም ሰው ወደ መስክ ከመግባትም ሆነ ከመውጣት በፊት የእጆቻቸውን ንፅህና መጠበቅ፤
- ✓ ሰራተኞች የግል መጓጓዣ መንገዶችን እንዲጠቀሙ ማበረታታትና በተቻለ መጠን የህዝብ መጓጓዣ ማስወገድ፡፡

- ✓ Workers should not greet each other with handshakes or embraces at any point during the day;
- ✓ If workers are operating in an area where sick or suspected infected people are currently or recently transited (in the previous 3 days), they should wear mask and disposable gloves at all times;
- ✓ If masks are not available, workers should be encouraged to prepare handmade ones using household items or clothes materials;
- ✓ Advice workers to wash their clothes frequently (daily if possible).

### iii. Access to Site

- ✓ Only essential visitors (workers, supervisors, and managers) should be allowed on site;
- ✓ Program/monitoring visits should be reduced to the minimum and should be planned when workers are not on site (i.e. lunch or prayer time);
- ✓ Construction site should be ensured no one can enter or approach the workers without authorization;
- ✓ Entry and exit gates should be clearly marked and guarded;
- ✓ Body temperature should be measured for all persons entering the site;
- ✓ Allow enough space for people to queuing in a safe manner at the entrance of the site while they wash their hands and get screened;
- ✓ A trained staff should be designated to guard the access, checking temperature of workers and visitors and enquiring about overall health condition and vulnerability;
- ✓ Ensure there are sufficient hand washing stations at the entrance and that they have water and soap, as well as clearly display signs requesting persons entering to wash their hands;

### መ. በግንባታ ስራ ላይ መደረግ ያለባቸው

- ✓ በተቻለ መጠን በማንኛውም ወቅት ሰራተኞች በመካከላቸው 2 ሜትር አካላዊ ርቀት መጠበቅ አለባቸው፡፡ በሚቻለው ያህል ተጠጋግቶ የሚሰሩ ስራዎችን ማስወገድ፤ እነዚህ ስራዎች የግድ መሰራት ካለባቸው ሰራተኞች ጭምብል ማድረግ ይኖርባቸዋል፤

- ✓ ቢቻል የግንባታ ሰራተኞች ተለይተውና ተግባራት እርስ በርስ በማያገናኛቸው መልኩ መመደብ አለባቸው፤ የሰራተኞች እረፍት፣ ምሳ እና የፀሎት ሰዓታት በፈረቃ እንዲሆን ይመከራል፤

- ✓ አንድ ሰራተኛ በመስክ ባለበት ወቅት የኮቪድ-19 ምልክቶች የሚያሳይ ከሆነ፣ የሚከተሉት እርምጃዎች መወሰድ ይኖርባቸዋል፤

  - ምንም ነገር መንካት አይኖርበትም፤
  - በማሳል ወይም በማስነጠስ ወቅት ሶፍት መጠቀምና ክዳን ባለው ቆሻሻ ማስወገጃ ውስጥ መጣል፣ አልያም በክንድ ሽፍኖ ማሳልና ማስነጠስ፤
  - ወደ ቤት በመመለስ ራስን ማግለል ወይም ከፍተኛ የህመም ስሜት ሲስተዋል ወደ ህክምና መሔድ፤
  - በሰራተኛው/በሰራተኛዋ በቅርቡ የተነኩ ቁሳቁስን ማፅዳት፡፡

- ✓ ሰልፍ በሚኖርባቸው እንደ መፀዳጃ ስፍራዎች ሁሉ 2 ሜትር አካላዊ ርቀትን መጠበቅ፤

- ✓ በመስክ የሚደረጉ ስብሰባዎችን መቀነስ፣ ለሰራተኞች የሚሰጡ የስራ መመሪያዎች አካላዊ ርቀትን በጠበቀ መልኩ በክፍት ቦታዎች መደረግ አለባቸው፤

- ✓ የግንባታ ስራዎች በተዘጋ ስፍራ የሚከናወኑ ከሆነ በር እና መስኮቶችን ክፍት በማድረግ በተቻለ መጠን አካባቢው እንዲናፈስ ማድረግ፤

- ✓ ወደ ግንባታ ስፍራ መግባት ያልተጠበቀ ድንገተኛ ክልከላ ሊኖር የሚችልበት ዕድል ሊከሰት ስለሚችል ማንኛውም ቁሳቁስ እና መሳሪያ በየለቱ እየተጸዱ በጥንቃቄ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፤

- ✓ የግንባታ ቁሳቁሶችንና ጭነቶችን በሚቀበሉበትና ከተሽከርካሪ በሚያወርዱበት ወቅት ሰራተኞች ምንጊዜም ከአሽከርካሪዎች ርቀታቸውን መጠበቅ አለባቸው፤ በተቻለ መጠን አሽከርካሪዎች በመኪና ውስጥ መቆየት ይኖርባቸዋል፤ ለጥንቃቄ ሲባል አሽከርካሪዎች ጭነቶችን ማውረድ ካለባቸው ያለ ሰራተኞች እርዳታ በራሳቸው ማድረግ ያለባቸው ሲሆን፣ ከማውረዳቸው በፊትና በኋላ እጆቻቸውን መታጠብ ይኖርባቸዋል፤ በእቃ አድራሾችና ተቀባዮች መካከል የሚኖር ማንኛውም ንክኪ መወገድ አለበት፤ ይህም ወረቀትና ብዕር ለፊርማ መቀባበልና የመሳሰሉትን ያካተተ ነው፡፡ ማንኛውም በወረቀት ላይ መፈረም ያለበት ሰው የራሱ ብዕር እንዲኖረው አልያም ከፊርማ በኋላ እጅን መታጠብ ይመከራል፡፡

- ✓ Anyone falling in one of the following categories should not be allowed on site:

  - Has a family member suspected COVID-19 patient living in the same household or self-isolating, or if s/he has got in close contact with a confirmed COVID-19 patient in the previous two weeks. S/he should not report on site and self-quarantining at home for two weeks;
  - Is showing one or more symptoms related to COVID-19 (high temperature, new persistent cough, shortness of breath). S/he should not report on site, stay home and self-isolate or seek medical care in case of severe symptoms;
  - Is a vulnerable person (by virtue of age, clinical/ health condition or pregnant).

- ✓ All persons should wash or clean their hands before entering and leaving the site;

- ✓ Workers should be encouraged to reach the site using individual modes of transportation and avoid public transport when possible.

### iv. During Construction;

- ✓ To the most possible extent, workers should maintain physical distance of 2 meters (6 feet) from others at all times. Performing activities that must be conducted in close proximity should be avoided when possible. If these activities must take place, workers should wear masks;

- ✓ If possible, construction crews should be segregated and tasks allocated so they do not overlap. It is suggested to establish crew shifts to be also applied for break, lunch and pray time;

- ✓ If a worker develops COVID-19 symptoms on site, the following actions should be followed:

  - Avoid touching anything;
  - Cough and sneeze into a tissue and put it in a closed bin, or in their flexed elbow in case they don't have tissues;
  - Return home and self-isolate, or seek medical care in case of severe symptoms;

### ሠ. እጅ መታጠብ፣ ጤና አጠባበቅና ንፅህና

- በቂ የእጅ መታጠቢያ ስፍራዎችን ከውሀና ሳሙና ጋር አልያም ከ60 በመቶ ያላነሰ አልኮል ይዘት ያላቸውን የእጅ ማፅጃ (ሳኒታይዘር) ማዘጋጀት፤ ውሀና ሳሙና በበቂ ሁኔታ መኖራቸውን አዘውትሮ ማረጋገጥ፤
- የእጅ መታጠቢያ መገልገያዎችን አዘውትሮ ማፅዳትና በመደበኛነት የፅዳት መርሀ ግብር ማውጣት፤
- የተለያዩ መገልገያዎችን፣ የግል ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶችንና በተደጋጋሚ የሚነካኩ ነገሮችን በተደጋጋሚ ቢያንስ በቀን አንዴ ከብክለት መፀዳት አለባቸው፤
- ቢቻል አስፈላጊ መፀዳጃ ቤት በስራ አካባቢ ባለ ቅጥር ግቢ ውስጥ ማዘጋጀትና ንፅህናውን መጠበቅ፤ በማንኛውም ሁኔታ ሰራተኞች መፀዳጃ ቤት ከተጠቀሙ በፊትና በኋላ እጃቻቸውን እንዲታጠቡ ማበረታታት፤
- ለመመገቢያ፣ ለማረፊያ እና ለፀሎት የሚሆኑ ስፍራዎችን ለይቶ በማዘጋጀት አጠቃቀሙን ከብክለት ተጋላጭ የምሆንበትን መንገድ መቀነስ፤ ሰራተኞች በሚመገቡበት፣ በሚፀልዩበት እና በረፍት ወቅት ርቀታቸውን መጠበቅ አለባቸው፤
- ጥንቃቄ የተሞላበት የመጠጥ ውሀ ስርጭት እንዲኖር በማድረግ ለአንዴ የሚያገለግሉ መጠጫዎችን ማቅረብ ወይም ሰራተኞች የግል መጠጫ እንዲኖራቸው ማበረታታት፤
- ማንኛውም ከግንባታ ቁሳቁስ ውጪ ያለ ጠጣር ቆሻሻ በፍጥነት ክዳን ባለው ቆሻሻ ማስወገጃ መቀመጥ ያለባቸው ሲሆን ሌላ ሰው እንዲያነሳቸው መተው የለባቸውም፤
- ለበሽታ አስተላላፊ ሊሆኑ የሚችሉ ማንኛውም ጠጣር ቆሻሻዎችን ለብቻ ለይቶ ማስወገድ፤ ከቆሻሻ ማስወገጃ ከረጢቶች ጋር የሚኖረውን ንክኪ ለመቀነስ እንዲቻል ድርብ የፕላስቲክ ከረጢቶችን መጠቀም፣ ይህም ለምሳሌ አንዱን በደንብ በመቋጠር በሌላው ደግሞ መሸፈን፤ ቆሻሻውን ከማስወገድ በፊት ቢያንስ ለ72 ሰዓታት ማቆየት፤

### ረ. ስራው ከተጠናቀቀ በኋላ

- ከርክክብ አስቀድሞ የስራ ቦታው በጥንቃቄ መፀዳትና ከብክለት ነፃ መደረግ አለበት፤
- ሁሉም የቆሻሻ፣ የግንባታ ተረፈ ምርቶች፣ መገልገያዎች እና ቁሳቁስ በጥንቃቄ ከመስክ ተነስተው በጥንቃቄ መወገድ አለባቸው፡፡

**ምንጭ፡** የዓለም ጤና ድርጅት፣ የአሜሪካ በሽታ መቆጣጠሪያ ማዕከል (CDC) እና ሌሎች ተዛማጅ የድረ ገጽ ምንጮች

- All surfaces and tools s/he may have recently touched should be cleaned and disinfected.

- ✓ In spaces where queuing may happen (including latrines and hand washing stations), consider marking safe distance of 2 meters (6.56ft) on ground or railings;
- ✓ Meetings on site should be avoided at all times. Instruction to workers should be given in open spaces and maintaining physical distance;
- ✓ If construction activities happen in an enclosed space, the site should be ventilated as much as possible, for example leaving doors and windows open during the working day;
- ✓ Due to potential sudden access restrictions, all materials and equipment should be carefully and safely stored before leaving the site at the end of every day;
- ✓ When receiving and unloading goods and construction materials, workers should keep distance from the drivers at all times. When possible, drivers should remain in their vehicles. If drivers must unload the goods for safety reasons, they should do so without the help of the workers and they should wash or clean their hands before and after. Any contact between deliverers and receivers should be avoided (including delivery papers and pens for signature, etc.). It is recommend that everyone needing to sign paperwork have their own pen or wash their hands after.

### v. Hand Washing, Hygiene and Cleaning

- ✓ Provide adequate hand-washing station with water and soap or an alcohol-based hand sanitizer (min. 60% alcohol). Ensure water and soap are topped up regularly;
- ✓ Clean the hand washing facilities regularly during the day, establishing a clear cleaning plan;
- ✓ Tools, reusable PPE and frequently touched surfaces should be cleaned and disinfected frequently (at least daily);



- ✓ If possible, appropriate latrine facilities should be made available inside the compound and be kept cleaned. In any case, workers should be encouraged to wash their hands before and after using the latrines;
- ✓ Dedicated eating, break and prayer areas should be identified on site and access should be staggered to reduce risk of congestion. Workers should keep physical distance while eating, praying and having a break;
- ✓ Provide safe drinking water dispensers and one-time cups, or encourage workers to carry an individual cup;
- ✓ All solid waste (excluding construction materials) should be put immediately in closed bins or closed bags and not left for someone else to clear up;
- ✓ Separate and collect all solid waste that could serve as transmission vector. To avoid contact with waste bags, use double plastic bags (for instance when removing a filled waste bag, cover tightly and wrap with a second plastic bag). Store the waste for at least 72 hours before disposing;
- ✓ Store leftovers construction materials for at least 72 hours before disposing.

### vi. Upon Completion

- The facility should be carefully cleaned and disinfected prior to the handover;
- All waste, construction materials, tools and equipment should be removed from the site and disposed safely.

(**Source:** WHO, CDC and Other Related web page sources)

የመዝናኛ ገጾች
INTERTAINMENT PAGE

# ILAALCHA

Tokko lama jettee
Adeemsa karaa kee
Galma geessee arguuf
Waan yaade garaan kee

Sakaalama hedduu
Uggurama jabaa
Deemsa kee keessatti
Situquu jalqabaa.

Kanumati hin beekne
Kaateef baatee isaa
Akka Hidda baddaa
Xaxee sikuffisaa

Osoo akka haasaaf
Oduu Gadheetiilaa
Namuma taateetuu
Hin jiraattu silaa

Ati yoo milkaa'uuf
Karoorfatte galma
Mul'ata kee laalii
Kan si godhu nama.

Oduuf Jibbaa namaaf
Hin kutatin Abdii
Fuuldura kee laali
Ajaan booda baddii

Silaa ilaalchi namaa
Akkuma bifa isaa
Garaagaraam beekii
Adeemsi hundasaa

Inni kaan namummaa
Keetiif sijaallataa
Kaanimmoo jiraachuu
Kee jibbee maraataa.

Jedhan kan jedhamuu
Kan sidiigu gochaa
Hin dhiphatin dhiisii
Hundumtuu ilaalchaa!

(Maddi: Fuula 'Telegram' Mujahid Habo Official)

## መኖር መኖር መኖር!

በማይ በምሰማው
አንዳንዴ ስገረም
ህይወት ከናላማው
ስህተት ይሆን እንዴ፤ በሞት የሚታረም?
ማለት ይቃጣኛል
የዚህ ዓለም ኑሮ
ጥያቄ ወርውሮ
ምላሽ ያሳጣኛል፡፡
ደሞ አንዳንዴ ሳስብ
ስለሰው ልጅ ስራ
የሰናፍጭ ቅንጣት በምታክል ጥበብ
የሚንድ ተራራ
በጨለመ ምድር፤ ብርሃን እሚዘራ
በሰማይ ጎዳና፤ ወፍ የሚያሰማራ
ባህርን የሚያጠምድ ፤መብረቅ የሚገራ፤
ከቀለሞች መሀል ፤ ምስል የሚያነቃ
ከዝምታ መሀል፤ የሚያፈልቅ ሙዚቃ
በቃሉ በጣቱ
በቅመም ቅንጣቱ
ዘልቆ የሚያከመኝ
እንደ ሳንዱቅ ከፍቶ፤ መልሶ እሚገጥመኝ
ይህንን ሁሉ ሳይ፤ ህይወት እየጣመኝ
መኖር መኖር መኖር፤ መኖር ነው የምመኝ ፤

(ምንጭ፡-ከበእውቀቱ ስዩም ቴሌግራም ገጽ)

### *Baacoo-(Kolfaaf)*

Namichatu maagaalaa/gabaa dhaqee meeshaa bitatee harreetti fe'ee gara manaa osoo deemaa jiruu harreen dadhabdee deemuufii didde. Namtichis harree kana afaanin itti iyyus, uleedhaan reebus, gurra qabee harkisus, ofdura deemuufii diddee danqame. Yeroo kanatti malli tokko dhufeef; Malli kunis qaaraa/qacaa barbarree bitee kiisha keessaa qabu cabsee hudduu harrettiitti suduu ykn cuqqaaluu ture. Innis yaada kana dafee hojiirra oolche. Akkuma inni qaaraa kana hudduu harrettiitti cuqqaleen harreenis namticha gattee figicha takkaa hin jirre itti fuute. Amma dubbiin garagaltee namtichi harree kana fiigee bira dhaqqabuu dadhaba. Innis malli harree akkanatti humna itti hore kun anaafis dalaguu hin dhabu jechuun qacaa hafte hudduutti cuqqaallate. Sana booda namtichi inumaa harrettii bira darbee durse mana gahe jedhama.







# ADDRESS & LOCATION OF ELILLY INTERNATIONAL HOTEL, SISTER COMPANY OF GEBECON PLC




Kazanchis Business District
Kirkos Sub-City 17/18
Tel: +25115587777/+25115587778
Fax: +25115585200
P.O. Box: 29118, Addis Ababa, Ethiopia
Email: info@elilly.com.et
Website Address: www.elilly.com.et

# Your First Choice in Hospitality!



# Elilly Modern Mall Complex Design